በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

## የከተማ ፕላን፣ ፅዳትና ውበት ቢሮ





# ከከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር ዘላቂ የከተማ ግብርና ማስፋፊያ ጥናት (የታተመ)

በዘርይሁን ተጻፈ ገ/ማርያም

መጋቢት 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

የሠንጠረዦች ዝርዝር ..... iv
የምስል ዝርዝር ..... iv
የምህፃረ-ቃላት ትርጉም ..... v
ክፍል አንድ ..... 1
1.መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ መነሻ ..... 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ..... 4
1.3.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ ..... 4
1.4.የጥናቱ ወሰን ..... 5
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 5
1.6.የጥናቱ አግባብነት ..... 5
1.7. የአጠናን ዘዴ ..... 6
1.8. የጥናቱ ውስንነት ..... 7
ክፍል ሁለት ..... 8
2.ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ..... 8
2.1.የከተማ ግብርና ..... 8
2.1.1. የከተማ ግብርና ምንድነው? ..... 8
2.1.2.የከተማ ግብርና ዓይነቶች ..... 9
2.1.3.የከተማ ገበሬዎች እነማናቸው ..... 9
2.1.4. የከተማ ግብርና ዬት ..... 11
2.1.5. የከተማ ግብርና ቅድመ ሁኔታ፣ ጥቅሞች፣ አሉታዊ ተፅዕኖዎችና እና ማነቆዎች ..... 17
2.2. የተሞክሮ ዳሰሳ ..... 28
2.2.1. ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮ ዳሰሳ ..... 28
2.2.2. የአፍሪካ አገሮች ተሞክሮ ..... 30
2.2.3.የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶች ..... 32
ክፍል ሶስት ..... 34
3.የከተማ ግብርና ከከተማ ፕላን አንፃር ..... 34
3.1. የከተማ ፕላን ምንድነው? ..... 34
3.2.የከተማ ፕላን በታዳጊ አገሮች ..... 35
3.3. የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ ለማድረግ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ..... 35

3.4. በታዳጊ አገሮች የከተማ ፕላን አዘጋጆች አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ለከተማ ግብርና ያላቸው ፋይዳ ........ 38
3.5. የከተማ መሬት ፕላን ዝግጅት መርሆዎችና ዘዴዎች፡ ከከተማ ግብርና ጋር ያላቸው ቅንጅት ........ 39
3.6. የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያዎች ጋር ማቀናጀት ........ 40
ክፍል አራት ........ 41
4. በኢትዮጵያ በከተማ ግብርና ዙሪያ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች ትንተና ........ 41
4.1.የኢፌድሪ ህገ መንግስት ........ 41
4.2.ፖሊሲ ........ 42
4.3. አዋጅ ........ 45
4.3.1. የከተማ ፕላን አዋጅ ........ 45
4.3.2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ........ 45
4.3.3. የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ በአዋጅ ........ 46
4.4. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ........ 46
4.5. ስትራቴጂ ........ 47
ክፍል አምስት ........ 51
5. መረጃን መተንተን ........ 51
5.1.የከተማ ግብርና ነባራዊ ሁኔታ በኢትዮጵያ ........ 51
5.1.1.የግብርና ዓይነቶች ........ 51
5.1.2.የከተማ ግብርና ሥፍራዎች ........ 52
5.1.3. የከተማ ግብርና ጥቅሞች ........ 52
5.1.4. የግብርናው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ........ 54
5.2. ከፕላን ጋር በተገናኘ ለከተማ ግብርና ማነቆ የሆኑ ጉዳዮች ........ 55
5.2.1.በፕላን ተቋማት በኩል- ........ 55
5.2.2.በፖሊሲ ማዕቀፍ ........ 60
5.2.3. በአመለካከትና ባህላዊ እይታ ችግር ........ 61
5.3.በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና ቁልፍ ማነቆዎች ........ 62
5.4.የከተሞች አስተዳደር ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር ........ 64
ክፍል ስድስት ........ 66
6.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ........ 66
6.1. ማጠቃለያ ........ 66
6.2. በኢትዮጵያ ለከተማ ግብርና ማነቆዎች ሊሰጡ የሚገባቸው የመፍትሔ ምላሾች ........ 66
6.2.1.የፕላን ተቋማትን አደረጃጀትና የሃብት ሥርጭትን መለወጥ ........ 67
6.2.2. የከተማ ፕላን ፖሊሲ ማዕቀፍን ማሻሻል ........ 72
6.2.3. የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ........ 74
6.3. በከተሞች ለከተማ ግብርና የሚመከሩ ስፍራዎችና ስታንዳርዶች ........ 75

6.3.1. **ለተለያዩ የከተማ ግብርና አይነቶች የመስክ ምርጫ አስፈላጊ መስፈርቶች** ............................ 75
6.3.2. **የግብርና ስፍራዎች መነሻ ስታንዳርድ** ............................................................................ 79
**ዋቢ መፃህፍት** ............................................................................................................ 91

# የሠንጠረዦች ዝርዝር


ሰንጠረዥ 1. በአንድ ከተማ የሚለማ የከተማ ግብርና ዘላቂነትን ሊያመላክቱ የሚችሉ አቅጣጫዎች..........27

ሰንጠረዥ 2. የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያዎች ጋር ማቀናጀት..............................40

ሰንጠረዥ 3. የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ዳሰሳ ........................................................................60

ሰንጠረዥ 4. የጥናቱ ናሙና ከሆኑ ባለሞያዎች የተመረጡ የከተማ ግብርና ቁልፍ ማነቆዎች ..................63

ሰንጠረዥ 5. በዓለማችን የተለያዩ ከተሞች ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር ........................................65

ሰንጠረዥ 6. በኢትዮጵያ በተወሰኑ ከተሞች ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር......................................65

ሰንጠረዥ 7. የቀንድ ከብት እርባታን ለማካሔድ የሚያስፈልግ የወለል መጠን ስታንዳርድ በከብቶች ዝርያ.80

ሰንጠረዥ 8. የወለል መጠን ስታንዳርድ በወተት ከብቶች የደም መጠን አንጻር ......................................81

ሰንጠረዥ 9. ለሚደልቡ ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን ስታንዳርድ በከብቶች ዝርያና በእድሜ82

ሰንጠረዥ 10. ለሚደልቡ ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን ስታንዳርድ በከብቶች የደም መጠንና በዕድሜ ..........................................................................................................83

ሰንጠረዥ 11. የምርት ማከማቻ ቦታ..........................................................................................85

ሰንጠረዥ 12. የበግ እና የፍዬል እርባታ መጠለያ የውስጥ ስፋት መጠን ................................................85

ሰንጠረዥ 13. የዶሮ ማራቢያ ስፍራዎች ርቀት ...........................................................................87

ሰንጠረዥ 14. ለዶሮ እርባታ የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት ...................................................................87


# የምስል ዝርዝር


ምስል. 1 የአራቱ ዞን የከተማ ሞዴል ..........................................................................................12

ምስል. 2 የከተማ ግብርና ጥቅም.................................................................................................14

ምስል. 3 የችካነ ከተማ አዳራሽ አረንጓዴ ጣሪያ ..............................................................................15

ምስል. 4 Von Thünen model.................................................................................................16

ምስል. 5 ዘመናዊ የከብት እርባታ በረት.......................................................................................84

ምስል. 6 የበግ እና የፍየል እርባታ............................................................................................86

ምስል. 7 የዶሮ እርባታ ..........................................................................................................88

ምስል. 8 ዘመናዊ የዶሮ እርባታ..................................................................................................88

ምስል. 9 ዘመናዊ የንብ እርባታ..................................................................................................90

## የአዝሎች ዝርዝር

አዝል 1. ለከተማ ፕላን ባለሞያዎች የቀረበ መጠይቅ ........................................96

አዝል 2 ለግብርና ባለሞያዎች የቀረበ መጠይቅ ........................................100

አዝል 3 ለከተማ ገበሬዎች የቀረበ የቃል መጠይቅ ........................................106

አዝል 4 ለዳሰሳው ጥናት የታቀፉ ከተሞች ........................................106

## የምህፃረ-ቃላት ትርጉም

**ኢፌዴሪ፡-** የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**ከልኮሚ፡-** የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

EIAR፡- Ethiopian Inistitute of Agricultural Research

**EPM-፡-** Environmental Planning and management

**FAO፡-** Food and Agriculture Organisation

FDRE፡- Federal Democratic Republic of Ethiopia

GDP፡- Gross Domestic Product

IDRC፡- International Development Research Centre

**NSW፡-** New South Wales

**UN፡-** United Nations

UNDP፡- United Nations Development Program

**USA፡-** United States of America

USDA፡- United States Department of Agriculture

WB፡- World Bank

# ክፍል አንድ

## 1.መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን ኢትዮጵያ መንግስት ሠፊ መሠረት ያለው ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ልማትን የማፋጠንና ድህነትን የማስወገድ ዓላማ ያለው የሀገሪቱን አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያስችል የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ማቀዱ ይታወቃል:: የዚህም ዕቅድ ራዕይ “በ2017 በህዝቦች ተሳትፎ እና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው::-----” ከዚህ ዕቅድ አምስት መሠረታዊ ዓላማዎች ከፊሎቹ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችን ማሳካት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው:: ከምዕተ ዓመቱ ግቦችም አንዱ ድህነትን መቀነስ እንደሆነ ይታወቃል::

ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት አረንቋ ተላቃ በአጭር ጊዜ ውስጥ በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ማሰለፍ የሚቻለው በከተማ ውስት የተንሰራፋውን ድህነትን በማስወገድም ጭምር በመሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ የሥራ ዕድልን በመፍጠር የከተማ ህዝብ ኑሮን ለማሻሻል የህዝብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ያላቸው ድርሻ ሲታይ በከተሞች ከማንም የልማት ተቋማት በላይ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ አስፈላጊ በመሆኑ የከተማ ግብርናን ማስፋፋት ለድህነት ቅነሳ መሳሪያነት እንደ አንድ አማራጭ መውሰድ ተገቢ ነው::

የከተማ ግብርና በከተማ አካባቢ የሚገኘውን የሰው ጉልበት፣ መሬትን፣ ውሀን፣ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እና ምርቶችን በመጠቀም የተለያዩ የግብርና ምርት ውጤቶችን አምርቶ ለገበያ የሚያቀርብ በከተማ ውስጥና በከተማ ዳርቻ የሚገኝ ኢንዱስትሪ ነው:: የከተማ ግብርና ባደጉም ሆነ ባላደጉ አገሮች ከድህነት ቅነሳና የምግብን ዋስትና ከማረጋገጥ አኳያ

ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ እየታመነ ቢመጣም ዘርፉ በሁሉም አገሮች በከተማ ፕላን ተገቢውን ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል፡፡

የከተማ ግብርና የዜጎችን የምግብ ዋስትና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በተለይም በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ድሃ ሴቶችን እና ከገጠር ወደ ከተማ የፈለሱትን ተጠቃሚ ከማድረጉም ባሻገር ለነዋሪዎች የሥራ ዕድል ምንጭ በመሆን ለድህነት ቅነሳ እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ የከተሞችን ውበት በመጠበቅ ለከተማ አካባቢዎች የሚሰጠው ጥቅም እጅጉን የጎላ ነው፡፡ ዘርፉ ወደ አገሪቱ ከተሞች ቢስፋፋ ለከተሞችና ለነዋሪዎች ዕድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደሚችል በማመን ከፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር ዘርፉ ያለበትን ችግር ለመለየት ይህ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የዚህ ጥናት ሰነድ በጠቅላላው ስድስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱን መግቢያ የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የተዛማጅ ፁሑፎችን የዳሰሰ ሆኖ ሶስተኛው ክፍል የከተማ ግብርናን ከፕላን አንፃር ይቃኛል፡፡ ከክፍል አራት ጀምሮ በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና የሚዳስስ ይሆናል፡፡ ክፍል አራት የህግ ማዕቀፎችን ሲያብራራ ክፍል አምስት በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና ነባራዊ ሁኔታ እና ዘርፉ ያሉበትን ችግሮች የለየ የጥናቱን ግኝቶች የሚያብራራ ክፍል ነው፡፡ በክፍል ስድስት በኢትዮጵያ ለከተማ ግብርና ማነቆዎች ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሔ ሃሳቦች ከተብራሩ በኋላ በከተማ ውስጥ ተስማሚ የግብርና ቦታዎችን እና ስታንዳርዶችን በመጠቆም ጥናቱ በዚሁ ይቋጫል፡፡

### 1.2. የጥናቱ መነሻ

በአለማችን ከተማነት በማደግ ላይ ባሉ አገሮች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ነው፡፡ ይሁንና ይህ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣው ከተማነት በርካታ ተያያዥ ችግሮችን ማለትም ሥራ-አጥነት፣ ድህነት፣ የጤና መዛባት፣ ለኑሮ አመቺ ያልሆኑና የቆሸሹ፣ የተጎሳቆሉና ፍርስራሽ ቤቶች መብዛት፣ የአካባቢ ብክለትንና የመሳሰሉትን አስከትሎ የመጣ በመሆኑ ለአብዛኛው ታዳጊ አገሮች ፈታኝ ሆኖባቸዋል፡፡ ስታትስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአለማችን ህዝብ ግማሽ ያህሉ ማለትም ሶስት ቢሊዬን ያህሉ የሚኖረው በከተማ ውስጥ ሲሆን ይኸው ህዝብ የምድራችንን የቆዳ ስፋት 3 በመቶ ብቻ በሆነው ተከማችቶ ይገኛል (UNFPA, 1993).፡፡ የከተማነት ዕድገት በንፅፅር ሲታይ በ1800 ዓ.ም በዓለማችን በከተማ

ውስጥ ይኖር የነበረው ህዝብ ከ5 በመቶ በታች የነበረ ቢሆንም ይህ አሀዝ በ2000 ዓ.ም ወደ 47 በመቶ አድጎ በ2030 ደግሞ 65 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይገመታል (UN፣ 1990፣ 1991)፡፡ እንደዚሁም በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ሪፖርት እንደሚያሳየው በሚቀጥሉት ዘመናት በታዳጊ አገሮች ከ90 በመቶ በላይ የህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚታየው በትልልቅ ከተሞች ሲሆን አብዛኛው ህዝብ ደግሞ ድሃ ነው ተብሎ ተገምቷል፡፡ በአፍሪካና በኢስያ አሁንም ዝቅተኛ የከተማ ህዝብ በሚኖሩባቸው አህጉራት እ.አ.አ እስከ 2025 የከተማው የህዝብ ቁጥር 54% ይሆናል ተብሎ ይገመታል (UN, 2002)፡፡ ምንም እንኳ ከተማነት ለአንድ አካባቢ ዕድገትና ስልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢኖረውም በከተማነት ዕድገት ምክንያት በሰዎች ጤና፣ በኑሮ፣ እና በአካባቢ ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ከፍተኛ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በዚህ ረገድ ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች ከዓለማችን ሁሉ ይልቅ ከፍተኛ የዕድገት ፈተና እንደሚያጋጥማቸው ታምኗል፡፡ ይህም አካባቢ የዓለማችንን እያደገ የሚሄድ በከፋ ድህነት አረንቋ ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ አብዛኛውን ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ተገምቷል፡፡ በ1980 እ.ኤ.አ ከአሥር አንዱ ድሃ ህዝብ የሚኖረው ከሳሀራ በታች ባሉ አገሮች ሲሆን ይህ አሀዝ በ2000 ከሶስት አንድ በመሆን አድጓል፡፡ የወደፊት ግምቶች እንደሚያሳዩት በክፍለ አህጉሩ በከተማ የሚኖረው የከተማ ድሃ ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ የሚያድግ በመሆኑ አሃዙ ከሁለት ሰው አንድ ይሆናል ተብሎ ተተንብዮአል፡፡ እአአ እስከ 2030 የክፍለ አህጉሩ ህዝብ ግማሽ ያህሉ ከተሜ ይሆናል ተብሎ ሲገመት አብዛኛው ህዝብ ደግሞ የሚኖረው በጎስቋላ ቤቶች ያለበቂ የምግብ፣ የውሃና የጤና አገልግሎት አቅርቦት በመሆኑ የአካባቢው የድህነት ጥልቀት አሳሳቢ እንደሆነ የዘርፉ አጥኚዎች ይናገራሉ (WB, 2008)፡፡

ኢትዮጵያም በዚህ ቀጠና ከሚገኙ አገሮች አንዷ በመሆኗ ፈጣን የከተሞች ዕድገት በጥንቃቄ ካልተመራ በስተቀር በከተማ መስፋፋት ምክንያት በሚመጡ ጠንቆች ተጎጂ ልትሆን እንደምትችል መገመት አያዳግትም፡፡

ኢትዮጵያ ምንም እንኳ የረጅም ዓመታት ታሪክ ባለቤት፣ ልዩልዩ ባህላዊ ቅርሶች ያሏት፣ ለፈጣን ዕድገት አመቺ የሆኑ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ብትሆንም አብዛኛው

የሀገሪቱ ህዝብ አሁንም የሚኖረው ከድህነት ወለል በታች በሆነ የኑሮ ደረጃ ነው (FDRE, 2002)፡፡ በሀገሪቱ ከተማነት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለው የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን አስከትሎ ነው፡፡ የከተሞቿ እድገት የመጣው በከተሞች በተፈጠረ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ዕድገት ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በከፍተኛ ፍጥነት ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ ባለው የሰው ቁጥርና በከተማ ውስጥ ባለው ከፍተኛ የውልደት መጠን ነው፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች ባሻገር ቀደም ሲል በነበረው የደርግ ሥርዓት አገሪቱ ትከተል በነበረው የተሳሳተ የእዝ ኢኮኖሚ ስርዓት ከተሞች ለአስከፊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች የተጋለጡ ሆነዋል፡፡ ሥራ-አጥነት፣ ድህነት፣ የጤና መዛባት፣ ለኑሮ አመቺ ያልሆኑ የቆሸሹ አካባቢዎች፣ የተጎሳቆሉና ፍርስራሽ ቤቶች መብዛት፣ የአካባቢ ብክለት እና የመሳሰሉት የሀገሪቱ ከተሞች አይነተኛ መለያዎች ሆነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አብዛኞቹ የሀገሪቱ ከተሞች በፕላን እየተመሩ ባለመሆናቸው ውበት የሌላቸው ሆነው ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና በሚፈለገው ደረጃ የዘላቂ ዕድገት መሠረት የማይታይባቸው ሆነዋል፡፡

ምንም እንኳ የከተማ ግብርና በከተሞች ያለውን የምግብ ዋስትና እጦትና የድህነት ችግርን እንደዚሁም የከተሞች አካባቢ ሥነ-ምህዳር የማስጠበቅ እምቅ ሃይል እንዳለው በአብዛኛው ህዝብ ግንዛቤው እያደገ ቢመጣም በሀገራችን ከተሞች ዘርፉ ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በሀገሪቱ ከተሞች የከተማ ግብርና በተለያዩ ማነቆዎች የተተበተበ በመሆኑ ለግብርናው አስቻይ ዕድሎችን መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ አሁን ዘርፉ ያለበት ችግር ለዚህ ጥናት መነሻ ሆኗል፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

#### 1.3.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ በከተማ ግብርና ላይ የተጠኑ ሳይንሳዊ ጥናቶችን በመዳሰስ በዚሁ መሰረት በኢትዮጵያ ከተሞች እና አካባቢያቸው ከከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር ዘላቂ የከተማ ግብርና ለማስፋፋት የሚያግዝ አስቻይ ሰነድ ማዘጋጀት ነው፡፡

#### 1.3.1.1.ዝርዝር ዓላማዎች

1. በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና ነባራዊ ሁኔታ መዳሰስ፣
2. ከከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር የከተማ ግብርና ማነቆዎችን መለየት፣
3. ሴክተሩ በሀገራችን በሚስፋፋበት ሁኔታ አስቻይ የመፍትሄ ሀሳቦችን መሰንዘር፣ እና
4. በከተማ ውስጥ ተስማሚ የከተማ ግብርና ስፍራዎችን እና የግብርና ቦታ ስታንዳርዶችን መጠቆም ናቸው፡፡

### 1.4.የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን በኢትዮጵያ የከተማ ግብርናን ከከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አንፃር ያለበትን ማነቆ መለየትና የመፍትሔ ሀሳቦችን መሰንዘር  ነው፡፡

### 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በየደረጃው ላሉ የከተማ ፕላን አዘጋጆች እና አስተግባሪዎች የከተማ ግብርና ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራና አማራጭ የገቢ ምንጭነት፣ ብሎም የምግብ ዋስትናን ለከተማው ድሃ ለማረጋገጥ ስለሚጫወተው ሚና በመረጃ ምንጭነት በማገልገል በዕለት ተዕለት ሥራቸው ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጡት የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ በሀገራችን በከተማ ግብርና ዙሪያ ለሚጠኑ ጥናቶች ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

### 1.6.የጥናቱ አግባብነት

የዚህ ጥናት ዋና ዋና አግባብነቶች የሚከተሉት ናቸው

1. የከተማ ግብርና በአብዛኞች ከተሞች ፕላን ዝግጅት ውስጥ ተካቶ ትኩረት ተሰጥቶት በዝርዝር እየተሠራ አለመሆኑ እና በአፈፃፀምም ችግር ያለበት በመሆኑ፣
2. በኢትዮጵያ ከተሞች እና አካባቢያቸው ያለው የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር እየተጎዳ በመሆኑ እና በዚህም ችግር ምክንያት ለከተሞች ተፈጥሮአዊ ሚዛንን አጠባበቅ መሥራት የሚያስፈልግ በመሆኑ፣

3. ከተሞች በአረንጓዴ ልማት የተዋቡ አለመሆናቸው፣
4. በሀገራችን በተለይም በከተሞች ሰፍኖ የሚገኘውን የሥራ አጥነትና የድህነት ችግርን ለመቅረፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞችን ማጠናከር፣ ማስፋፋትና ማልማት አይነተኛ መሳሪያ እንደሆነ የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ አገሪቱ ለነደፈችው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና ለምዕተ ዓመቱ ግብ ስኬት የከተማ ግብርና የበኩሉን ድርሻ እንደሚጫወት ስለሚታመን ናቸው::

### 1.7. የአጠናን ዘዴ

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተግባራዊ የሆነው የዳሰሳ ጥናት ሲሆን የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል:: የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች በፁሁፍ-መጠይቅ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ እና በአካል የዓይን ምልከታ በማድረግ የተሰበሰቡ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥ ከሆኑ መፃህፍት፣ የከተማ መዋቅራዊ ፕላኖችን በመቃኘት፣ ሌሎች ተያያዥ የሆኑ የህግ ማዕቀፎችንና ስታትስቲካዊ መረጃዎችን በመዳሰስ እና ታትመው ከወጡትና ከኢንተርኔት ከተገኙ ምንጮች ተሰብስበዋል:: በመጨረሻም የተሰባሰቡትን የጥናቱን መረጃዎች በመጠንና በጥራት ተጠናቅረውና ተተንትነው ውጤታቸው ቀርቧል::

የጥናቱን ምላሽ ሰጪዎችን፤ የፕላን እና የግብርና ባለሞያዎች ለመለየት ግብርናው በሀገሪቱ በሁሉም ከተሞች ካለው ተመሳሳይ ባህሪ አንፃር ናሙና ከተሞች በውሳኔ ተለይተዋል:: እነዚህ ናሙና ከተሞች በመጠን ከትልልቁ እና ከትንንሹ ውክልና እንዲኖራቸው ተደርጓል:: ናሙና የፕላን ባለሞያዎቹ የክልል የፕላን ኢንስትቲዩት እና የከተሞች የፕላን የሥራ ሂደት አባላትን ያካተተ ሲሆን ናሙና የግብርና ባለሞያዎች የተመረጡት ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና በናሙናነት ከተመረጡ ከተሞች የግብርና የሥራ ሂደቶች ነው:: የጥናቱ ረቂቅ የመጨረሻውን መልክ ከመያዙ በፊት በጥናት ቡድኑ፣ ከባለድርሻ አካላት እና በመስሪያ ቤቱ ባለሞያዎችና የበላይ አመራር አካላት ጋር በስፋትና በጥልቀት በረቂቅ ጥናቱ ላይ ሀሳብ በመለዋወጥ ጥናቱን ማዳበር ሌላው የጥናቱ አካል ነበር::

### 1.8. የጥናቱ ውስንነት

ከተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች የመጀመሪያ ደረጃ መረጃን ለመሰብሰብ በሃገሪቱ ያሉ የፕላን እና የግብርና የሥራ ሂደቶችን ለማግኘት በግንኙነት መስመሮች የመረጃ እጥረት ምክንያት ከርቀት ያሉ የክልል ከተሞችን የጥናቱ ናሙና አለማድረግ የዚህ ጥናት አንደኛው ውስንነት ሲሆን በሀገር ደረጃ የከተማ ግብርና የተመለከቱ የመረጃ እጥረቶች ሌላው የዚህ ጥናት ውስንነቶች ናቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ መንገድ የተላኩ መጠይቆች ምላሽ አለማግኘት እንደዚሁ ሌላው ውስንነት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

### 2.1.የከተማ ግብርና

### 2.1.1. የከተማ ግብርና ምንድነው?

የከተማ ግብርና የተለያዩ ክፍሎች በተለያየ ሁኔታ ለመተርጎም የሞከሩ ሲሆን ትርጉሙ ተመሳሳይነት ቢኖረውም ባለው የትንታኔ ጥልቀት ለየት ብለው መታየታቸው አልቀረም። በቀላል አገላለፅ የከተማ ግብርና ማለት በከተማ ውስጥና በከተማ አካባቢ በአነስተኛ ቦታ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል እና ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴን በመጠቀም የምግብና የሌሎች የግብርና ምርት ውጤቶችን አምርቶ እና አቀነባብሮ ለገበያ የሚያሰራጭ የሥራ ዘርፍ ነው።

በሌላ በኩል የሃብት አጠቃቀምን ግምት ውስጥ በማስገባት የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የከተማ ግብርናን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል። የከተማ ግብርና የከተማውን የህዝብን ዕለታዊ የፍጆታ ፍላጎትን ተከትሎ መሬትንና ውሃን በመጠቀም በአነስተኛ ቦታ ላይ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል የተፈጥሮ ሀብትንና የከተማ ቆሻሻን በቀጥታና ዳግም ጥቅም ላይ በማዋል የተለያዩ ለምግብና ለኃይል ምንጭነት የሚያገለግሉ የእፅዋትንና የከብት ምርት ውጤቶችን በከተማ ውስጥና በከተማ አካባቢ የሚያመርት፣ የሚያቀነባብር እና ለገበያ የሚያሰራጭ ኢንዱስትሪ ነው ይላል *(Smit, 1996:3)*።

ከላይ ከተሰጡት ትርጉሞች በተጨማሪ Tinker (1994) የከተማ ግብርና ምንነት ሲተነትን እንደሚከተለው ይገልፀዋል። የከተማ ግብርና ማለት በከተማ ውስጥና በከተማ አካባቢ የምግብ ሰብሎችን፣ ፍራፍሬዎችን፣ የምግብ ዛፎችን፣ ለመድሃኒት የሚሆኑ ተክሎች፣ አበባዎች እና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልሉ የዕፅዋት ምግቦችንና የቀንድ ከብቶችን፣ የዶሮ እርባታን፣ ዓሳን፣ እንዲሁም አሳማንና ማርን ያጠቃለሉ የእንስሳት ምግብ ውጤቶችን በከተማና በከተማ አካባቢ አምርቶ ለገበያ የሚያቀርብ የሥራ ዘርፍ ነው ብሏል።

### 2.1.2.የከተማ ግብርና ዓይነቶች

የ1996 የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ሪፖርት እንዳብራራው የከተማ ግብርና በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተከፍሏል፡፡ እነሱም፡

1. የውሃ ውስጥ ዕፅዋት (aquaculture)፦ በውሃ ውስጥ የሚመረቱትን አትክልትንና እፅዋትን ያጠቃልላል፡፡
2. የአትክልትና ፍራፍሬ (horticulture)፦ በጓሮ የሚመረቱትን የጓሮ አትክልት ምርት እና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትን እንደዚሁም በቤቶች ጣሪያ ላይ (roof garden) እና በህንፃዎች በረንዳ እና ግድግዳ ላይ (vertical farming) የሚተገበሩ የከተማ ግብርና አይነቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡
3. የከብት ዕርባታ (animal husbandry)፦ የከተማ ውስጥ ከብት ዕርባታ ከሀገር አገር እንደ አገሩ ባህልና ፍላጎት የሚለያይ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ፦ የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየል፣ የአሳማ እና የቀንድ ከብቶችን እርባታ ናቸው፡፡
4. አግሮፎረስተሪ (agroforestry)፦ በከተማ ውስጥ ለተለያዩ ዓላማዎች ማለትም ለአካባቢ ውበት፣ ለጥላ፣ ለማገዶ እና ለሌሎች ጉዳዮች የሚተከሉ ዛፎችን ያጠቃልላል፡፡
5. ሌሎች፦ ከላይ ከተጠቀሱት የግብርና ዓይነቶች ውጪ ያሉትን ለምሳሌ የመድሃኒት ዕፅዋት ምርት፣ የንብ ማነብ፣ የጥሪኝ እርባታ፣ የአበባ ምርት፣ የከብት መኖ ምርት፣ ማገዶ ምርት እና የመሳሰሉት ያጠቃልላል (UNDP,1996)፡፡

### 2.1.3.የከተማ ገበሬዎች እነማናቸው

የከተማ ገበሬዎች በሁሉም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን አብዛኛው የከተማ ገበሬዎች ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ላይ ያሉ ሆነው የምግብ ተክልን ለዕለታዊ ፍጆታ ወይም ለገቢ ምንጭነት በጥቂት መሬት ላይ መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚያመርቱ ናቸው *(Jacobi et al, 2000:4)፡፡*

አንዳንድ ጥናቶች እንደገለፁት የሴቶች ተሳትፎ በአንዳንድ የከተማ ግብርና ዘርፎች ለምሳሌ በጓሮ አትክልትና በአነስተኛ የከብት እርባታ ዘርፍ ከፍተኛ ብልጫውን ይወስዳሉ። ሴቶች በከተማ ውስጥ በግልፅ በሚተገበሩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ብዙውን ጊዜ በጥቃቅንና አነስተኛ የምርት እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተው ይታያሉ። ጥናቱ ጨምሮ እንደገለፀው ወንዶች ብዙውን ጊዜ በገበያ ተኮር ግብርና ላይ ብልጫውን ሲወስዱ በጥቂት አገሮች ህፃናት በማረምና ውሃን በማጠጣት በዘርፉ ይሳተፋሉ።

በሌላ በኩል ሞውጎት የተባለ የዘርፉ ተመራማሪ የከተማ ገበሬዎች በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተዋጽኦ ያላቸው መሆኑን ገልጾ የዘርፉን ተሳታፊዎች ከዓላማቸው አንፃር በሶስት ዓይነቶች ይከፋፍላቸዋል (Mougeot, 1993: 14)።

1. ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ገበሬዎች፦ እነዚህኞች ገበሬዎች በግብርና ሥራ ላይ ለመሰማራታቸው ምክንያት በአብዛኛው ኑሮን ለማሸነፍ እና ከዘርፉ በሚገኘው የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን በምግባቸው ለማካተት ነው።
2. መካከለኛ ገቢ የጓሮ አትክልተኞች፦ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ የከተማ ገበሬዎች በግብርናው ላይ የተሰማሩት ተጨማሪ ምግብን እና ገቢን ለማግኘት ነው።
3. ሻጭ ገበሬዎች (agri business farmers)፦ እነዚህ የከተማ ገበሬዎች ከዘርፉ በመደበኛነት ገቢ ለማግኘት የተሠማሩ ናቸው።

ከላይ በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ከተመደቡት ውስጥ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውም ሥራውን ቀጥሮ በማሠራት የሚሳተፉ እንደሆነና በሶስተኛው ክፍል ውስጥ ያሉት አናሳዎች እንደሆኑ ጥናቶች ጨምረው ይጠቁማሉ።

በአብዛኛው የከተማ ግብርና የሚካሄደው በቤተሰብ ደረጃ ቢሆንም በተለያዩ አካባቢዎች ሥራው በጋራ ወይም በቡድን ይተገበራል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ቢያንስ አምስት ያህል ማህበሮች በወንዞች ዳርቻና በትንንሽ ኩሬዎች አካባቢ በግብርና ላይ ተሰማርተው እንዳሉ የወ/ሮ አክሱማይት ገ/እግዚአብሔር ጥናት ያሳያል *(Axumait; 1993: 15).*

### 2.1.4. የከተማ ግብርና ዱት

የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥና በከተማ ዳርቻ የሚተገበር ሲሆን በፕላን ዝግጅት የሚከተሉት የከተማ ቦታዎች ለከተማ ግብርና በሚረጡ አግባብነት እንዳለው በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በ2004 ዓ.ም የተዘጋጀው የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ማንዋል ውስጥ ተጠቁሟል፡፡

1. በከተሞች ውስጥና በከተሞች ዳርቻ ለጓሮ አትክልት፣ ለግጦሽ፣ ለደን ልማትና እና ለሌሎች ተመሳሳይ የግብርና ዓይነቶች  የሚለዩ ቦታዎች በወንዞች፣ በረግረግማ ቦታዎች፣ በጎርፍ መውረጃ እና በመሳሰሉት አካባቢዎች መሆን ይገባቸዋል
2. ሰፋፊ የከብቶች እርባታ ስፍራዎች ለስጋም ሆነ ለወተት በከተሞች ዳርቻ አካባቢ ሆኖ ወደ ከተማው ከሚነፍሰው የነፋስ አቅጣጫ በተቃራኒው መሆን ይኖርበታል
3. የንብ እርባታም ከከተማው የማስፋፊያ ክልል ውጪ መሆን አለበት
4. የዶሮ እርባታዎች በከተማው ክልል ውስጥ ከዋናው መንገድ ራቅ ባሉ ከአፈር ወለድ ብክለት፣ ከጩኸት ከጪስ እና ከአየር ብክለት በተጠበቁ ንፁህ ስፍራዎች መሆን ይኖርባቸዋል
5. የአብዛኛው  የከተማ ግብርና ስፍራዎች ሜዳማ ሆነው የተዳፋትነት መጠናቸው  1-10% በሆኑ ሥፍራዎች መሆን ይገባዋል (*MUDC,* 2012)፡፡ ነገር ግን የደን ልማት፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ልማት ሥራዎች ከዚህ የተዳፋትነት መጠን ባለፉ ሥፍራዎች ሊከናወን ይችላል፡፡

#### የከተማ ግብርና ክልል ሞዴሎች


የከተማ መሬትን በዞን መደልደል የከተማ መሬትን በአግባቡ ለማስተዳደር ከማስቻሉም ባሻገር በመሬት አጠቃቀሙ የከተማ ግብርና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት የተለያዩ ግብርና አይነቶች የት ፈቃድ ሊያገኙ ይገባል ወይም የትኞቹ ዱት ክልክል ሊሆኑ ይገባል የሚሉ ጉዳዮችን በማንሳት ግብርናው ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አይነቶች ጋር ተጣጥሞ የሚቀጥልበትን ሁኔታ በማረጋገጥ ዘላቂ የከተማ ልማት አቅጣጫን ይጠቁማል፡፡ በዚህ ረገድ በከተማ ውስጥ የከተማ ግብርናን በዘላቂነት ለማካሄድ በከተማ ፕላን ውስጥ ተስማሚ የግብርና ቦታዎችን የሚያሳዩ የተለያዩ ሞዴሎች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

**የአራቱ ዞን የከተማ ሞዴል**

የከተማ ግብርና በከተማ ክልል እና ዙሪያ መሬት ላይ በተለያዩ ቦታዎች ሊከናወን ይችላል። የከተማ ግብርና የትግበራ መረብ የአራቱ ዞን የከተማ ሞዴል የከተማ ግብርና ለሚካሔድባቸው ቦታዎች ከታች በምስል አንድ እንደተመለከተው በአራት ዞን ከፍሎአቸዋል። እነዚህም ዞኖች ፡

1. ማዕከላዊ ዞን (core zone)፣
2. ኮሪደር ዞን (corridor zone)፣
3. በማዕከላዊ እና በከተማው ዳርቻ ዞኖች መካከል የሚገኝ ዞን (wedge zone)፣ እና
4. ዳርቻ ዞን (periphery zone) ናቸው።

**ምስል. 1 የአራቱ ዞን የከተማ ሞዴል**




**ምንጭ** ፡ Smit et al. (1996),

ማዕከላዊ ዞን ኮሪደር ዞንን አስከትሎ ከፍተኛ የህዝብ ክምችት እና ብዙ የመሬት አጠቃቀም ውህደት የሚታይበት ዞን ነው። ስለዚህ የየዞኖች ተፈጥሮ እና ባህሪ በሥፍራው ሊካሔድ የሚገባችውን የከተማ ግብርና ዓይነቶች ይወስነዋል። እንደ Smit et al. (1996) አገላለፅ ማዕከላዊ ዞን ባለው ከፍተኛ የሰዎችና የቤቶች ክምችት ምክንያት የከተማ ግብርና ብዙ ጊዜ የሚከሄደው በቤቶች ጣሪያ፣ ለጊዜው ክፍት በሆኑ ባዶ

ቦታዎች፣ በቤት በረንዳ እና በህዝብ ፓርኮች ሲሆን አልፎ አልፎም በላስቲክ በተሸፈኑ አረንጓዴ ቤቶች (greenhouse) ይካሔዳል፡፡

ምንም እንኳን የኮሪዶር ዞን እንደ ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ የህዝብና የቤቶች ክምችት ባይኖርበትም ተግባራዊ የሚሆኑት የግብርና አይነቶች ከማዕከላዊ ዞን ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ በኮሪደር ዞን የከተማ ግብርና የሚካሔደው በአብዛኛው በመንገድ እና በባቡር ሀዲድ ዳርቻዎች ነው፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ መስመር ዳርቻዎች ግንባታ ያልተካሔደባቸው ብዙ ቦታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው (Smit et al. 1996)፡፡ በኮሪዶር ዞን ለውበት የሚሆኑ እፅዋት፣ አነስተኛ የእንስሳት እርባታዎች፣ የጓሮ አትክልት እና የዶሮ እርባታዎች ሊካሔድ ይችላል፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ የሚካሔዱ የግብርና አይነቶች በአብዛኛው በመጠን አነስተኛ ሆነው ዝቅተኛ የቆሻሻ ልቀት ያላቸው እና አነስተኛ ጥቅምም የሚሰጡ ናቸው፡፡ የዚህ ዞን ግብርና ተግባራዊ እየሆነ ባለበት መሬት ላይ የረዥም ጊዜ እቅድ አይኖርም (Beatley, 2000)፡፡

በማዕከላዊ እና በከተማው ዳርቻ ዞኖች መካከል የሚገኝ ዞን (wedge zone) በጥቅሉ አብዛኛው የመሬት ክፍሉ ለሌሎች የከተማ ልማት አይነቶች አመቺ ያልሆኑ የከተማ መሬት ያለበት ለምሳሌ ተዳፋት መሬቶች፣ የወንዝ ዳርቻዎች እና የመሳሰሉትን የሚገኝበት ነው (Smit et al. 1996)፡፡ በትልልቅ ከተሞች ለግብርናው አገልግሎት የሚውሉ መሬቶች የዚህ ዞን መሬቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የወተት ላም እርባታ፣ የዶሮ እርባታ፣ በአነስተኛ ግድቦች የአሳ እርባታ እና የመሳሰሉ የግብርና አይነቶች በዚህ ዞን ይካሔዳሉ፡፡ በማዕከላዊ እና በከተማው ዳርቻ ዞኖች መካከል የሚገኝ ዞን (wedge zone) ለከተማ ግብርና አገልግሎት እንዲውል ማድርግ በከፍተኛ ሁኔታ የአካባቢ ጥበቃ ዓላማን ለማሳካት ያስችላል (CFSC, 2003)፡፡

ምስል. 2 የከተማ ግብርና ጥቅም



**ምንጭ፦** Smit et al. (1996),

የመጨረሻው ዞን ከከተማ ዳርቻ ዞን periphery zone ሲሆን ይህም ዞን በአብዛኛው በከተማው ዳርቻ ያለውን የመሬት ክፍል የያዘ ሲሆን በዚህ ዞን ውስጥ ከገጠር አካባቢ ይልቅ ዞኑ ካለው የገበያ ቅርበት የተነሳ በርካታ የግብርና አይነቶች የሚታዩበት ዞን ነው:: በዚህ ዞን ውስጥ በጣም ሰፋፊ የጓሮ አትክልቶች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የዶሮ፣ የከብት፣ እና የንብ እርባታዎች ይካሔዱበታል::

## የህዝብና የቤት ክምችት በሚገኙባቸው ክልሎች ተስማሚ የሆነው የከተማ ግብርና

ከላይ እንደተገለፀው እንደ ዞኑ አይነት የዞኖች የህዝብና የቤቶች ክምችት ደረጃ የሚለያይ በመሆኑ የግብርናውም አይነት እንደ ዞኑ ሁኔታ ይለያያል:: ማዕከላዊ እና ኮሪደር ዞኖች ከፍተኛ የህዝብና የቤቶች ክምችት ያሉባቸው በመሆኑ ለግብርናው የሚሆን ትርፍ መሬት እምብዛም የላቸውም (Smit et al., 1996):: ትርፍ መሬት ቢኖር እንኳ ለግብርናው አገልግሎት የሚሰጠው በጊዜያዊነት ነው:: ስለዚህ ለግብርናው ብዙ ትርፍ መሬት ሊኖር የሚችለው ዳርቻ ዞን (periphry zone) እና በማዕከላዊ እና በከተማው ዳርቻ ዞኖች መካከል በሚገኝ ዞን (wedge zone) ውስጥ ነው:: በነዚህ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ለግንባታ አመቺ ያልሆኑ ለከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በስፋት ይመደባሉ:: ዝቅተኛ የህዝብ ክምችት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ለከተማ ግብርና የሚመደቡ መሬቶች የወንዝ

ዳርቻዎችና የጎርፍ መውረጃዎች፣ የሃይቅ ዳርቻዎች እና ተዳፋትነት ያላቸው መሬቶች ናቸው። ለተዳፋት ቦታዎች ተስማሚ የሚሆነው የከተማ ግብርና አይነት የአፈሩን መሸርሸር እና ሙቀትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የደን እና የአትክልትና ፍራፍሬ ዛፎች ልማት ናቸው (Beatley, 2000)። እንደዚሁም የውሃማ ዳርቻዎች ለም አፈር የሚገኝባቸው ቦታዎች በመሆናቸው ለጓሮ አታክልት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለውሃ ውስጥ እፅዋት፣ ለአሳ እርባታ እና ለመሳሰሉት የከተማ ግብርና አይነቶቸ ይውላሉ። እንደነዚህ ያሉት የግብርና አይነተችም የውሃ ብክለትን በመቀነስ የተፈጥሮ አካባቢን በማከም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ (Smit et al., 1996)።

**ምስል. 3 የችካጎ ከተማ አዳራሽ አረንጓዴ ጣሪያ**



**ምንጭ:** Bunnell, Gene. 2002.


ከፍተኛ የህዝብ እና የቤቶች መጨናነቅ በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚካሄደው የከተማ ግብርና ዓይነት የጓሮ፣ የግድግዳ እና የጣራ ላይ ግብርና እንደዚሁም የመንገድ ዳርቻ የግብርና አይነቶች ናቸው (Smit et al., 1996)። የጣሪያ እና የግድግዳ ላይ ግብርናዎች ለቤቶች እና ለአካባቢዎች ውበትን በመሆን የአካባቢው ሙቀት በማስተካከል የከተሞችን አካባቢ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጥቅም አላቸው።

## የቮን ቱነን ሞዴል

የቮን ቱነን ንድፈ ሀሳብ ወይም ሞዴል በከተማ ውስጥ እና የከተማ አካባቢ መሬትን አዋጪ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል አቅጣጫን ያሳያል። የቮን ቱነን ሞዴል በቦታ ላይ የኢኮኖሚውን

ወይም የግብርናውን አይነት ከከተማው ማዕከል በመነሳት የተለያዩ የግብርና አዝርዕቶች ከማዕከል ካላቸው ቅርበትና ርቀት አንጻር መጣጣማቸውን ይወስናል:: ሞዴሉ ከምርት ቦታ እስከ ገበያ ማዕከል ድረስ ያሉትን ሶስት ወሳኝ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው:: እነሱም የኑሮ ደረጃን፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎችን (added value ) ነው::

**ምስል.** 4 Von Thünen model




**ምንጭ ፦ Paul DE GRAAF Ir and Jan-Willem VAN DER SCHANS PhD**

በዚህ ሞዴል የተመለከቱት ቁጥሮች ቱነን ከተማንና የከተማውን ዙሪያ ለማሳየት የተጠቀመ ሲሆን በቁጥሩ ለተወከሉ ክልሎችን እንደሚከተለው ያስረዳል::

1. አንድ ቁጥር የከተማው እምብርት ሲሆን በዚህ አካባቢ ትኩስ ምርቶች ለምሳሌ የጓሮ አታክልትና የወተት ምርትን ይፈቅዳል
2. የሁለት ቁጥር ክልል የከተማው ዙሪያ ሲሆን በዚህም አካባቢ ለማገዶ የሚሆኑ የደን ዛፎችን ይፈቅዳል
3. የሶስት ቁጥር ክልል ለትራንስፖርት አመቺ የሆኑትን የሰፋፊ የአዝርዕት ልማት ክልል ነው ይላል
4. በመጨረሻም በአራት ቁጥር ክልል ላይ በእግራቸው ተጉዘው ወደ ገበያ ሊመጡ የሚችሉ የእንስሳት እርባታ ሥፍራ ቢሆን አዋጪ ነው ይላል::

ምንም እንኳ በከተሞች የእድገት ጅማሮ ላይ ከላይ የተገለፀው ሞዴል በከተሞች ውስጥ እና በከተሞ ዙሪያ ላሉት የግብርና እንቅሳቃሴዎች ገላጭ ቢሆንም ከላይ ያየናቸው ጉዳዮች ፈጣን በሆነው የትራንስፖርት ቴክኒዮሎጂ እና በኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ምክንያት የዚህ ሞዴል ተጽዕኖ ባደጉ አገሮች የቀነሰ ይመስላል::

## 2.1.5. የከተማ ግብርና ቅድመ ሁኔታ፣ ጥቅሞች፣ አሉታዊ ተፅዕኖዎችና እና ማነቆዎች

### 2.1.4.1. ቅድመ ሁኔታ

በአንድ አካባቢ የከተማ ግብርናን ለመተግበር በአካባቢው የሚገኙ ለሥራው የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላት ወሳኝ ሲሆን የሚከተሉት ለዘርፉ እንቅስቃሴ ዋና ዋና ቅድመ ሁኔታዎች ተብለው የሚገመቱ ናቸው።

1. የተፈጥሮ ሐብት፦ በአካባቢው የሚገኘው የአፈር ዓይነትና እና የአየር ፀባይ (የዝናብና የሙቀት መጠን) ተስማሚነት ለከተማ ግብርና ወሳኞች ናቸው። ለምሳሌ በካይሮ የሚታየው ዝቅተኛ የዝናብ መጠን በከተማው የጓሮ አትክልትን ለማልማት እንቅፋት ቢሆንም ለከብት እርባታ ግን እድልን ይሰጣል (Drescher, 2000)። ተስማሚ የአየር ፀባይ፣ለም አፈር እና ዝቅተኛ የተፈጥሮ አደጋ (ድርቅ፣ ጎርፍ፣ በረዶ የመሳሰሉት) መኖር በአንድ አካባቢ የከተማ ግብርናን ለማካሄድ እና ለህብረተሰቡ ተጠቃሚነት አመቺ ሁኔታዎችን ከሚፈጥሩ ነገሮች ዋናዋና ናቸው።
2. የመሠረተ ልማትና የአገልግሎት መሟላት፦ መሠረተ ልማት እና የአገልግሎት ዘርፎች መሟላት ለከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዳንዶች ሲሆኑ እነዚህም የግብአት መሟላት፣የብድር አገልግሎት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መሟላት ሆነው በዋናነት ግን የውሃና የመሬት አቅርቦት ወሳኙን ቦታ ይይዛሉ (Jacobi et al; 2000: 10)። በሌላ በኩል የመሠረተልማት መሟላት ከውሀ አቅርቦት ጋር ተዳምሮ የዝናብ እጥረት ችግርን የሚቀርፉ በመሆናቸው በከተማ ውስጥ ለግብርናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው ተብሎ ይታመናል (Drescher; 1998: 9)። ይሁንና የከተማ ግብርና በመሠረተ ልማት አቅርቦት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ዘርፉ አቅርቦቱ ባላቸው በጥቂቶች ብቻ ሊያዝ ይችላል የሚል ስጋት አለ። ስለዚህ የከተማ ግብርና ይበልጥ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችለው የከተማ ውስጥ ቆሻሻ ውሃን ለዚህ ሥራ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው ብለው አጥኚዎች ያሳስባሉ (Furedy et al. 1997; IDRC 1999; Kiango & Amend 1999 in Drescher et al; 1998: 10).
3. ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች፦ የአካባቢው አባወራዎች እና እማዎራዎች የግብርና ባህልና የምግብ አጠቃቀም ምርጫ ለከተማ ግብርና እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ አላቸው ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ በዕድገታቸው ግብርናን ባህላቸው አድርገው ያደጉ አባወራዎች በከተማ ኑሮአቸው በቶሎ ግብርናን ይጀምራሉ። በሌላ በኩል ገበያ ላይ የማይገኙ የግብርና ውጤት ተጠቃሚ የሆኑ

ቤተሰቦች ምግቡን ለማግኘት በራሳቸው ጓሮ ሲያለሙ ይታያሉ:: በተጨማሪም በከተማ ውስጥ የሚደራጁ ማህበራት በዘርፉ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ አላቸው ተብሎ ይታመናል::

4. የኢኮኖሚ ጉዳዮች፦ ለከተማ ግብርና ወሳኝ ናቸው የሚባሉ የኢኮኖሚ ጉዳዮች በከተማ ውስጥ የተከማቸ የሥራ ጉልበት ሥራ ማጣት፣ የገቢ ምንጭ እጦት እና የግብርና ምርት ውጤቶች ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ናቸው:: በተለይም ደግሞ በከተማ ውስጥ የተንሰራፋው የስራ አጥ ቁጥር መጨመር ሰዎችን ወደ ግብርና ሥራ እንዲገቡ ከሚያስገድዱ ነገሮች አንዱ ነው::

የከተማ ገጠር መንገድ ዝርጋታ ውስንነት እና ከፍተኛ የትራንስፖርት ዋጋ መጨመር በቀላሉ የሚበላሹ የግብርና ምርት ውጤቶች ለምሳሌ የጓሮ አትክልት፣ ወተትና የወተት ምርት ውጤቶች፣ ቅጠላ ቅጠሎች እና የመሳሰሉት በከተማ ውስጥ እንዲመረቱ በር ይከፍታል::

ሌላው መሰረታዊ የሆነ የኢኮኖሚ ጉዳይ የግብአት፣ የብድር አቅርቦት መሟላት እና የቁጠባ ባህል ማደግ ናቸው:: ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ምቹ ገበያን መፍጠር ሌላው መሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ነው::

#### 2.1.4.2. የከተማ ግብርና ጥቅሞች

የከተማ ግብርና ጥቅሞች እርስ በርስ ቁርኝት ባላቸው በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በአካባቢያዊ ተፅዕኖ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ሊታይ የሚችል ቢሆንም የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እነዚህን ከላይ የተገለፁትን ዋና ዋና ሃሳቦች ባጠቃለለ መልኩ ዘርፉ የሚሰጠውን ጥቅም እንደሚከተለው ያብራራል::

**1.ለጤና እና ለምግብ ዋስትና፦**

የከተማ ግብርና ድሃውን የከተማ ህዝብ ከነቤተሰቡ የተመጣጠነ እና የተሟላ የምግብ አቅርቦት እንዲኖረው በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል:: እጅግ በጣም ውድ የሆኑ የምግብ አይነቶች ለምሳሌ ፍራፍሬዎች፣ የጓሮ አትክልቶች፣ ስጋና የመሳሰሉትን በምግባቸው ውስጥ በቤት ምርታቸው እንዲያካትቱ በማስቻል ቤተሰቡ የተመጣጠነ ምግብ በማግኘት በምግብ እጥረት ምክንያት ከሚከሰቱ ችግሮች እንዲጠበቁ ያደርጋቸዋል:: ከዚህ

በተጨማሪም የከተማው ነዋሪ ትኩስ ያልተበላሹ የግብርና ምርት ውጤቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል የከተማ ግብርና ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል።

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተገናኘ ስሚት እና ሌሎች የዘርፉ አጥኚዎች ርሀብና የምግብ እጥረትን በማስወገድ የከተማ ግብርና የከተማው ድሃ ህዝብ ጤነኛ፣ አምራች እና በሽታን የሚቋቋሙ ዜጎች እንዲሆኑ ያደርጋል በማለት ያብራራሉ። ከዚህ በተጨማሪም የከተማ ግብርና የአየርና የውሃ ብክለትንና በሽታ አምጪ ህዋሳትን በመቀነስ እና የአካባቢው ቆሻሻዎች ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ከተሞች ንፁህ እና ውብ እንዲሆኑ ያደርጋል (Smit et al, 1996: 160)።

የከተማ ግብርና ጥቅም በጥራትም በመጠንም ሊለካ የሚችል ሲሆን አንደኛ የምግብ አቅርቦት መጠንን ከፍ በማድረግና ርሀብን በመቀነስ በሌላ በኩል ደግሞ የምግብ ጥራትን በማሻሻል ዘርፉ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ቢሆንም የከተማ ግብርና ከምግብ ጥራት ጋር ያለውን ቁርኝት የተመለከቱ ጥናቶች በአፍሪካም ሆነ በሌሎች የታዳጊ አገሮች በጣም ጥቂቶች ናቸው (UNDP, 1996)። ይሁንና ዘርፉ በተለያዩ ትልልቅ ከተሞች የምግብን ዋስትና በማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት የተለያዩ ጥናቶች ያብራራሉ።

ከዚህ በተገናኘ ሁኔታ በከተሞች በተካሄደው ጥናት ከተሞች በስፋት በጓሮ አትክልት ምርት፣ በዶሮ እና በከብት እርባታ ራሳቸውን ችለው ህዝባቸውን እየመገቡ እንደሆነ ተረጋግጧል። ለምሳሌ ዳካር የሀገሪቱን 60% የጓሮ አትክልት ፍጆታ እና 65-70% የዶሮ እርባታ ፍጆታ ትሸፍናለች (Mbaye etal; in Klemsu; 2000: 104)። እንደዚሁም ደግሞ 90% የጓሮ አትክልት ፍጆታ በራሷ በከተማዋ እንደሚሸፈን ጥናቶች ያሳያሉ (CENCOSAD 1994 in Klemsu;2000)። በዳሬሰላም ከ90% በላይ የሚሆነው ቅጠላቅጠል የጓሮ አትክልት የሚመረተው በከተማ ውስጥ ባሉ ባዶ ቦታዎችና በቤቶች ጓሮ እንደሆነ ተመሳሳይ ጥናቶች ያመለክታሉ (Stevenson et al 1996 in Klemsu; 2000: 104)። በሌላ በኩል በሀራሬ በከተማ ግብርና ላይ የተሰማራውን ህዝብ ቤተሰብ ተዘውታሪ ምግብ የአራት ወራት ከዘርፉ እንደሚሸፍንላቸው አንድ ጥናት ያመለክታል (Mbiba B., 2000)።

**2.የከተማ ግብርና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች**

የከተማ ግብርና መሠረታዊ ጥቅሞች ከገቢ ምንጭነት፣ ከሥራ ምንጭነት፣ ከአነስተኛ የንግድ ተቋም ልማትና ከከተማ የምግብ አቅርቦት እና የከተማ ቦታ አጠቃቀም አንፃር ከሚኖራቸው ሚናዎች ሊታዩ ይችላሉ፡፡

**ሀ. የገቢ ምንጭ፣ የሥራ ምንጭ እና የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት**

የከተማ ግብርና ለሚሊዮኖች አነስተኛ የንግድ ተቋማት ተወዳዳሪና ተመራጭ የሆነ በከተማ ውስጥ እና በከተማ አካባቢ የሚተገበር የሥራ ዘርፍ ነው፡፡ እንደ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም አገላለፅ ዘርፉ አነስተኛ ክህሎትና ካፒታል ላላቸው እንዲሁም ሴቶች እና በእድሜ ለገፉ አዛውንት የከተማ ነዋሪዎች የገቢ ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል (UNDP; 1996: 168)፡፡ በጥሬ ገንዘብ መጠነኛ ገቢን ማግኘት መቻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ጉዳዮች መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ከሳሃራ በታች ባሉ አገሮች ከሚኖሩ የከተማ ነዋሪዎች በተለያዩ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው መደበኛ ደሞዝ ተከፍሎአቸው የሚተዳደሩ የሠራተኛው መጠን ከ10% በታች ነው (UNDP, 1996)፡፡ በመሆኑም ለከተማ ነዋሪዎች በትንሹም ቢሆን በትልቁ፣ በመደበኛም ሆነ በኢመደበኛ መንገድ በተለይም በታዳጊ አገሮች የከተማ ገበሬዎች ተፎካካሪና በቂ ገቢን ከዘርፉ እያገኙ የዘርፉ ተጠቃሚዎች በመሆን የመኖር ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ አስችሎአቸዋል፡፡

አሁን በዘመናችን በዘርፍ ላይ የተካሄዱ አብዛኛዎች ጥናቶች አጽንኦት ሰጥተው የሚገልጹት ኢንዱስትሪው ሥራን ለመጀመር ቀላል መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በትንሽ መሬት፣ በትንሽ ወጪ እና በትንሽ ክህሎት ሥራውን መጀመር የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ በሉሳካ በሌላ ተሰማርቶ ሥራን ለመምራት ዕድሉ ለሌላቸው ምንም ችሎታና አቅም ለሌላቸው ለሴቶች፣ ለአዛውንቶች እና ለህፃናት የከተማ ግብርና የሥራ ዕድልን በመፍጠር ከሌሎች መደበኛ ካልሆኑ የሥራ ዘርፎች ይልቅ ከፍተኛ ጥቅም በመስጠት ላይ ይገኛል (Sanyal, 1985 cited in UNDP, 1996: 172)፡፡ ምንም እንኳ በዚህ ደረጃ ከሥራው የሚገኘው ውጤት አነስተኛ ቢሆንም በዘርፉ የሚሠማሩ የሥራ ተቋማት ደረጃ በደረጃ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን በጥረት ማሳደግ እና ማስፋት እንደሚችሉ የሌሎች ከተሞች ተሞክሮ ያሳያል፡፡

## ለ. የምግብ አቅርቦትና ፍትሃዊ የመሬት አጠቃቀም

የከተማ ግብርና ለነዋሪው በግል እና በቡድን በቤተሰብ ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚሁም ምክንያቱ የከተማ ግብርና የከተማው ህዝብ መሠረታዊ የምግብ ፍላጎትን በተለይም በጓሮ አተክልት በማርካት የከተሞችን የኢኮኖሚ አቅም በማጠናከር የብሄራዊውን የኢኮኖሚ እድገት ይደግፋል (Smit; 1996: 163)፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለይም በትንሽ ገቢ ባላቸው ታዳጊ አገሮች የከተማ ግብርና ለከተማው ህዝብ አንዱ የምግብ አቅራቢ ሀይል ነው ብለው ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ግብርና በገጠር የማይመረቱትን ረዘም ባሉ ጉዞ ውስጥ በቀላሉ የሚበላሹ የግብርና ውጤቶችን በማንኛውም ወቅት የሚያቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለብሔራዊው ጠቀሜታ እንደ ገጠሩ ግብርና ሁሉ መሠረታዊ እንጂ እንደ ተጨማሪ የምግብ አቅራቢ ሆኖ የሚታይ መሆን የለበትም፡፡

በሌላ በኩል እንደ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እይታ የከተማ ግብርና አዋጪና የመሬት ተጠቃሚነትን ከሚያረጋግጡ ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ ድርጅቱ ይህንን ካለበት ምክንያቶች ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል (UNDP, 1996: 177-178)፡፡ የከተማ ግብርና

- ለጊዜው ነፃ ሆነው የተቀመጡ መሬቶችንና በከተማ ማስፋፊያ ዞኖች አካባቢ ያሉትን ባዶ መሬቶችን ጥቅም ላይ በማዋል የገቢ ምንጭ አፍላቂ በመሆኑ፣
- ጥቅም ላይ ያልዋሉ የውሃ አካላትን እና ተዳፋታማ ሥፍራዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የአፈሩን ለምነት መጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ፣
- በተለያዩ ተቋማት የተያዙ ለግንባታ ያልዋሉ መሬቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ፣
- ፓርኮችን፣ የስፖርት ሜዳዎችን፣ የዩኒቨርሲቲ ጊቢዎችን፣ የመንገድ ዳርቻዎችን፣ የወንዞች ዳርቻዎችን፣ ዘላቂ ማረፊያዎችን እና ሌሎች የከተማ አካባቢዎች ባዶ መሬቶችን በአግባቡ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር አጣጥሞ መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፣
- የከተማ ዳርቻዎችን ለዶሮ እርባታ፣ ለጓሮ አትክልትና ለመሳሰሉት በማዋል የከተማ መሬትን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፣
- አብዛኛው የከተማ ግብርና ትንሽ መሬትን እና ዕውቀትን የሚፈልግ ቢሆንም ነገር ግን ለብዙዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ፣ እና

- የከተማ ግብርና ለህዝብ አገልግሎት በሚውሉ ነገሮች ላይ የሚወጡ ወጪዎችን የሚቀንስ በመሆኑ ናቸው::

### 3. ለዘላቂ የከተሞች ዕድገት ያለው ጥቅም

የከተማ ግብርና የከተሞችን ቆሻሻ አያያዝ እና የሀብት አጠቃቀምን በአግባቡ እንዲመራ በማድረግ የአካባቢውን ደህንነት በማሻሻል ለከተሞች ዘላቂ ዕድገት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

### ሀ. የከተሞችን አካባቢ ደህንነት በማስጠበቅ

በዓለማችን በተለይም በታዳጊ አገሮች በከተሞች በሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ዕድገት እና ተገቢ ያልሆነ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የመሬት አጠቃቀም እየጎዱት ያለው የከተማውን የውስጥ የተፈጥሮ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያለውን ሥነ ምህዳር ጭምር ነው:: ከላይ የተገለፁት ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የአካባቢው ሙቀት መጨመር፣ የአፈር መሸርሸር፣ የዕፅዋት ዝርያ መመናመን፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ለምሳሌ ጎርፍና የመሳሰሉት መጨመርን ያስከትላሉ:: የከተማ ግብርና የሚጫወተው ሚና እነዚህን ትልልቅ የከተማ ችግሮች በማስወገድ ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን የተፈጥሮ ሚዛን እንዲጠበቅ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል::

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ዲልስትራ እና ሌሎችም የከተማ ግብርና በከተማ ፕላን ዝግጅት ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶ ከታቀደ በከተማ ውስጥ የሚተከሉ የአትክልት ዛፎች ለአካባቢው የአየር እርጥበትን በመጨመር፣ ሙቀትን በመቀነስ እና መልካም መአዛን በመስጠት በካይ ጋዞችን በመቀነስ፣ የፀሐይ ብርሀንን በመቀበል ጥላ በመፍጠር እና ጠንካራ የነፋስ ሃይልን በመገደብ ከተሞች ለኑሮ ተስማሚ አካባቢ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ በማለት በጥናታቸው አረጋግጠዋል (Deelstra, 2000: 22)::

### ለ. ለውጤታማ የከተማ መሬት አስተዳደር

ከተሞች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ህብረተሰብ አካባቢ ያሉት ባዶ ቦታዎች ለምሳሌ የመንገድ ዳርቻዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ ለልዩ ልዩ መሠረተ-ልማት የዋሉ መሬት ዳርቻዎች ብዙውን ጊዜ ቆሻሻማና አስቀያሚ ቦታዎች ናቸው:: ስለዚህ የከተማ ግብርና እነዚህን

ቦታዎች በማፅዳትና በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ፣ ለምግብ ምርት እና ለአረንጓዴ መሠረተ ልማት  መሬቶችን  ጥቅም ላይ በማዋል በዝቅተኛ ማዘጋጃ ቤት ወጪ የከተሞችን አካባቢዎች ውበት እንዲጠበቁ በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል (UNDP, 1996: 184)፡፡

### ሐ. ለከተሞች ቆሻሻ አያያዝ ያለው ጥቅም

በዚህ ዘመን አብዛኛው ትልልቅ ከተሞች የአየር እና የውሃ ብክለት አምጪ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በማስተዳደር በኩል ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው፡፡ ደረቅ ቆሻሻ እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎችን ማዘጋጀት ለከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑም የሰፊ ከተማ  የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በፍጥነት በቆሻሻ የሚሞሉ በመሆናቸው ማዘጋጃ ቤቶች ለሁሉም የከተማን ክልል ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ለመስጠት አቅም የላቸውም (UNDP, 1996: 186)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመንገድ ዳር የሚከማቹ ቆሻሻዎች የአየር ብክለትና የጤና ቀውስ በማስከተል ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደ ጃክ እና ሌሎች አመለካከት ለዘላቂ የከተሞች ደህንነት ለማስጠበቅ ከተሞች በቆሻሻ አያያዝ እና አጠቃቀም  ዙሪያ  የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ደረቅ ቆሻሻዎች ለእርሻ እና ለከብቶች መኖ እንዲሁም ቆሻሻ ውሃዎች ተጣርተው በመስኖ ወይም በቀጥታ ለፍራፍሬ ዛፍ ምርት እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል (Smit; 1996: 196)፡፡

### መ. ለተፈጥሮ ሐብት ጥበቃና ለአደጋ መከላከል ያለው ጥቅም

የከተማ ግብርና በምትክ የኃይል አቅርቦት አማራጭ በመሆኑ ለማገዶና ለተለያዩ ጉዳዮች በሚኖረው የደን መጨፍጨፍ ምክንያት በተፈጥሮ ደን ላይ ያለውን ጫና በመቀነስ በተፈጥሮ ሐብት ላይ የሚደርሰውን ውድመት በመከላከል ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ የከተማ ግብርና የከተማ ቦታዎችን እና የፍሳሽ ውሃዎች ያለብክነት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለቆጣቢ የመሬትና የውሃ ሀብት አጠቃቀም መሳሪያ ነው (Sachs and Silk; 1990 in UNDP; 1996: 189)፡፡

የከተማ ግብርና ለተፈጥሮ አደጋ የተጋለጡ የከተማ አካባቢዎች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እንዲቀንሱ በማድረግ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሳሌ ተራራማ አካባቢዎች እና የወንዝ ዳርቻዎች በማልማት በነፋስና በውሃ ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን መቀነስ ይቻላል፡፡

### 2.1.4.3. የከተማ ግብርና አሉታዊ ተፅዕኖዎች

የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በከተማ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን የጤና እና የንፅህና ችግር በከተማ አካባቢ ማስከተል የሚችል እምቅ ኃይል አለው፡፡ እንደ ጥናቶች አገላለፅ በከተማ የሚፈጠረው የጤና ችግር ከምርት ማሰባሰብ በፊት እና በግብይት ወቅት ከሚኖር የምርት ብክለት ጋር ሊገናኝ ይችላል፡፡

ከኢንዱስትሪዎች እና ከንግድ ማዕከላት የሚለቀቁ ብክለት አስከታይ ኬሚካሎች ግብርናው የሚጠቀማቸውን አፈሩን፣ ውሃውን እና አየሩን በመበከል ተፅዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ይህም ብክለት ደግሞ በራሱ በአምራቹ፣ በነጋዴው እና በተመጋቢው ላይ አደገኛ የጤና ችግር ያስከትላል፡፡ በሌላ በኩል ያልታከመን የቆሻሻ ውሃን ለመስኖ ሥራ ማዋል በሰዎች ጤና ላይ ለሚፈጠሩ በርካታ ችግሮች ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ከ90 እጅ በላይ ወደ ወንዞች፣ ወደ ሀይቆች እና ወደ አነስተኛ የውሃ ክፍሎች የሚለቀቁ ፍሳሾች በአደገኛ በሽታ አምጪ ባክቴሪያዎች የተመረዙ ናቸው (Nelson 1996, cited in Klemsu, 2000: 110)፡፡ በነዚህ  አገሮች ደግሞ አብዛኛው የመሥኖ ሥራዎች ተግባራዊ እየሆኑ ያሉት በብቸኝነት በተበከሉ ውሃዎች አማካኝነት ነው፡፡ ለምሳሌ በኬንያ ናይሮቢ አብዛኛው የከተማ ግብርና መደቦች ያሉት ከኢንዱስትሪና ከመኖሪያ ሰፈር በሚለቀቁ ቆሻሻዎች ምክንያት በእጅጉ በተበከለው በኬንያ ወንዝ ዳርቻ ላይ ነው (Foeken et al, 2000: 121)፡፡ በጋና አክራ ከተማ እንደዚሁ አብዛኛው የጓሮ አትክልት ሥፍራዎች የሚገኙት ከኢንዱስትሪና ከመኖሪያ ሰፈር በሚለቀቁ ቆሻሻዎች ምክንያት በጣም በተበከሉ ወንዞች ዳርቻዎች አካባቢ ነው (Klemsu; 2000: 111)፡፡ ስለዚህ ከምግብ ብክለት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በአክራ የሚመረቱ ቅጠሎቻቸው ሳይቀቀል በጥሬው ለምግብነት የሚውሉ የተክል አይነቶች በምግብ ብክለት ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በተበከሉ አፈሮች ላይ እና በኢንዱስትሪ አካባቢዎች የሚመረቱ የጓሮ አትክልቶች በብረት፣ በሳልፈር

ናይትሬት እና በመሳሰሉት የተበከሉ ይሆናሉ። እነዚህ አደገኛ የሆኑ ጋዞች ደግሞ በሰው ልጆች አዕምሮ ላይ፣ በጨጓራቸው ላይና በደም ዝውውራቸው በተለይም በህፃናት ላይ እያስከተሉ ያሉት ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው (Ibid)። እንደ ከለምሱ ጥናት በከተማ ግብርና ምርት ውጤቶች ላይ የብክለትን ውጤትን ከሚያስከትሉ መሠረታዊ ነገሮች አንዱና ዋናው ነገር የእነዚህ በካይ ጋዞች ከማልሚያ ቦታዎች ያለው ርቀትና ከምርቱ ጋር ያለው የቀረቤታ ቆይታ ይወስነዋል። በተጨማሪም የአትክልቱ ዓይነት ለመበከል ያለው ተፈጥሮአዊው ባህሪው ሌላው የብክልት ምክንያት ነው። በአጠቃላይ ረጅም ጊዜ የሚፈጁ ቅጠላቅጠል የጓሮ አትክልቶች ለብክለት በእጅጉ የተጋለጡ ናቸው (Ibid)። በሌላ በኩል ደግሞ የፍራፍሬ ዛፎች እና ሥራሥሮች ብክለትን በመቋቋም ከፍተኛ አቅም እንዳላቸው በአሜሪካን አገር በኒዮርክ የተደረገ ጥናት ያሳያል። ከዚህ ችግር ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንደዚህ አይነቱን ችግር ለማስወገድ የአፈሩን PH መጠበቅ በመሆኑ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ቅጠላቅጠል የጓሮ አትክልቶችን ከዋናው መንገዶች በ7.5 ሜትር ራቅ ተደርገው እንዲለሙ በማድረግ እና አፈሩ የPH መጠኑ እንዲጨምር ብስባሽ ነገሮችን አፈሩ ላይ መጨመር እንደሆነ ጥናቱ ያሳስባል።

በግብርና ሥራ ላይ የሚውሉ በመጠን ያለፈ የኬሚካል ርጭት ለምሳሌ ማዳበሪያ፣ ተባይ ማጥፊያ፣ በሽታ ማጥፊያ፣ እና የአረም ማጥፊያዎች የግብርናውን ምርት ውጤት ቢያሻሽሉም በአካባቢውና በሰዎች ጤና ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት በቀላል የሚገመት አይደለም። ስሚት እና ሌሎችም እንደሚያሳስቡት እነዚህ በካይ ኬሚካሎች የመተንፈሻ አካሎችን በመጉዳት፣ የእናት ጡት ወተትን በመበከል ብሎም መካንነትን በማስከተል ከፍተኛ ጉዳት ያመጣሉ (Smit et al; 1996: 200)። ከዚህ በተጨማሪም ወደ አየር የሚለቀቁ የግብርና ኬሚካሎች ከፍተኛ የህዝብ ክምችት ባሉባቸው ከተሞች የሚያስከትሉት ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው (UNDP; 1996: 199)።

#### 2.1.4.4. የከተማ ግብርና ማነቆዎች

የከተማ ግብርና ልማት ለኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ ኢንዱስትሪ ቢሆንም ዘርፉ በተለያዩ ማነቆዎችና በተዛባ አመለካከት የታጠረ ነው። እንደ ጃክ ስሚትና ሌሎች እይታ ዘርፉ ያለበት እነዚህ ማነቆዎች ቢወገዱለት ግብርናው በመቶ ሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ የከተማ

ነዋሪዎች አስተማማኝ የምግብ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል (Smit et al; 1996: 211)፡፡ እነዚሁ አጥኚዎች ግብርናው በተጨባጭ ያለበትን እጥረት የለዩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ የተዛባ ባህላዊና ማህበራዊ የአመለካከት ማነቆዎች፣ ተቋማዊ ማነቆዎች፣ የግብዓትና የአገልግሎት እጥረቶች፣ ከምርት በኋላ በተለይም ለምግብነት በማቀናጀት፣ በገበያ እና በአደረጃጀት ደረጃ የሚከሰቱ ማነቆዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በዚሁ ሥራ ላይ ጥናት ያደረገው ሞጎት በበኩሉ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች መንግስታት ለዘርፉ የሚሰጡት እውቅና ማነስ በተለያየ መንገድ ለግብርናው ማነቆ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ሞጎት እንደሚለው የእነዚህ አገሮች የግብርና፣ የምግብ፣ የጤና እና የአካባቢ ፖሊሲዎች በአብዛኛው የከተማ ግብርናውን ስለማያጠቃልሉ የከተማው ነዋሪ በግብርናው ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም አሳጥቶታል (Mougeot; 2000: 26)፡፡

በተለይም በታዳጊ አገሮች ዘርፉን ለማሳደግ የታቀዱ ይፋዊ የሆኑ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ባለመኖራቸው እና የከተማ ግብርና በከተማ ፕላን ዝግጅት ውስጥ የሚሰጠው ቦታ አለመኖሩ ከዋና ዋናዎቹ ማነቆዎቹ አንዱ ሲሆን ዘርፉ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ሴክቴር ራሱን ችሎ የማይንቀሳቀስ በመሆኑ የብድር፣ የምርምር፣ እና የልማት ተቋማት እንደዚሁም የገበያ ኤጄንቶች በአጠቃላይ ዘርፉን ለውድቀት የተጋለጠ አድርገው እንዲቆጥሩ አድርጓቸዋል (UNDP, 1996: 214)፡፡

በአብዛኛው የገጠርና የከተማ ገበሬዎች ተመሳሳይ ፍላጎትና የብድር አቅርቦት ችግር አሉባቸው፤ ይሁንና ጠንካራ የገንዘብ አቅም ያላቸው አበዳሪዎች የከተማ ግብርና እንደ አስፈላጊ ኢንዱስትሪ የማይቆጥሩት በመሆኑ የከተማ ገበሬዎች በብድር ዙሪያ ጠንከር ያለ ማነቆዎች አሉባቸው፡፡

በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የከተማ ግብርና ሌላው መሠረታዊ ማነቆዎች የመሬት እና ሌሎች ግብአቶች ለምሳሌ እንደ ማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣እና የማምረቻ ማሣሪያ አቅርቦት ችግሮች ናቸው (Drescher et al;1999:12)፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በተጨማሪም አንዳንድ ጥናቶች እንደሚገልፁት የከተማ ግብርና በባህሪው በገላጣ ሥፍራ ላይ የሚተገበር በመሆኑ በስርቆት ምክንያት የሚባክኑ የጓሮ አትክልቶች መኖርና እና የፖሊስም ጥበቃ አለመኖር የግብርናው አንደኛው ማነቆ ነው፡፡

### 2.1.4.4.የከተማ ግብርና ዘላቂነት

የከተማ ግብርና በከተሞች ዘላቂ ሆኖ እንደ ሴክተር የሚቀጥለው አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና በጤና ጉዳዮች የሚሰጠው ጥቅም ጠንካራ ሆኖ ሲዘልቅ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 1. በአንድ ከተማ የሚለማ የከተማ ግብርና ዘላቂነትን ሊያመላክቱ የሚችሉ አቅጣጫዎች**

| | አካባቢያዊ ሁኔታዎች | ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች | ማህበራዊ ሁኔታዎች | የጤና ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|
| **አበረታች ሁኔታዎች** | የከተማ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች የተክሎች ምግብ<br><br>በከተማ አረንጓዴነት የአካባቢው ጤና | የግብአትና የገበያ አቅርቦት<br><br>የሥራ ዕድልና ድህነት ቅነሳ | በባዶ ቦታዎች የህብረተሰቡን የአረንጓዴ መዝናኛ ፍላጎት ማሟላት | በወባ ትንኝ መዋለጃ ስፍራዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ<br><br>በአፈር አጠባበቅ የቆሻሻ አያያዝ |
| **የሚጋጩ ጉዳዮች** | የከተማ ብክለት በግብርና ምርት ውጤቶች<br><br>የአካባቢ ብክለት በግብርና ኬሚካል ልቀት<br><br>በግብርና ተክል ወለድ በሽታዎች ብክለት | ለከተማ መሬት ይዞታ ፉክክር | የህብረተሰቡ ለከተማ ግብርና ያለው አመለካከት | የበሽታዎች መከሰት<br><br>የከተማ ግብርና የሚያስከትላቸው የተፈጥሮ አደጋዎች ዙሪያ ያለው የመረጃ አናሳነት |

**ምንጭ**: *Axel W. Drescher quoting Van den Berg, 2002:565 with some modification*

### 2.2. የተሞክሮ ዳሰሳ

#### 2.2.1. ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮ ዳሰሳ

የከተማ ግብርና ከከተማ መሬት አጠቃቀም ጋር በማቀናጀት ዙሪያ ያሉትን ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 1. በጀርመን-በርሊን የከተማ መሬት ለከተማ ግብርና መመደብ

ድሬስኬር (2001) በጀርመን መሬትን ለግብርና ሥራ ስለመስጠት ዘግቦ ነበረ፡፡ ይህም ክስተት ወደ አፍሪካ በተለይም ከሳሃራ በታች ባሉ አገራት መዛመት የቻለ በተደራጀ ሁኔታ ይካሄድ የነበረ ትልቅ የግብርና ዘዴ ነው፡፡ ድሬስኬር እንደገለጸው የመጀመሪያው የድሆች የግብርና ሥራ ሲጀመር ወቅቱ የዛሬ ሁለት መቶ ዓመት ርሃብና ድርቅ በጀርመንና በሌሎች የአውሮፓ አገሮች በእጅጉ የተዛመተበት ወቅት ነበረ፡፡ ፈጣኑ የኢንዱስትሪ ልማት በፈጣን የከተማነትና ወደ ከተማ የሚደረግ ስደት ጋር ተዳምሮ በጀርመን በርካታ ቁጥር ያላቸውን ነዋሪዎችን የምግብ እጥረትን ጨምሮ ለከፋ ጎስቋላ ኑሮ ዳርጓቸው ነበረ፡፡ በወቅቱ ለዚህ ችግር አንደኛው የመንግስት ምላሽ የከተማ ግብርና ማስፋፋት ነበር፡፡

ድሬስኬር እንደተመለከተው የግብርና ማሳዎቹ በመጠን ከ200 እስከ 400 ካሬ ሜትር ያህል ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ጠንከር ያሉ የእርሻ መሳሪያዎችን መጠቀም የሚያስችሉ አልነበሩም፡፡ ይሁንና እነዚህ የእርሻ ማሳዎች የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር ግን በተለይም በክፉ ቀናት ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ ነበረ፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በርሊን ብቻዋን ወደ 200,000 የግብርና ማሳ ነበራት፡፡ ዛሬም እስከ 80,000 የሚደርሱ ማሳዎች አሉ፡፡ ለዚህ ውጤታማና ቋሚ የግብርና ማሳ መቋቋም መሰረቱ በጀርመን ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ የግብርና ማህበራት መደራጀት ነበረ፡፡

የከተሞች አስተዳደር እና ማዘጋጃ ቤቶች የመሬት፣ የውሀ እና የሌሎች (አጥር፣ ጥበቃ) አቅርቦቶችን በማቅረብ ዘርፉን ያግዙ ነበረ፡፡ በተጨማሪም የመሬት ግብር ክፍያቸው በጣም አነስተኛ ነበረ፡፡ በከተሞች የብስባሽ ማዳበሪያዎችን የመጠቀምና ሌሎች አዳዲስ የግብርና ዘዴዎች ማስፋፋት በከተሞች የሚታዩ ክስተቶች ነበሩ (*Magigi,Wakuru, 2008)*፡፡

## 2. ሲንጋፑር

በእጅጉ ዘመናዊ የሆነችው በደሴት ላይ የተገነባችው ከተማ ሲንጋፑር ሙሉ በሙሉ በስጋ ምርት በዓመት አንድን ሰው እስከ 140 ፓውንድ በመመገብ ራስዋን የቻለች ነች። ከተማዋ በጓሮ አትክልት 7,000 ሄክታር መሬት ላይ በማልማት 25 በመቶ ራስዋን የቻለች ነች። የሲንጋፑር ግብርና ሚኒስቴር ለ10,000 የከተማ ገበሬዎች ፈቃድ በመስጠት ህጋዊ እውቅናቸውን አረጋግጧል። በትርፍ ጊዜአቸውም በግብርና ላይ የተሰማሩ ሌሎች በርካታ ገበሬዎች አሉ (UNDP, 1996)።

## 3.ሲዲኒ-አውስትራሊያ

የኒው ሳውዝ ዌልስ (NSW) የግብርና ሚኒስቴር በቅርቡ ለምና ምርታማ የሆነው የመሬት ሃብት ለአካባቢውና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ጥቅም ያለው መሆኑን ገልፆ በሲዲኒ ስትራቴጂክ ፕላን ዘላቂ ግብርናን አካቷል። ከከተማ ግብርና የሚገኘው ጥቅም ለጠቅላላው ኢኮኖሚ ከ2 ቢሊዮን ዶላር እስከ 3 ቢሊዮን ዶላር የሚደግፍ ከመሆኑም በላይ የሲዲኒ ከተማ ግብርና ለከተማው ህዝብ ትኩስና ያልተበላሹ ምግቦች አቅራቢ ነው። ለምሳሌ የከተማው የእንጉዳይ 85 በመቶ፣ የቲማቲም 70 በመቶ እና የሸንኩርት 95 በመቶ ፍጆታ የሚሸፈነው በከተማው ምርት ነው። ይህ ፕላን ከሌሎች የመንግስት የኢኮኖሚ ዘርፎች (ከጤና፣ ከግብርና፣ ከአካባቢ ልማት፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከትምህርት እና ከመሳሰሉት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች) ጋር ያለውን ትብብር እና ቁርኝት ያጠናክራል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል (Ibid)።

## 4. ሻንጋይ - ቻይና

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ1950ዎቹ ጀምሮ የሻንጋይ ማዘጋጃ ቤት አስተዳደር የህዝቡን የምግብ ፍላጎት በተሟላ መልኩ ለማርካት በከተማ ውስጥ ምግብን የማምረት እቅድን በማዘጋጀት እየመራ ይገኛል። እስከ ቅርብ ጊዜም የከተማዋ የምግብ ምርት አቅርቦት ከህዝቡ ፍላጎት አንፃር በከፍተኛ ሁኔታ የሚበልጥ በመሆኑ እቅዱ በዓለማችን ውጤት ካመጡ ዕቅዶች አንዱ መሆን ችሏል። የመንግስት ዓላማ በከተማው ክልል ውስጥ በምግብ ራስን ማስቻል እና የትራንስፖርት፤ የጎተራ እና የኃይል ፍጆታን መቀነስ ነው። ለግብርናው ሥራ የከተማው ክልል የተከፋፈለው ለእርሻ፣ ለደን፣ ለዓሳ ልማት ወይም

ለከብት እርባታ ካላቸው አመቺነት ነው። የተቀናጀ የከተማ ምግብ ፖሊሲ እና የቴክኖሎጂ ምርምር እገዛ እና የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ያተኮረው በከተማው ፍላጎት ላይ ነው።

የከተማው አስተዳደር የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ (የሰዎችን እዳሪን ጨምሮ) አያያዝና አጠቃቀም (ለግብርናው ሥራ) እንዲውል ያደርጋል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የከተማው ህዝብ የጓሮ አትክልት ፍላጎት ሙሉ በሙሉ እየተሸፈነ ያለው በከተማው ምርት ነው። ከዚህ በተጨማሪም ግብርናው በከፍተኛ መጠን የጥራጥሬ፣ የዶሮ እና የዓሳ ፍላጎትንም እየሸፈነ ይገኛል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቻይና ውስጥ በተፈጠሩ በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ዕድገት ምክንያቶች የመሬት ይዞታ ማጣት ከህዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ጋር ተዳምረው ሻንጋይ እና ሌሎች የቻይና ከተሞች በምግብ ሰብል ራሳቸውን ከመቻል ይልቅ ከውጪ በሚገቡ የግብርና ምርት ውጤቶች ላይ ጥገኛ እየሆኑ መጥተዋል (Ibid)።

## 2.2.2. የአፍሪካ አገሮች ተሞክሮ

### ከሳሃራ በታች ያሉ አገራት ተሞክሮ

ከሳሃራ በታች ባሉ አገሮች የከተማ ግብርና በከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አስተዳደር ውስጥ በመሬት አቅርቦት ዙሪያ በርካታ ማነቆዎችና ችግሮች እየተጋፈጠ ይገኛል። እነዚህም ችግሮች የሚንፀባረቁት ዘርፉ የሚንቀሳቀስባቸውን አካባቢዎች በማመላከት፣ በመሬት አቅርቦት፣ በፖሊሲ አወሳሰን፣ በህግና በሌሎች አስተዳደራዊ አፈፃፀሞች ዙሪያ ነው። ይሁንና እነዚህ ተደማሪ ችግሮች ቢኖሩም ዘርፉ በአካባበው ከተሞች ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ መሆኑን በሚከተሉት አገሮች የተጠኑ ጥናቶች ያሳያሉ **(Wakuru, 2008)**።

### 1.ካምፓላ-ኡጋንዳ

#### መሬትን ለከተማ ግበሬ ተደራሽ ማድረግ

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ1970 የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጀምሮ የካምፓላ ከተማ ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቤተሰብ ለአማራጭ የምግብ ምንጭነት፣ የምግብ ወጪን በመቀነስ ለቁጠባ እና ለገቢ ምንጭነት ፊቱን ወደ ግብርና አዙሮ ይገኛል። ከከተማው ህዝብ ወደ 1.5 ሚሊዮን ማለትም የጠቅላላው 40 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የእንስሳት ወይም የእፅዋት ተዋጽኦ ምግቡ

እንደዚሁም 70 በመቶ የዶሮ ምርት ውጤት ምግቡ የሚሸፈነው በከተማው ምርት ውጤት ነበረ (*World Bank, 2008*):: በካምፓላ የከተማ ግብርና የሚተገበረው በተለይ አብዛኛው ድሃው በሚኖርበት እና የደከሙ ቤቶች በሚታዩበት በሸለቆ ውስጥ ነው:: ምንም እንኳ በካምፓላ ዘርፉ በገበያ እና በልዩ ልዩ አገልግሎት አቅርቦት ጥቅም እየሰጠ ቢሆንም ለእንስሳት እርባታ እና ለጓሮ አታክልት ልማት መሬት ማግኘት ለከተማው ድሃ በጣም አስቸጋሪ ነው::

የካምፓላ ድሆች እንዴት መሬት እንደሚያገኙ ለማወቅ በተደረገ ጥናት ድሆቹ በተለያዬ መንገድ ለመሬት ተደራሽ እንሚሆኑ ያረጋግጣል (*World Bank, 2008*):: እነሱም ወረራ (46 በመቶ)፣ ውሰት (34 በመቶ)፣ ውርስ (11 በመቶ)፣ ከግለሰብ ኪራይ (5 በመቶ)፣ የቤተሰብ ይዞታ (4 በመቶ) ናቸው:: በአሁኑ ሰዓትም አብዛኛው የካምፓላ ገበሬ (60 በመቶ የሚሆነው) በከፍተኛ ሁኔታ የእርሻ መሬት ፍለጋ ላይ ይገኛል:: እነዚህም ገበሬዎች ከመንግስት በሊዝ፣ ከቤተሰብ በውሰት ወይም ደግሞ ፈንድ በማፈላለግ በግዢ መሬትን ለማግኘት እንዳሰቡ ይናገራሉ ( *Van Veenhuizen,(2006: 53-86)*::

## 2. ዳሬሰላም-ታንዛኒያ

### የከተማ ግብርናን በከተማ መዋቅራዊ ፕላን ዝገጅት ውስጥ ማካተት

በዳሬሳላም የከተማ ግብርና በቤቶች ጓሮ የሚካሄድ ምርትን፣የእንስሳ እርባታን፣ የህብረት እርሻን፣ በከተማ ባዶ ቦታ ላይ የሚካሄድ ግብርና እና በከተማ ዳርቻ ላይ የሚካሄድ ግብርናን ያጠቃልላል (Jacobi et al., 2000 and Dongus, 2000):: በዳሬሰላም በከተማ ግብርና ላይ ከተሰማሩት አብዛኛዎቹ በጓሮ ምርት ላይ የተሰማሩ ሴቶች (Dongus, Ibid) የከተማ ባዶ ቦታ እና የመንገድ ዳርቻዎችን የሚያለሙ ወጣቶችና ወንዶች ናቸው (Mlozi et al, 1992; Kyessi, 1997 and Sawio, 1998):: ይሁንና በከተማው እያደገ የመጣው የግብርና እንቅስቃሴ በርካታ የፖሊሲ ለውጦችን፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ለህብረተሰቡ ሁለንተናዊ እድገት እንዲውሉ የማድረግ አስፈላጊነትን አነቃቅቷል:: ይህም ለዘላቂ የከተማ ልማት በከተማው ሀብት ላይ ያለውን ጫና እና ግጭት የሚቀንስ አዲስ የስትራቴጂ ቀረፃ እንዲኖር አስገድዷል::

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1992 ዓ ም የዳሬሰላም ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ፕላን እና አስተዳደር (EPM) አዲስ አቅጣጫ ቀይሷል፡፡ አዲሱ አቅጣጫ የከተማ ግብርናን ጨምሮ ለብዙ ጉዳዮች ለውጥ እንደ ሞተር ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በዚህ አዲስ አቅጣጫ እ.አ.አ. በ1993 ዓም የከተማው አስተዳደር ለግብርናው ትኩረት ለመስጠት በንኡስ አስተዳደር ደረጃ አዳዲስ ሃሳቦችን ተለዋውጧል፡፡ በዚህ የሃሳብ ልውውጥ የባለድርሻ አካላት የከተማው ግብርና ለከተማው ህዝብ 30% ያህሉን የምግብ አቅራቢ በመሆኑ ዘርፉ በከተማው የሥራ ዓይነቶች ስትራቴጂ ውስጥ እንዲታቀፍ ተስማምቷል፡፡ በከተማው የከተማ ግብርና አንዱ አጀንዳ እንዲሆን የሚያስችል የግብርና ስትራቴጂ የሚቀርፅ የግብርና ሥራ ማህበር ተቋቁሞ ነበር፡፡ ይህም ማህበር ለከተማው ግብርና ስትራቴጂካዊ ፕላን ሲቀርፅ አሳታፊ የሆነ መንገድን ተጠቅሟል፡፡

የዚህ ሁሉ ሂደት ውጤት ከአክሽን ፕላን ዝግጅት ጀምሮ ግብርናው በከተማ መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ እስኪጣመር ድረስ ያለው ሂደት በጣም ጥሩ ነበር፡፡ የዚሁ ቡድን የጥናት ውጤትም ግብርናው የትና በምን ያህል ደረጃ በሚሉ ጉዳዮች በከተማ ልማት ስትራቴጂክ ፕላን ውስጥ ለመወሰንም መሠረቶች ሆነዋል፡፡ በዚህ ፕላንም ለግብርና የሚውሉ የከተማ መሬት በዞን ክፍፍል ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ የከተማውንም ህግና መመሪያም የማሻሻልም ሃሳብ ተቀባይነትን አግኝቶ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የከተማ ልማት ስትራቴጂክ ፕላኑ ለግብርናው በዞን ክፍፍል ውስጥ በመደበኛነት መሬት የሰጠ ከመሆኑም ባሻገር ወደፊት ለሌሎች የልማት ዕቅዶች የተያዙትን ባዶ የከተማ መሬቶች ሁሉ በጊዚያዊነት ለግብርና ልማት እንዲውሉ ፈቅዷል፡፡ በዕቅዱም ግብርናው ለዜጎች እንደ ዋናው የሥራ ዘርፍ በመሆን እንዲያገለግል እውቅና ሰጥቷል፡፡ በሌሎችም ህጎች ለምሳሌ በግብርና እና በከብት እርባታ ፖሊሲ (1997)፣ በብሄራዊ የከተማ ልማት ፖሊሲ (Jan 2000) እና በሌሎችም የከተማ ግብርናው እውቅና ተንፀባርቋል (Wakuru, 2008)፡፡

### 2.2.3.የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶች

በከተማ ግብርና ዙሪያ ከዓላም አቀፍና ከተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ተሞክሮዎች የሚከተሉት ጠቃሚ ትምህርቶችን ልንማር እንችላለን፡፡

- ✓ አንዳንድ ከተሞች የከተማ መሬትን ለከተማ ግብርና በመመደባቸው በከተማ ውስጥ የተንሰራፋውን የምግብ እጥረትንና የዜጎችን የከፋ ጎስቋላ ኑሮ ማሻሻል መቻላቸው፤
- ✓ በተለያዩ ከተሞች የከተማ ግብርና በከተማ መዋቅራዊ ፕላን ዝግጅት ውስጥ በማካተታቸው በርካታ የፖሊሲ ለውጦችን፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ለህብረተሰቡ ሁለንተናዊ እድገት እንዲውሉ የማድረግ አስፈላጊነትን አነቃቅቷል፤
- ✓ የከተማው ግብርና ዘርፍ በከተሞች አስተዳደር እና ማዘጋጃ ቤቶች በመሬት፣ በውሃ እና በሌሎች (አጥር፣ ጥበቃ) አቅርቦቶች የሚታገዝ መሆኑ፤
- ✓ የዘርፉ ባለሞያዎች እና የከተማው አስተዳደር የብስባሽ ማዳበሪያዎችን የመጠቀምና ሌሎች አዳዲስ የግብርና ዘዴዎች በማስፋፋት ዘርፉን የሚያግዙ መሆናቸው፤
- ✓ አንዳንድ ከተሞች ለከተማ ገበሬዎች ፈቃድ በመስጠት ህጋዊ እውቅናቸውን በማረጋገጥ ዘርፉን የሚያግዙ መሆናቸው፤
- ✓ በከተሞች የሚገኘው ለምና ምርታማ የሆነው የመሬት ሃብት ለአካባቢውና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ጥቅም ያለው በመሆኑ ይህንኑ ሃብት ለመጠቀም በአንዳንድ ከተሞች የዘላቂ ከተማ ግብርናን በስትራቴጂክ ፕላን ውስጥ ማካተታቸው እና ይህ ፕላን ከሌሎች የመንግስት የኢኮኖሚ ዘርፎች (ከጤና፣ ከግብርና፣ ከአካባቢ ልማት፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከትምህርት እና ከመሳሰሉት) የመንግስት ሴክተሮች ጋር መቀናጀት ያለበት መሆኑ
- ✓ የከተማው ክልል ለግብርናው ሥራ የተከፋፈለው ለየተግባራቱ ካላቸው አመቺነት መሆኑ፤
- ✓ የተቀናጀ የከተማ ምግብ ፖሊሲ እና የቴክኖሎጂ ምርምር እገዛ እና የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ያተኮረው በከተማው ፍላጎት ላይ መሆኑ፤
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የከተማ መሬት አቅርቦት ከመንግስት በሊዝ መሆኑ እና የመሳሰሉት ከላይ በተለያዩ ከተሞች ከተዳሰሱ ተሞክሮዎች የተገኙ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ናቸው።

# ክፍል ሶስት

## 3.የከተማ ግብርና ከከተማ ፕላን አንፃር

የከተማ ፕላን አዘጋጆች፣ የከተማ ፕላን ፖሊሲዎች፣ እና ሌሎችም የፕላን ዝግጅት አካሎች በከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ እንደሆነ በርካታ አጥኚዎች በጥናታቸው አረጋግጠዋል:: የከተማ ገበሬዎች ለሚያጋጥማቸው ለእንደነዚህ ላሉ ችግሮች “የፕላን ሪፎርም ”እንደ መፍትሄ ሃሳብ እየተነሳ ይገኛል (ለምሳሌ፣ Binns and Lynch 1998)፡፡

ይሁንና እንዲህ አይነቱ አስተያየት ግልፅ ያልሆነና የሚነሳውም የከተማ ፕላን አዘጋጆች የህብረተሰብ ለውጥ ለማምጣት ያላቸውን ሚና በተመለከተ ከተሳሳተ ግንዛቤ ነው:: ስለዚህ ስለ ፕላን ሪፎርም በፕላን ፖሊሲ ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ከማንሳት ይልቅ የከተማ ፕላን ምንድነው፣ የከተማ ፕላን አዘጋጆች ምንድው የሚሰሩት፣ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ለከተማ ፕላን አዘጋጆች አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ምንድናቸው እና የከተማ ፕላን ዝግጅት ግብን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ስትራቴጂዎችና መሳሪያዎች ምንድናቸው የሚሉት ጉዳዮችን አንስቶ መወያየት የከተማ ግብርናን በከተማ ፕላን ውስጥ ለማካተት ለሚኖር ውሳኔ ጠቃሚ ነው::

### 3.1. የከተማ ፕላን ምንድነው?

የከተማ ፕላን የከተማ ራዕይን ለማሳካት እና በከተማዋ የሚታዩ መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት በመንግስት የአስተዳደር ሂደት ውስጥ ወደፊት ሊሰሩ የሚገቡ ነገሮችን ቅርፅና የተሻለ የአተገባበር ሂደትን መምረጥ ማለት ነው (Bartone et al. 1994, Smith 1993, Hodge 1991)፡፡ የከተማ ፕላን የህዝብን ሃብት (ለምሳሌ መሬትን) ለመጠበቅና ለማከፋፈል እንደዚሁም ከሃብቱ የሚገኙ ጥቅሞችን በፍትሃዊነትና በአግባቡ ለማከፋፈል የሚረዳ መሳሪያ ነው (Taylor and Williams, 1982)፡፡

### 3.2.የከተማ ፕላን በታዳጊ አገሮች

በታዳጊ አገሮች ያሉ ትልልቅ ከተሞች በከተማ ፕላን በተለይም በከተማ መሬት አጠቃቀም እና በመሳሰሉት አፈፃፀሞች ተጠቃሚዎች ናቸው (Menezes, 1983)፡፡ ይሁንና ግለሰቦች ለከተማ መሬት አስተዳደር ባላቸው በተሳሳተ አረዳድ የከተሞችን ፕላን ዝግጅትን ሊቃወሙት ይችላሉ (Taylor and Williams, 1982)፡፡ በታዳጊ አገሮች ትልልቅ ከተሞች ህገወጥ የመሬት ንግድ ዘላቂነት የሌለው የመሬት አጠቃቀምን በመፍጠር ለፕላን አዘጋጆችና ለፖሊሲ አዘጋጆች ፈተና በመሆን ትልቅ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡

የከተማ ፕላን አዘጋጆች ካለባቸው በርካታ ችግሮች የፕላን ዝግጅቱ ከነችግሩ የአውሮፓዊያን ባህል ነፀብራቅ ሆኖ በቅኝ ገዢዎች የመጣ በመሆኑ እንደገናም በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ በማስተር ፕላን ግፊት የመጣ መሆኑ አንዱ ሲሆን (Khosla 1993, Kironde 1992,Taylor and Williams 1982)፣ ሌላው ችግር የከተማ ፕላን በታዳጊ አገሮች የፖለቲካ ለውጥ ሲኖር ከለውጡ ጋር አብሮ የግድ መለወጥ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ በአብዛኛው የከተማ ፕላን አዘጋጆች በባህላዊው ወይም በአገርኛው የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያ የፕላን ግቦችን እውን ለማድረግ የሃብትና የሥልጣን ውስንነት ያለባቸው መሆኑ እንደ አንድ ችግር ይታያል፡፡

ይሁንና በታዳጊ አገሮች ያሉ የከተማ ፕላን አዘጋጆች በጥቅም ላይ ያለውን የመሬት አጠቃቀም እንደገና በማደስ የከተማ ፕላን ግቦችን ለማሳካት አዲስ የልማት ስትራቴጂ ሳያስፈልጋቸው አልቀረም፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በታዳጊ አገሮች የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ ፕላን ግብን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ በማድረግ ሂደት ላይ የሚያጋጥማቸውን አስቻይ እና ፈታኝ ሁኔታዎችን ማየት ያስፈልጋል፡፡

### 3.3. የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ ለማድረግ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች

የከተማ ፕላን አዘጋጆች ግዙፉን የፕላን ግብ እንዴት እንደሚያሳኩት መረዳት የከተማ ግብርናውን ለማቀላጠፍ በፕላን ዝግጅቱ ወቅት ያለባቸውን አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ትንታኔ መስጠት ያስችላል፡፡

**አስቻይ ሁኔታዎች**

የሚከተሉት ነጥቦች ለከተማ መሬት አጠቃቀምን ለመለወጥ የከተማ ፕላን አዘጋጆች ያላቸው ዋና ዋና አስቻይ ነጥቦች ናቸው።

**1.ለከተማ ፕላን ፖሊሲና ለማዘጋጃ ቤት ፕላን ግብአት በመሆናቸው**

በአንድ የከተማ የፕላን ዝግጅት ውስጥ ማለትም ለከተማ ማስተር ፕላን ዝግጅት፣ ለከተማ ፕላን ፖሊሲ ረቂቅ ዝግጅት እና ለተለያዩ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ላልሆኑ የከተማ መሬት አጠቃቀምን ለውጥን ለሚያመጡ ጉዳዮች ሁሉ የከተማ ፕላን አዘጋጆች ከፍተኛ እገዛ አላቸው።

**2. የከተማ ፕላን ዓላማዎችን ለማሳካት የተለያዩ ስትራቴጂዎችና ዘዴዎችን የሚጠቀሙ መሆናቸው**

የፕላን አዘጋጆች በፕላን ዝግጅት ሂደት ውስጥ የተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ ዘዴዎችን ወይም ፕሮግራሞችን ይጠቀማሉ (Anderson, 1995)። እነኝህም የፕላን ዝግጅት ዘዴዎች ቀጥተኛ ያልሆነ ፣ ቀጥተኛ ፣እና ተቋማዊ ናቸው (Hack, 1988)።

**ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች**

በከተማ መሬት ባለቤቶች በመሬቱ አጠቃቀም ላይ የራሳቸው መብት ያላቸው በመሆኑ ብዙውን ጊዜ የከተማ ፕላን አዘጋጆች የታሰበውን የመሬት አጠቃቀም ግብን ለማሳካት የሚጠቀሙት ቀጥተኛ ያልሆነውን ዘዴን ነው (Levy, 1991)። እነዚህ ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው (Smith 1993, Levy 1991)።

- በከተማ መሬት መረጃ ሥርዓት እና በከተማ መነሻ ጥናት የተደገፈ የከተማ መሬት ዞን እና የዞን የህግ ማዕቀፎች፣
- የአካባቢ ተፅእኖ ጥናት፣
- የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣
- የመሬት ይዞታ ምስረታ (subdivision control)
- ኢኮኖሚያዊ ዘዴዎች፣ እና
- ሌሎች ዘዴዎች ናቸው።

**ቀጥተኛ ዘዴዎች**

ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው በከተማ አስተዳደር ባለስልጣናት፣ በከተማ ህግ አውጪ አካላት በሚወጡ አዋጆች ለምሳሌ በበጀት፣ በመሬት አዋጅ እና በመሳሰሉት ናቸው።

**ተቋማዊ ዘዴ**

ይህ በተቋሙ በራሱ በሚፈጠር መዋቅራዊ ለውጥ እና የሰው ሀይል አደረጃጀትን በመቀያየር በከተማ መሬት አጠቃቀም ላይ ለውጥን የማምጫ ዘዴ ነው።

በአጠቃላይ የከተማ ፕላን አዘጋጆች በከተማ መሬት አጠቃቀም ለውጥ ግብን ለማሳካት በፕላን ዝግጅትና አተገባበር ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና አስቻይ ነጥቦች ናቸው።

- የአንድ ከተማ ማህበረሰብ የሚመራው የማዘጋጃ ቤት ፕላን ቅርፅ ባለው ህጋዊ በሆነ የከተማ ፕላን ፖሊሲ ነው። ይህም ግልፅነት ባለው ሁኔታ ህዝቡ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያግዝ ነው።
- በህብረተሰቡ የፕላን ዝግጅት ሂደት ውስጥ፣ የከተማውን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ በመቅረፅና ይህንኑ ፖሊሲ በመተግበር የፕላን አዘጋጆች ቁልፉን ሚና ይጫወታሉ፣
- የፕላን አዘጋጆች የከተማ ፕላን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ መሳሪያዎች ያላቸው በመሆኑ፣
- የከተማ ፕላን ፖሊሲ የሚዘጋጀው በከተማ ደረጃ መሆኑ፣
- በለሙ አካባቢዎች የፕላን አዘጋጆች ቀዳሚውን ተነሳሽነት የሚወስዱ በመሆኑ ናቸው።

**ፈታኝ ሁኔታዎች**

1. ፕላን አዘጋጆች ውሳኔ ሰጪዎች አለመሆናቸው፤
2. በከፍተኛ የመንግስት እርከን ላይ የሚወጡ ህጎችና ፖሊሲዎች በከተማ ደረጃ ከሚወጡ ህጎች ጋር ሊጋጩ የሚችሉ መሆኑ፤
3. በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ከፊሉ ከተማዎች የተደራጀ የከተማ ፕላን ፖሊሲ የላቸውም። በመሆኑም በህብረተሰቡ የአኗኗር ታሪክ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ አካባቢዎች በተቀላቀለ ፖሊሲ፣ አጫጭር ህጎች እየታቀዱ በተለያዩ የፕላን አዘጋጆች እና የፖለቲካ ሰዎች በፈለጉት ሁኔታ የሚተረጎሙ መሆናቸው፤

4. የፖለቲካ ሰዎችና ዜጎች በፕላን ዝግጅት ውስጥ በፕላን ቅርፅ ላይ በመወሰን፣ የፕላን ፖሊሲውን በመቀበል እና ፖሊሲውን በተግባር እንዲውል የሃብት አቅርቦት በማድረግ ትልቅ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ፤
5. በአብዛኛው የከተሞችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕላኖችን ግብ የሚያሳካ አዲስ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ሲዘጋጅ የከተማ ፕላን አዘጋጆች የሚጠቀሙት ቀጥተኛ ያልሆነ ዘዴን ነው። ስለሆነም በዚህ ዘዴ አስገዳጅ ነገሮች አለመኖርና የክትትል እጥረት መኖር የከተማ ፕላን ፖሊሲው ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርግ መሆኑ፤
6. የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ገለልተኛ አካሎች በከተማ የመሬት ፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ ስለሚኖራቸው፤
7. ግንባታዎች ባሉባቸው አካባቢዎች የከተማ ፕላን አዘጋጆች ያላቸው ተፅዕኖ አናሳ መሆን እና የመሳሰሉት ናቸው።

### 3.4. በታዳጊ አገሮች የከተማ ፕላን አዘጋጆች አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ለከተማ ግብርና ያላቸው ፋይዳ

የከተማ ፕላን አዘጋጆች በከተማ መሬት አጠቃቀም ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳርፉ ከላይ በተዳሰሱ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ተመልክተናል። ስለዚህ ከዚህ የምናጠቃልለው ምንድነው? የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ መሬት ለአንድ ዓላማ ለምሳሌ ለከተማ ግብርና እንዲውል ዕድል በመፍጠርና በማበረታታት የራሳቸው ሚና እንዳላቸው ነው። የከተማ ፕላን አዘጋጆች በከተማ ልማት ፖሊሲ ዝግጅት ውስጥ እንደ አቀጣጣይ በመሆን የቀረቡ ዕቅዶች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ወይም እንዲጣሉ በማድረግ በመሬት የሀብት ክፍፍል የሚፈጠሩ ሽኩቻዎችን በመፍታት ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ የሚገባቸውን የከተማ መሬቶች በማመላከት ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። ነገር ግን በከተማ መሬት አጠቃቀም የመጨረሻው ውሳኔ የሚሰጠው በተለያዩ የእርከን ደረጃ ላይ ባሉ የመንግስት ውሳኔ ሰጪዎች፣ በሌሎች የማዘጋጃ ቤት ባለሞያዎች፣ በከተማ ነዋሪው ህዝብ ይሁንታ እና ተፅእኖ ላይ ተመስርቶ ነው (IDRC,1999)።

### 3.5. የከተማ መሬት ፕላን ዝግጅት መርሆዎችና ዘዴዎች፡ ከከተማ ግብርና ጋር ያላቸው ቅንጅት

የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን የሚወሰነው በፖሊሲ፣ በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ ጉዳዮችን እና ቴክኖሎጂን ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን በውጤቱም የህዝቡን ኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ለማበልጸግ እና የመሬት አጠቃቀም ቅንጅትን ለማምጣት ነው። የተቀናጁ የመሬት አጠቃቀም መርሆዎች በፕላን ዝግጅት ሂደት ውስጥ የወደፊቱን የመሬት አጠቃቀም ውሳኔን ለመምራት የጠራ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲኖር ያደርጋል። የመሬት አጠቃቀም ፕላን እና ካርታ መኖር የከተማ ግብርናን ጨምሮ ማንኛውም ለውጥ እንዲቀናጅና ክትትል እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። እንደ ከተማ ፕላን ባለሞያዎች ተሞክሮ መሠረታዊ የመሬት አጠቃቀም መርሆዎች የሚከተሉትን የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው።

1. ለኑሮ አመቺነትን ማረጋገጥ (Sense of Place)፦ የተደራጀ፣ የተመቻቸ ለሰዎች ለትምህርት፣ ለስራ እና ለኑሮ ምቹና አስደሳች አካባቢ መፍጠር
2. ተደራሽነት (Accessibility)፦ ተደራሽነትን ማረጋገጥ ለማህበራዊ ምቾትና አገልግሎት፣ ለመረጃ ልውውጥ እና ለኢንቬስትመንት እና ለልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ስኬት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በማንኛው ጉዳይ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች የህዝብ የእርስ በርስ ግኑኝነትን የቀለለ ሆኖ በሁሉም ሥፍራ የሚኖሩ ሰዎች አብረው ተቀናጅተው እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።
3. የአካባቢ ደህንነትን መጠበቅ (Respect for the environment)፦ የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ ማቀድ ለአካባቢው ዘላቂ ልማት ዋስትናን ያረጋግጣል።
4. ፍሰትን (Circulation)፦ የፍሰት ኡደቱን ማሳደግና ማጎልበት፣ በከተማውና በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ትስስርና ልውውጥ ማጎልበት፣ ለእግረኛ ትኩረት በሚሰጥ መልኩ የትራፊክ ፍሰቱን ማቅለል እና የህዝብ ለህዝብ ግኑኝነትን ማጠናከር
5. ማጣጣም (Compatibility)፦ ቀደም ሲል የነበረውንና አዲሱ ተጣጥመው እንዲቀጥሉ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ
6. ከጊዜና ከሁኔታ ጋር ማሻሻል (Flexibility)፦ ከህብረተሰቡና የባለ ድርሻ አካላትን ፍላጎትን መሠረት አድርጎ ልዩ ልዩ የግንባታና የልማት እቅዶችን ማሻሻል (Magigi, Wakuru 2008)።

በተለያዩ ደረጃዎች በሚዘጋጁ የከተማ መሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅቶችና በከተማ ግብርና አተገባበር ሂደት ላይ እነዚህ መርሆዎች ሊቃኙ ይገባል። ከላይ ለተገለፁ መርሆዎች የተሰጡ ትንታኔዎች እንደሚያሳዩት የከተማ ግብርና ቅርፅና አፈጣጠር በከተማ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ውስጥ መታቀፍ ያለበት መሆኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያሳያል።

### 3.6. የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያዎች ጋር ማቀናጀት

የከተማ ግብርና በፕላን ዝግጅት ሂደት ከተለያዩ የፕላን ማቀጃ መሳሪያዎች ጋር ማቀናጀት ያስፈልጋል:: ግብርናው የሚቀናጀው በተለያዩ የፕላን ዝግጅት ደረጃዎች ላይ ሲሆን ቅንጅቱን ለማምጣት የተለያዩ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያዎች ጋር እንዴት ማቀናጀት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው::

**ሰንጠረዥ 2. የከተማ ግብርናን ከተለያዩ የፕላን ማዘጋጃ መሳሪያዎች ጋር ማቀናጀት**

| የፕላን ዝግጅት ደረጃዎች | የከተማ ግብርና ማቀናጃ ሁኔታዎች | ባለድርሻዎች |
|---|---|---|
| **የመሬት አስተዳደር** | በፕላን ዝግጅት ተሳታፊ በሚሆኑ ተቋማት ውስጥ በውሳኔ አሰጣጥ፣ በአፈፃፀም፣ በፋይናንስ፣ በማስተባበርና በመቆጣጠር ላይ በሚኖር ህብረት<br>በከተሞች አስተዳደር ለከተማ ግብርና ዘላቂነት ተስማሚ ቦታዎችን መለየት<br>የከተማ ግብርና መሬት ይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ | ማዕከላዊ መንግስት፣ የክልል መንግስታት፣ የግሉ ሴክተር፣ የሲቪሉ ማህበረሰብ እና ሌሎች የልማት አጋሮች |
| **ማስተር ፕላን** | በመንግስት ደረጃ ለፕላን ዝግጅት በሚወጡ ፖሊሲዎችና ግቦች | ለመሬትና ለከተማ ልማት ሃላፊነት ያለው ሚኒስቴር<br>የክልሎች ጉዳይ የሆኑ ሚኒስቴሮች<br>የከተማ አስተዳደሮች<br>አማካሪዎች |
| **ስትራቴጂክ ፕላን** | የከተማ ግብርና ላይ ብቻ ያተኮረ መኖር | የአካባቢ ባለስልጣናት (የከተማ አስተዳር ወይም ማዘጋጃ ቤቶች) |
| **የመሬት አጠቃቀም ፕላን** | የከተማ ግብርናን ቦታ የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት<br>የተለዩ መሬቶችን በብሎክ ወይም በፕሎት ማሳየት<br>በከተማ ግብርና ቦታዎች ላይ ቀያሾችን መጠቀም | የአካባቢ ባለስልጣናት (የከተማ አስተዳር ወይም ማዘጋጃ ቤቶች)<br>ለመሬትና ለከተማ ልማት ሃላፊነት ያለው ሚኒስቴር |
| **የመሬት ሽንሽና** | ትርፍ መሬት ባሉባቸው እና ዝቅተኛ የህዝብ ክምችት ባሉባቸው በከተሞች ዳርቻዎች | የአካባቢ ባለስልጣናት (የከተማ አስተዳር ወይም ማዘጋጃ ቤቶች) ለመሬትና ለከተማ ልማት ሃላፊነት ያለው ሚኒስቴር |
| **ሳይት ፕላን** | ለከተማ ግብርና የሚሆኑ ቦታዎችን በግለሰብ ማሳ ደረጃ ማሳዬት | ግለሰብ አልሚዎች<br>አማካሪዎች |

**ምንጭ፡ Magigi, Wakuru ,2008**

# ክፍል አራት

## 4. በኢትዮጵያ በከተማ ግብርና ዙሪያ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች ትንተና

### 4.1.የኢፌድሪ ህገ መንግስት

በ1987 የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የዜጎችን ሰብአዊ፣ ዴሞክራሲያዊና የኢኮኖሚ መብት በተመለከተ በተለያዩ ክፍሎች ደንግጓል። በዚህ ህገ-መንግስት አንቀፅ 41 ስለኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህል መብቶች ይደነግጋል። በዚህ አንቀፅ የሚከተሉት የዜጎች የኢኮኖሚ መብቶች ተደንግገዋል።

- ✓ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።
- ✓ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።
- ✓ መንግስት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራን ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።
- ✓ መንግሥት ዜጎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል ።

በሌላ በኩል በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀፅ 43 ስለልማት መብቶች ይደነግጋል። በዚህ አንቀፅ ሥር የሚከተሉት የዜጎች የልማት መብቶች ተደንግገዋል።

- ✓ የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ ዕድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው ይላል።
- ✓ የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የዜጎችን ዕድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል።

በሌላ በኩል በዚሁ ህገ-መንግስት ምዕራፍ አሥር የብሄራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎችን ይደነግጋል። በዚህ ምዕራፍ አንቀፅ 90 ስር የሚከተሉት መርሆዎች ተደንግገዋል።

- ✓ ሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሀ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ይደረጋል (ኢፌዴሪ መንግስት፣1987)።

የሚሉት ከድህነት ቅነሳና ከሥራ አጥነት ችግር ጋር በተያያዘ የከተማ ግብርናን በሀገሪቱ ከተሞች በማስፋፋት የዜጎችን የኑሮ ትግል ለማገዝ የሚያስችሉ የፖሊሲ አንቀፆች ናቸው።

### 4.2.ፖሊሲ

### ሀ. የከተማ ልማት ፖሊሲ

በነሐሴ 1998 ዓም በምኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቀው የከተማ ልማት ፖሊሲ ክፍል ሁለት የፖሊሲው ራዕይ፣ ዓላማና መነሻ መርሆዎችን ያብራራል። የፖሊሲው ራዕይ "ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ልማትና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያረጋግጡ፣ ለኑሮ አመቺና በፕላን የሚመራ እንዲሆኑ በማድረግ የአካባቢያቸው የልማት ማዕከልና የዴሞክራሲ ተምሳሌት ሆነው እርስ በርስ ተሳስረው ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን በማረጋገጥ በልፅገው ማየት ነው" ይላል። በዚሁ ክፍል ውስጥ የተለያዩ የፖሊሲው መርሆዎች የተገለፁ ሲሆን በ"መ" ስር የተገለጸው የሚከተለውን ሃሳብ ይዟል ።

- ✓ የከተማ ልማት ሥራ ማዕከሉ ድህነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ እንዲሆን ማድረግ ነው ይላል ።

በክፍል አራት ፈጣንና ፍትሀዊ ልማት በከተሞች  በሚለው ሥር በንዑስ አርስት ስለ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማትን ማስፋፋትን አንደኛው የፖሊሲው አካል አድርጎ አስቀምጧል። በዚህ ክፍል የሚከተለውን ሀሳብ እናገኛለን።

> "የከተማ ልማት ሥራችን ማዕከሉ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማትን ማስፋፋት መሆን ይኖርበታል ። ምክንያቱም  ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት ለከተማ ድህነት

ቅነሳና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት ቁልፍ ሚና ስላላቸው ነው፡፡”
ይላል፡፡

እንደዚሁም ደግሞ በዚሁ ክፍል ሥር የአካባቢ ጥበቃ በከተሞች በሚለው የከተማ አስተዳደሮች ሊወስዱ ከሚገባቸው የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎች አንዱ ስለ ተክል መትከል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ በ “መ” የቀረበው የሚከተለው ነው፡፡

- ✓ በየተቋማቱ፣ በመኖሪያ ቤቶች፣ በየመንገዱና በከተማው መናፈሻዎችና ተፋሳሾች ተክል የመትከልና የመንከባከብ ሥራ ማካሄድ፤ተክሎቹ ሲያረጁ ወይም ለሌላ ሥራ ሲፈለጉም የግድ እንዲተኩ ማድረግ፡፡ የሚለው ጉዳይ አንደኛው የፖሊሲው አካል ነው (ከልኮሚ፣ 1998)፡፡

## ለ. የአካባቢ ፖሊሲ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እ.አ.አ. በ1997 ያወጣው የአካባቢ ፖሊሲ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችን ለማሳካት የተነደፈ እንደሆነ የፖሊሲው ሰነድ ያብራራል፡፡

1. ዘላቂነት ያለው የአካባቢ ሥነ-ምህዳር በመፍጠር የብዝሃ ህይወት ሥብጥርን በመጠበቅ የሚተኩ የተፈጥሮ ሃብት የሚቀጥለውን ትውልድ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ በአግባቡ መጠቀም እና የመራባት ሑደት እንዲቀጥል ማድረግ፡፡
2. የማይተኩ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ቀጣይነትን በሚያረጋግጥ እና አካባቢን ጉዳት ላይ በማይጥል መልኩ እንዲሆን ማድረግ
3. የነዋሪዎችን ተፈጥሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ ፍላጎታቸውን በዘላቂነት ለማርካት በሚያስችል መልኩ መኖሪያ አካባቢን ማሻሻል፡፡
4. የአካባቢ ብክለትን መከላከል … እና የመሳሰሉት ናቸው

በተጨማሪም የከተሞችን የተፈጥሮ አካባቢን በመጠበቅ ለኑሮ ምቹ ሆነው ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ቀጣይነት ያለው የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርቦሽ የሚጠይቅ የቅንጅት ሥራ እንደሚያስፈልግ ሰነዱ በፖሊሲ አቅጣጫው አመልክቷል (FDRE፣ 1997)፡፡

## ሐ. የከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ፖሊሲ፤ የአፈፃፀም ስልቶች እና የአቅም ግንባታ ማዕቀፎች

የከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ፖሊሲ በክፍል ሁለት ውስጥ የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ማስፈፀም፤ የከተሞች አረንጓዴ ልማትና ውበት መጠበቅ የሚለው አራተኛው ንዑስ ርዕሥ በኢትዮጵያ ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ዙሪያ የሚከተለውን መርህ አስቀምጧል።

"የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ማስፈፀም በመሰረታዊነት የከተሞችን የመተግበር ብቃት ማሳደግ እንዲሁም ለዚሁ የሚያግዝ አሠራርና አደረጃጀት መፍጠርን የሚያካትት ሲሆን ከተሞች በመሬት አጠቃቀም ፕላናቸው ማቀፍ ውስጥም አረንጓዴ፣ የተዋበ፣ የተክልና ዕጽዋት ከተማን (Garden city) መርህን በተከተለ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታ" ይላል (ኢፌዴሪ፣ 2003)።

## መ. በአዲስ አበባ የከተማ ግብርና ፖሊሲ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሀገር ደረጃ የከተማ ግብርና ፖሊሲ በኢትዮጵያ እስካሁን ባይኖርም በ2004 ዓ ም የአዲስ አበባ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የከተማ ግብርና ፖሊሲ ቀርጿል። ይህም ፖሊሲ አራት የፖሊሲ ግቦች ሲኖሩት እነዚህን የፖሊሲ ግቦች ለማሳካት ከዚህ የሚከተሉት ስድስት የፖሊሲ አላማዎች ተቀርጸዋል፡፡

1. በከተማው ለሚከናወን የግብርና ስራ ተስማሚ የሆነ መሬት አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ፤
2. በከተማዋ ለሚከናወን የግብርና ስራ ዘላቂ እና አስተማማኝ የሆነ የውሃ አቅርቦት መኖሩን እና ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፤
3. በከተማው የሚተገበር የግብርና ስራ ምርታማነትን ማሳደግ እና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን ማምጣት እንዲችል ሁሉን አቀፍ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ አስፈላጊውን የድጋፍ አገልግሎት ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ፤
4. በከተማዋ የሚከናወን የግብርና ስራ ከጤና እና አካባቢ ስጋቶች ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ፤
5. የከተማ እና ከፊል ከተማ ግብርናን በተመለከተ ያለውን ግንዛቤ እና የህግ ማዕቀፍ ማሻሻል፤
6. በከተማ እና ከፊል ከተማ ግብርና ፕሮግራሞች ውስጥ የሥነ-ፆታ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ከከተማ ግብርና አንጻር መካተታቸውን ማረጋገጥ (አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ 2004)።

## 4.3. አዋጅ

### 4.3.1. የከተማ ፕላን አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለ ከተማ ፕላን በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 በፕላን የሚመሩና የዳበሩ ከተሞች እንዲኖሩና በከተሞች ውስጥ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠርና በማመቻቸት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲሻሻል የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተደንግገዋል።

በአዋጁ ክፍል ሁለት ማለትም "የከተማ ፕላን ስለማመንጨትና ስለማዘጋጀት" በሚለው አንቀጽ አምስት ላይ ማንኛውም የከተማ ፕላን የሚመንጭበትና የሚዘጋጅብት ሂደት መሠረታዊ መርሆዎች ተቀምጠዋል። ከነኝህም መርሆዎች የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

- ✓ የማህበረሰብ እና የአካባቢ ደህንነትን መጠበቅ፣
- ✓ የህዝብና የግል ፍላጎቶች ተጣጥሞ መገኘት፣
- ✓ ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጥ ሆኖ መገኘት ናቸው።

በሌላ በኩል በክፍል ሁለት አንቀፅ አስራ አንድ የአካባቢ ልማት ፕላን ትርጓሜ እና ይዘት ውስጥ ንኡስ አንቀፅ ሶስት ማንኛውም የአካባቢ ልማት ፕላን እንደየ አግባብነታቸው የአረንጓዴ ቦታዎችን፣ ክፍት ቦታዎችን፣ የውሃ አካላትን እና እንዲሁም ለጋራ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል።

### 4.3.2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ

በሀገራችን በኢትዮጵያ ከተሞች ደረጃ የከተማ ግብርና ጽ/ቤትን ማቋቋሚያ አዋጅ ባይኖርም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ በጥር 15 ቀን 1995 ዓም ፀድቋል። ይህ አዋጅ የከተማ ግብርና ጽ/ቤትን ስልጣንና ተግባርን ይደነግጋል። በዚህ አዋጅ ድንጋጌ ጽ/ቤቱ፦

1. በከተማ ውስጥ ግብርናና ምርት በጥራት የሚመረትበትንና ለገበያ የሚቀርብበትን እንዲሁም የግብርና ልማትን የሚያጎለብት የኢንቬስትመንት ሥራ የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሳል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል።

2. የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለገበሬዎች እንዲዳረስ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ውጤታቸውንም ይከታተላል። ለገበሬው ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል ።

3. ለገበሬዎች የእንስሳት ህክምናና የማዳቀል አገልግሎት መስጠቱን ያረጋግጣል። የአስተዳደሩን የእንስሳት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል። የአስተዳደሩን የብዝሃ ህይወት ቤተ ሙከራዎችን ያስተዳድራል፤ የምርምር ውጤቶችን ገበሬዎች እንዲጠቀሙባቸው ያደርጋል።

4. የእንስሳት ቆዳና ሌጦ አገር አቀፍ ደረጃን መሠረት በማድረግ በጥራት መመረታቸውን ያረጋግጣል።

5. የእንስሳትንና የእፅዋትን የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል። በከተማ ውስጥ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

6. ደን የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሳል፣ ስለደን ሃብት ልማት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ ያዘጋጃል።

7. በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል። የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው (አዲስ አበባ አስተዳደር፣ 1995)።

### 4.3.3. የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ በአዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በአዋጅ ቁጥር 721/2011 የወጣው አዋጅ በአንቀፅ 18 የከተማ ቦታ ሊዝ ዘመን አስመልክቶ ለከተማ ግብርና የሚሰጡ የከተማ መሬቶችን በተመለከተ በአንደኛው ንዑስ አንቀፅ በቁጥር

ሀ. በተራ ቁጥር ሁለት ለከተማ ግብርና የሊዝ ዘመን ጣሪያ 15 አመታት መሆኑን ደንግጓል (ኢፌዴሪ፣ 2004)።

## 4.4. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

**የስትራቴጂክ ዕቅዱ ዓላማ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰፊ መሠረት ያለው፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ልማትን የማፋጠንና ድህነትን የማስወገድ ዓላማ ያለው አጠቃላይ የሀገሪቱን የልማት እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያስችል የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2003-2007) ማዘጋጀቱ ይታወቃል:: ይህንን ዕቅድ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ክፍለ-ኢኮኖሚያዊ የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አዘጋጅቷል:: የዚህ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ዝርዝር ዓላማዎች ውስጥ እንደተገለጸው የመጀመሪያው ዓላማ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት አማካይነት በከተሞች በስፋት የሚታየውን የሥራ አጥነትና ድህነት ችግር መቅረፍ የሚያስችል ስልት በመንደፍ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ነው:: ይህ ዕቅድ ዝርዝር ዓላማና ግቦች ያሉት ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል::

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ክፍለ-ኢኮኖሚያዊ የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁለተኛው ዓላማ ሰፊ የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ ድህነትን በማስወገድ ሠፊ መሠረት ያለው ልማታዊ ባለሀብት በመፍጠር ለኢንዱስትሪው ልማት አስተማማኝ መሠረት በመሆን በሀገሪቱ ልማት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወት በምርትና በአገልግሎት ብቁ ተወዳዳሪና ብቁ የሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ማፍራት ነው::

በዚህ ዕቅድ ውስጥ የስራ ዕድል ፈጠራ በፕሮጀክት አራት የተካተተ ሲሆን ዓላማውም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ድህነትንና ሥራ አጥነትን መቅረፍ ነው::

በሌላ በኩል በግብ አራት በዕቅድ ዘመኑ በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በከተማ ግብርና ዘርፍ ለ356,012 ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ የተያዘ መሆኑ በሰነዱ ተቀምጧል (ከልኮሚ፣ 2002)::

## 4.5. ስትራቴጂ

*ሀ. የፌዴራል መንግስት የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና አብዮታዊ ዴሞክራሲ፦*

በ1999 ዓ.ም ታትሞ የወጣው የፌዴራል መንግስት የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰነድ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማትና የህዝብ ተጠቃሚነት በሚለው ክፍል ውስጥ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ የሥራ ዕድልን በመፍጠር የከተማውን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ያሳያል (ኢፌዴሪ መንግስት፣ 1999) ፡፡

በ2003 የፀደቀው የመንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ፣ የድጋፍ ማዕቀፍና የአፈፃፀም ስልቶች ሰነድ በዘርፉ የመንግስትን ስትራቴጂ ያብራራል፡፡ ይህም ስትራቴጂ የተለያዩ ዋና ዋና ዓላማዎች ቢኖሩትም የሚከተለው አንዱ ነው፡፡

“ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር የህዝባችንን ገቢ ለማሻሻልና ድህነትን ለመቀነስ እንዲሁም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲፈጠር ማድረግ”፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የልማት አቅጣጫ በ“ሠ” እንደተጠቀሰው ዘርፉ ለግብርና ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ተመጋግቦ እና ተደጋግፎ እንዲያድግ ያሳያል፡፡

በዚሁ ሰነድ ላይ በክፍል አንድ በሦስተኛው ምዕራፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ትኩረት የሚሰጣቸው ዘርፎችን በመለየት በንኡስ አርዕስት 3.5 በግልፅ አብራርቷል፡፡ በዚህም መሠረት በስትራቴጂው የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት የዓምስቱን ዓመት የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ መነሻ በማድረግ በተለይ ለኤክስፖርትና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን ለሚተኩ የማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ ልዩና የላቀ ትኩረት ይሰጣል፡፡

በተለይ ሰፊ የሥራ ዕድል ለሚፈጥሩ ለማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ ለንግድና የተለያዩ አገልግሎትና በግብርና ዘርፎች ሥር ላሉ ንዑስ ዘርፎችና የሥራ ዘርፎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

በስትራቴጂው የተገለፁት የከተማ ግብርና ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘመናዊ የእንስሳ ዕርባታ፣
- የንብ ማንባት፣
- የዶሮ እርባታ፣
- ዘመናዊ የደን ልማት፣

- አትክልትና ፍራፍሬ፣
- ዘመናዊ የመስኖ ሥራ፣
- የእንስሳ መኖ ማቅረቢያ (ኢፌዴሪ መንግስት፣ 2003)፡፡

### ለ. የአረንጓዴ ልማትና ውበት ስትራቴጂ፦

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሀገሪቱ ከተሞች በአረንጓዴ ልማት የተዋቡ ሆነው ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ የአረንጓዴ ልማትና ውበት ስትራቴጂ መቅረጹ ይታወቃል፡፡ ይህም ስትራቴጂ በከተሞች ለአረንጓዴ ልማት ግብ ስኬት የከተማ ግብርናን በመሳሪያነት ያሰለፈ ሲሆን በዚህ ስትራቴጂ ለከተማ ግብርና ልማት አተገባበር የሚሆን ግልጽ የአሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋት ዙሪያ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> "የከተማ ግብርና ልማት ለምግብነት የሚሆኑ ሰብሎችን ከማምረት በተጨማሪ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ብዙዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ለከተማ አረንጓዴነት ልማት ሽፋን ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የከተማ ግብርና ልማት የሚመራበት ግልጽ የሆነ አሰራር ይዘረጋል፡፡ ለዚሁም የከተማ ግብርና አረንጓዴነት ልማት ደንብ፣ መመሪያ፣ ስታንዳርድና የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት ልማቱን ማካሄድ እና የክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ሥራ መስራት ወሳኝ ይሆናል፡፡" ብሏል (ከልኮሚ፣ 2004)፡፡

### ሐ. የከተሞች ኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅ

በከተሞች የሚታየውን የድህነትና የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ በሚካሄደው እንቅስቃሴ በከተማ ግብርና ዘርፍ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችሉ የድጋፍ ፓኬጆችን በማዘጋጀት በዘርፉ የሚሰማሩ አንቀሳቃሾችን በተሻለ ሁኔታ በማሳተፍ ለከተሞች ልማት የበኩላቸውን እንዲጫወቱ ለማስቻል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራም የከተማ ግብርና ዘርፍ የድጋፍ ፓኬጅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀረፀውን ለመነሻነት ለዚህ ጥናት ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ሰነዱ በከተማ ግብርና ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚህ ስርም ስድስት የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መስኮች ተለይተዋል እነርሱም የአትክልት ልማት፣ የሀር ልማት፣ አነስተኛ የበግ ማደለብ ሥራ፣ የወተት ከብት እርባታ፣ የንብ እርባታ እና የዶሮ እርባታ ናቸው፡፡ ሰነዱ በከተማ ግብርና የሥራ ዘርፍ ያሉ ማነቆዎችን፣ መፍትሄዎችንና ወደዚህ የሥራ መስኮች

ለሚሰማሩ ሰዎች የሚያስፈልጉ የድጋፍ ፓኬጆች ወይም ግብዓቶችን አካቷል *(ኢፌዴሪ፣ 1999)*።

በአጠቃላይ በሀገሪቱ የተቀረፁ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶች፣ ስትራቴጂዎችና ፓኬጆች ዘላቂ የከተማ ግብርና በከተማ ልማት ማዕቀፍ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ያሳያል።

# ክፍል አምስት

# 5. መረጃን መተንተን

## 5.1.የከተማ ግብርና ነባራዊ ሁኔታ በኢትዮጵያ

የግብርና ልማት እና ዕድገት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ወሳኝ ነው። የግብርናው ዘርፍ ለሀገሪቱ ከአጠቃላዩ GDP 70 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን ዘርፉ በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚኖሩ ገበሬዎች ዋና የኑሮ መሠረት ሆኖ ቆይቷል። የማእከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደሚያመለክተው በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራው የህዝብ ቁጥር ከሀገሪቱ ከአጠቃላዩ 86 በመቶ ያህሉ ነው። በከተሞች አካባቢ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ የህዝብ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ለጊዜው መረጃው ባይገኝም በተለያዩ ጾታ፣ የእድሜ ክልል እና የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ብዛት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በዘርፉ እንደተሰማሩ ለዚህ ጥናት የተደረገ የአይን ምልከታና የቃለ መጠይቅ ምላሽ ግምት ያሳያል።

### 5.1.1.የግብርና ዓይነቶች

የ1996 የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ሪፖርት እና የተለያዩ የከተማ ግብርና ጥናቶች ውስጥ እንደተገለፀው የተለያዩ የከተማ ግብርና ዓይነቶች በከተሞች ተግባራዊ እየሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ከተሞች ረዘም ላሉ ዓመታት በርካታ የግብርና ዓይነቶች እየተካሄዱ እንደቆዩ በተለያዩ የጥናት ውጤቶች ተገልጿል። በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ጥናት ናሙና ከሆኑ ከተሞች የተሰበሰበው መረጃ በከተሞች በስፋት እየተካሔዱ ያሉ የግብርና አይነቶችን ለይቷል። እነሱም የጓሮ አትክልት፣ የፍራፍሬ ዛፎች፣ የደን ዛፎች፣ የአበባና የውበት ተክሎች፣ ትንንሽ ለማዳ እንስሳ እርባታ፣ የባህላዊ መድሀኒት ተክሎች፣ ትልልቅ ለማዳ እንስሳ እርባታ፣ የዶሮ እርባታ፣ የአሳ እርባታ፣ የንብ እርባታ፣ የጥርኝ እርባታ፣ የሃር ትል ልማት፣ የአሳማ እርባታ፣ የጥንቸል እርባታ፣ በከተማ ዙሪያ የአዝርእት ልማትን፣ ለእንስሳ መኖ የሚሆኑ ተክሎችን ማልማትን ያጠቃለለ ነው።

እነኚህ የግብርና አይነቶች ሲካሄዱ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶች ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሆነ የተሰባሰበው መረጃ ያሳያል። ለምሳሌ ዘመናዊ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ የተለያዩ

የአረም የተባይ እና የበሽታ ማጥፊያ ኬሚካሎች፣ ማቀዝቀዣ፣ የጫጩት መፈልፈያ፣ የጠብታ መስኖ፣ የቤት ውስጥ የተለያዩ ማብቀያ ዕቃዎች፣ የእንስሳት መድሃኒቶች፣ በወንዞች ወይም በሃይቆች ላይ የመስኖ ስራ፣ የቤት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀምን፣ የሽንት ቤት እዳሪን ለማዳበሪያነት መጠቀምን፣ ዘመናዊ የንብ ቀፎ፣ የሽግግር ቀፎ፣ የእንስሳ መኖ እና መሬትን በዋናነት ጨምሮ የመሳሰሉ ግብአቶች ጥቅም ላይ አየዋሉ እንደሆነ የተሰባሰበው መረጃ ያሳያል።

### 5.1.2.የከተማ ግብርና ሥፍራዎች

በኢትዮጵያ ከተሞች የከተማ ግብርናዎች የሚካሄዱባቸው ሥፍራዎች አንዳንዶች ካልሆኑ በስተቀር በአብዛኛው ከተማ የቦታ አመራረጥ በጥናት የተደገፈና እና ህጋዊነትን የጠበቀ አለመሆኑን የባለሞያዎች ምላሽ ያረጋግጣል። በከተሞች በአብዛኛው የከተማ ግብርና የሚካሄዱባቸው ሥፍራዎች የሚከተሉት ናቸው።

- በወንዞች እና በሐይቅ ዳርቻዎች፣
- ለቆሻሻ ማስወገጃ በተከለሉ አካባቢዎች፣
- በግለሰብ ግቢዎች፣
- በማስፋፊያ አካባቢዎች፣
- ለአረንጓዴ ተብለው በተለዩ አካባቢዎች፣
- በመኖሪያ አካባቢዎች፣
- በከተማ ዳርቻዎች፣
- በከተማ የውስጥ ባዶ ቦታዎች፣
- በትምህርት ቤቶች፣
- በተራራማ አካባቢዎች የደን ልማት፣
- በመንገድ ዳርቻዎች እና አካፋዮች፣
- በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ባሉ ባዶ ቦታዎች…ወዘተ ናቸው።

### 5.1.3. የከተማ ግብርና ጥቅሞች

በዓለማችን የከተማ ግብርና የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጥቅሞች እንዳለው ከላይ በተዛማጅ ፁሑፎች ዳሰሳ ውስጥ እንደተገለፀው የተለያዩ ጥናቶች ያረጋገጡ

ሲሆን በኢትዮጵያ ከተሞችም ቢሆን እየተካሄደ ያለው የከተማ ግብርና ከሌሎች ዓለማት ተመሳሳይ ጥቅሞች እንዳለው ጥናቶች ያስረዳሉ (Mohammed, 2002):: በዚህም የዳሰሳ ጥናትም በአንዳንድ የናሙና ከተሞች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ግብርናው በተመሳሳይ ሁኔታ ለከተማው ህዝብ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን እየሰጠ እንደሆነ የተጠያቂዎች ምላሽ አረጋግጧል:: በኢትዮጵያ ከተሞች የከተማ ግብርና የህብረተሰቡን ጤናን እና የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ፣ የሥራ ዕድል መፍጠርና በገቢ ምንጭነት፣ የከተሞችን አካባቢ ደህንነት በማስጠበቅ እና ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት በርካታ የማይናቁ ጥቅሞችን ለህብረተሰቡና ለከተማ አካባቢዎች እየሰጠ ይገኛል:: በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ከተሞች የከተማ ግብርና እየሰጠ ያለው ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉትን ዝርዝሮች እንደሚያጠቃልል የተሰጡ ምላሾች ያሳያሉ ::

1. በጤና እና በምግብ ዋስትና ዘርፍ፦
   - የምግብ ምንጭ በመሆን
   - የተመጣጠነ እና የተሟላ የምግብ አቅርቦት በመስጠት
   - ረሃብና የምግብ እጥረትን በማስወገድ ሁሉም የከተማው ህዝብ ጤነኛ፣ አምራች እና በሽታን የሚቋቋሙ እንዲሆኑ በማድረግ የበኩሉን ድርሻ ይጫወታል
2. በኢኮኖሚው ዘርፍ
   - የገቢ ምንጭ በመሆን
   - የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣
   - የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ የገንዘብ አቅምን መገንባት፣እና
   - የውጪ ምንዛሪን ማስገኘት
3. የከተሞችን አካባቢ ደህንነት በማስጠበቁ በኩል
   - የከተሞችን ውበት እንዲጠበቁ በማድረግ፣
   - የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻን በማስተካከል ጽዱ ከተማ በመፍጠር፣
   - በጥላ ዛፎች የእግረኞችን ደህንነት መጠበቅ፣
   - የመኖሪያ ቤቶች አካባቢዎች ለኑሮ አመቺ እንዲሆኑ በማድረግ፣
   - የአካባቢ የአየር ሚዛን እንዲጠበቅ በማድረግ፣ እና
   - የከተሞችን አካባቢ ሥነ ምህዳር እንዲጠበቁ በማድረግ

4. የማህበራዊ ጥቅሞች፦ የከተማ ግብርና ልመናን፣ ሴተኛ አዳሪነትን፣ ወንጀልና እና የመሳሰሉትን በከተሞች እንዲቀንሱ በማድረግ ማህበራዊ ቀውሶች በሀገሪቱ ከተሞች እየተዋጋ ይገኛል።

### 5.1.4. የግብርናው አሉታዊ ተጽዕኖዎች

የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በከተማ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን በአግባቡ ካልተመራ የጤና እና የንፅህና ችግር በከተማ አካባቢ የማስከተል እምቅ ሀይል አለው። እንደ ጥናቶች አገላለፅ በከተማ የሚፈጠረው የግብርና አሉታዊ ተጽዕኖ በምርት ወቅት፣ በምርት ማሰባሰብ እና በግብይት ወቅት ከሚኖር የምርት ብክለት ጋር ሊገናኝ ይችላል። በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና የማይናቅ ትልቅ ጥቅም ቢኖረውም በግብርናው ምክንያት እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችም እንዳሉ የባለሞያዎች ምላሽ ያሳያል። የሚከተሉት በከተሞች እየታዩ ያሉ የከተማ ግብርና ችግሮች ናቸው።

- የእንስሳት ፍግን በአግባቡ ካለመያዝ የተነሳ በአየር ብክለት ምክንያት በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት ማስከተል፣
- በዶሮ እና በአሳማ እርባታ ምክንያት የሚከሰት የአካባቢ ሽታ፣
- የከብቶች እዳሪ እና በግብይት ወቅት የአትክልት ምርቶች አካባቢን ማቆሸሽ፣
- የአትክልት ምርቶች ለብክለት የተጋለጡ ከመሆኑ የተነሳ በአያያዝ ችግር ምክንያት በሰዎች ጤና ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣
- ስልጠና ባላገኙ ገበሬዎች ጥቅም ላይ በዋሉ የተለያዩ ኬሚካሎች ምክንያት የሚፈጠር የውሃና የአየር ብክለት፣
- ከኢንዱስትሪና ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚለቀቁ ኬሚካሎች የተበከለ ውሃን በመጠቀም በተመረቱ አትክልቶች ምክንያት በአምራቹ፣ በአቅራቢዎችና በተጠቃሚዎች ላይ የሚመጣ የጤና ችግር፣
- ለግብርና ሥራ የሚውሉ ኬሚካሎች ለመጠጥና ለሌሎች ሥራዎች የሚውሉ ውሃን መበከል፣
- በሚቴይንና በካርበን ልቀት ምክንያት የአየር ብክለት መከሰት፣
- በዶሮዎች እና በሌሎች እንስሳት ጩኸት ምክንያት የሚፈጠር የድምፅ ብክለት እና

➢ አልፎ አልፎ የንቦች በሰውና በከብቶች ላይ የሚያደርሱት የወረራ ችግር ናቸው።

## 5.2. ከፕላን ጋር በተገናኘ ለከተማ ግብርና ማነቆ የሆኑ ጉዳዮች

የፕላን አዘጋጆች እና የፕላን ፖሊሲ በሶስት መንገዶች ማለትም በፕላን ተቋማት በኩል፣ በፖሊሲ ማዕቀፍ በኩል እና በባህልና በአመለካከት በኩል በከተማ መሬት ላይ ለግብርናው ሥራ ማነቆ እንዲከሰት ጥርጊያ መንገድ ሊያበጁ ይችላሉ።

### 5.2.1.በፕላን ተቋማት በኩሉ፦

የፕላን ተቋማት በጥቅሉ በፕላን ሥራ ውስጥ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን፣ ተቋማቱ የፕላን ሥራውን የሚሄዱበት መንገድ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሥራ ላይ የሚውሉ የሀብት አይነቶችን ሁሉ ያጠቃልላል። ስለዚህ እነዚህ የፕላን ተቋማት በኢትዮጵያ ለከተማው ግብርና የመሬት ውስንነት እንዲፈጠር እንዴት ሚና እንደሚጫወቱ በሚከተሉት ክፍሎች እናያለን።

*ሀ.የከተማውን ግብርና የመምራት ሃላፊነት፡*

የከተማውን ግብርና ለመምራት፣ ለማገዝ፣ ለመደጎም ብሎም ለመከታተል እና የምርምር ሥራዎችን ለማቀላጠፍ ሃላፊነት ያለው ተቋም በሌለበት ሁኔታ ግብርና ውስብስብ ለሆኑ ቀውሶች የተጋለጠ ይሆናል። ለውጤታማ የአካባቢ ጥበቃ ፕላን ዝግጅትና አስተዳደር እንደዚሁም ለተሟላ አገልግሎት አሰጣጥ በግብርናው ዘርፍ እንዲኖር ሃላፊነት ያለው ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅር እና ተቋማዊ አደረጃጀት መኖር አስፈላጊነትን Bartone etal.(1994:33) በጥናታቸው አረጋግጠዋል። ይሁንና አብዛኛው ታዳጊ አገሮች ውጤታማ የሆነ የአካባቢ ፕላን ዝግጅት እጥረትና እና የአካባቢ ጥበቃ ግቦችን ለማሳካት የጋራ መግባባት ችግር አለባቸው (Ibid ,1994)።

የምስራቅ አፍሪካና የሌሎች አህጉራት ታዳጊ አገሮች ርእሰ ከተሞች ላይ በተደረገ ጥናት የከተማ ፕላን ባለሞያዎች ምላሽ የከተማ ግብርናውን ሥራ ለመምራት፣ ፖሊሲ ለመቅረፅ፣ የግብርና ዞኖችን ለመለዩት፣ ለመመዝገብና ፈቃድ ለመስጠት፣ እንደዚሁም

ክትትል ለማድረግ እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ከሁለት በላይ ሃላፊነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት እንደሚሳተፉበት ያስረዳል (IDRC,1999)፡፡

በእነዚህ አገሮች በተመሳሰይ ሁኔታ በሁሉም ከተሞች የግብርና ዞኖችን መለዬቱ የፕላን ባለሞያዎች ተግባር ሲሆን ለግብርና ሥራ ፈቃድ የመስጠት ሃላፊነት የከተማው አስተዳር ነው፡፡ እንደዚሁም የኤክስቴንሽን አገልግሎት የመስጠቱ እና ክትትልና ድጋፍ ማድረጉ የግብርና መምሪያዎች ሃላፊነት ነው፡፡ ምንም እንኳ ግብርናው በሃላፊነት መጓደል ያጋጠመው ችግር ባይኖርም ግብርናውን ተቀናጅቶ አለመምራት ያለበትን አደጋ ለማዬት የምላሽ ሰጪዎች ፍላጎት አልተንፀባረቀም፡፡

በኢትዮጵያ በተመረጡ ከተሞች (በአዲስ አበባ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በሞጆ፣ በመቀሌ) ከከተማ ፕላን አዘጋጆች እና ከከተማ ግብርና ባለሞያዎች በ2004 በፁሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳዬው ከሌሎች ታዳጊ አገሮች አፈፃፀም ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የከተማውን የግብርና ሥራ ለመምራት፣ ፖሊሲ ለመቅረፅ፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ፣ የግብርና ዞኖችን ለመለዬት እና ለመሳሰሉት በሌሎች ታዳጊ አገሮች እንዳለው ሁሉ በተናጠል ሃላፊነት ያላቸው የመንግስት ተቋማት በተሟላ መልኩም ባይሆንም አንዳሉ የባለሞያዎች ምላሽ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ የከተማ ግብርናውን ለመምራት፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ ለመስጠት ሃላፊነት ያለው የመንግስት ተቋም በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ሲሆን የከተማ ግብርና ሥፍራዎችን የመለዬት ሃላፊነት የከተማ ፕላንና መረጃ ኢንስቲትዩት ድርሻ ነው፡፡ እንደዚሁም የከተማ ግብርና ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ለመቅረፅ ሃላፊነቱ በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የከተማ ግብርና የሥራ ሂደት ነው፡፡ እነዚህም ሃላፊነት ያላቸው የመንግስት ተቋማት የግብርናውን ዘርፍ የአካባቢን ጥበቃ ጨምሮ የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻልና ከተሞች ለኑሮ አመቺ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር በቅንጅት የመስራቱ እና የመምራቱን ሁኔታ የተጠያቂዎች ምላሽ አያሳይም፡፡

### ለ.የህግ እና የፖሊሲ ከለላና ድጋፍ፡

የከተማ ግብርና በፖሊሲ እና በህግ ማዕቀፍ እንዲመራ ማድረግ ለዘላቂ የከተማ ግብርና ልማት የመጀመሪውያና ትልቁ እርምጃ ነው፡፡ በሀገር እና በከተማ ደረጃ የተቀረፀ የከተማ ግብርና ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ በሌለበት ሁኔታ ግብርናን ያካተተ የከተማ ፕላን ፖሊሲ

ውጤታማ ሊሆን አይችልም። በእንዲህ አይነት በሚመራ የከተማ ግብርና ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማና እምነት ያለው ገበሬ ሊኖር አይችልም።

የፕላን ተቋማት በከተማ ግብርናውን እድል ለመወሰን በህብረተሰቡ ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ በጥቅሉ በተቋማዊ አቅም ደረጃ ሊታይ ይችላል። ተቋማዊ አቅሙ የከተማውን ግብርና ለመደገፍ ያለው ብቃት የሚለካው በግብርናው ሥራ ለፖሊሲና ለኤክስቴንሽን አገልግሎት በዋሉ የሰው እና የሌሎች የሀብት አቅርቦታችን ነው።

በአትዮጵያ የከተማ ግብርና የተመለከተ ዝርዝር የፖሊሲና የስትራተጂ ማዕቀፍ በሀገር ደረጃ አለመኖሩ በዚህ ጥናት ውስጥ ከተካተቱት ባለሞያዎች ውስጥ 67% የሚሆኑት የከተማው ግብርና ሁለተኛው ጠንካራ ማነቆ እንደሆነ በሰንጠረዠ-3 የተመለከተው የባለሞያዎች ምላሽ ያሳያል። በተጨማሪም ከተጠያቂዎች የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳዩው ከአዲስ አበባ የከተማ ግብርና ፖሊሲ በስተቀር በሌሎች ከተሞች የከተማ ግብርና ፖሊሲ ሆነ ስትራቴጂ እንደሌላቸው በምላሻቸው አረጋግጠዋል።

የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ በአመዛኙ ለተለያዩ ማነቆዎች የተጋለጠ ነው። ለምሳሌ በመሬት አጠቃቀም ፕላን ወይም በከተማ ግብርና ፖሊሲ አለመኖር ምክንያት የሚከሰቱ ክልከላዎች የዘርፉ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው። ህጋዊ ከለላ በሌለበት ሁኔታ የሚቀጥል የከተማ ግብርና ዘላቂ እና አስተማማኝ ሊሆን አይችልም። ይሁንና የከተማ ግብርና ህጋዊ ከለላ ባይኖረውም የሀብት አጠቃቀም ክትትል ፖሊሲ በሌለበት አገር ዘርፉ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል (Helmore and Ratta, 1995)። እንዲህ አይነቱ የቁጥጥር ማነስ ለከተማው ግብርና መዛመት ዓመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በዳሬሳላም እና በጊኒ ቢሳዎ ተከስቷል።

በኢትዮጵያም ቢሆን የግብርናውን ሥራ በህግ እና በፖሊሲ መደገፍ ዙሪያ አንደኛው ማነቆ መሆኑን የተጠያቂዎች ምላሽ ሲጠቁም በተለይም በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በተለያዩ ምክንያቶች የግብርናው እንቅስቃሴ ክልከላ እንዳጋጠመው አረጋግጧል። የዚህም ክልከላ ምንጭ ግብርናው በከተማ ውስጥ እና ዳርቻ ሲካሄድ የፖሊሲ፣ የህግና የደንብ ከለላ በአፈፃፀም ያላገኘ እንደሆነ ጥርጣሬአቸውን ጠቁመዋል።

## ሐ. የከተሞች የግብርና መሬት እና የግብርና ውጤቶች መረጃ፡

በከተሞች የከተማ መሬት አስተዳደር እየጨነገፈ ያለው በመሬት ይዞታ ላይ ግልፅ መረጃ አለመኖር ነው (Bartone et al. 1994)፡፡ እንዲህ አይነቱ ሪከርድ የፕላን አዘጋጆች በመንግስትና በግል የተያዙ ቦታዎችን መለየት እንዲችሉ፣ ለሊዝ የመሬት ዋጋን መወሰን እንዲችሉ፣ እና ለአነስተኛና ጥቃቅን የከተማ መሬቶች ማን ባለቤት ነው? ማን ነው የሚጠቀምበት? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡ ያለበቂ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የመሬት ግብይት ቁጥጥር ማድረግ አይቻልም፡፡ IDRC በታዳጊ አገሮች ላይ ባደረገው ጥናት አብዛኞቹ የአለማችን ታዳጊ አገሮች የከተማ ግብርና መረጃዎች በአግባቡ እየተያዙ እንዳልሆነ እና በአንዳንዶችም ከተሞች ምንም አይነት መረጃ እንደሌለ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ለምሳሌ በካምፓላ እና በዳሬሳላም ስታትስቲካዊ መረጃዎች በጣም ውስን እንደሆኑ፣ ነገር ግን በጋና ኩማሲ በግብርና ማህበራት ቁጥር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የዶሮ እርባታን የተመለከተና በግብርና ኢኮኖሚክስ ዙሪያ የተለየያዩ መረጃዎች እየተመዘገቡ እንደሆነ ጥናቱ ጠቁሟል (IDRC, 1999)፡፡

የከተማ ግብርና መረጃን በተመለከተ በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ናሙና ከሆኑ ከተሞች የተሰባሰበው የባለሞያዎች ምላሽ እንሚያሳዬው ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በአያንዳንዱ አስፈላጊ ጉዳዮች የሚመዘገቡ መረጃዎች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በሀገሪቱ ከተሞች የሚከተሉት መረጃዎች ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

1. የተሳታፊ ሥርጭት (በፆታ፣ በዕድሜ፣ በኑሮ ደተጃ፣ በማህበር፣ በግል፣ ባለሐብት፣ NGO)፣
2. የከተማ ግብርና የመሬት ሽፋን በእያንዳንዱ የግብርና አይነት፣
3. ግብርናው እየሰጠ ያለው ጥቅም ፡ለአምራቹ እና ለከተማው ህዝብ፣
4. አመታዊ የምርት መጠን በአይነት፣
5. የግብአት ሥርጭት መጠን እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ይሁንና በአዲስ አበባ፣ በአዳማ እና በደብረዘይት የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የከተማ ግብርና የሥራ ሂደት ውስጥ በተወሰኑ የግብርና ጉዳዮች ከጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት አንፃር

መረጃዎች እየተያዙ እንደሆነ ከሶስቱም ከተሞች ከተሰበሰቡ አመታዊ ጥቅል መረጃዎች ተረጋግጧል። በእነዚህ ከተሞች እየተመዘገበ ያለው ጅምር የመረጃ አያያዝ ግብርናው የያዘውን የመሬት ሽፋን በየአይነቱ፣ የይዞታ ዓይነት፣ ግብርናው እየሰጠ ያለው ጥቅም፣ አመታዊ ምርት እና የግብአት ሥርጭት የማያጠቃልል ነው።

### መ. የገንዘብ፣ የአገልግሎት እና የድጋፍ አቅርቦት

ለከተማው ገበሬ የመረጃ አገልግሎት መስጠት፣ የግብርና ግብዓት ማቅረብ፣ የሰርቶ ማሳያ ፕሮግራሞች፣ የብድር አቅርቦት እና የመሳሰሉት ሁሉ የከተማውን ግብርና ለማነቃቃት የሚወሰዱ እርምጃዎች የተቋማዊ መገለጫዎች ናቸው። በታዳጊ አገሮች ከተሞች የተካኼደው ጥናት የከተማ ገበሬዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ፣ የብድር አገልግሎት እና የመረጃ አቅርቦት እጥረት የከተማ ገበሬዎች መሠረታዊ ችግሮቻቸው እንደሆነ የ1999 የIDRC ጥናት ያሳያል።

በሀገራችንም ኢትዮጵያ ከአቅርቦት ጋር በተገናኘ የከተማ ገበሬዎች ችግራቸው ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ከዚህ ጥናት በፊት የአቶ ሞሐመድ በአዲስ አበባ ከተማ ግብርና ላይ የተሠራው ጥናት አረጋግጧል። እንደ ጥናቱ አገላለፅ የከተማ ገበሬ 68.9 እጅ ያህሉ የኤክስቴንሽን ድጋፍ እጥረት ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጠማቸው በአዲስ አበባ ከተማ የተካሔደው የዳሰሳ ጥናት አረጋግጧል።

የዚህ ጥናት ውጤትም የከተማ ግብርናው በባለሞያዎች አለመታገዝ አንዱ መሠረታዊ ችግር እንደሆነ ለይቷል። ለዚህ ጥናት ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የቢሾፍቱና የአዳማ የከተማ ገበሬዎች የድጋፍ አለመኖር አንዱ መሠረታዊ ችግራቸው እንደሆነ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ የአዲስ አበባ፣ የቢሾፍቱ እና የአዳማ የከተማ ፕላን ባለሞያዎች ከ50% በላይ ምላሽ ይህንኑ ሀሰብ የሚያጠናክር ቢሆንም ከ90 እጁ በላይ የግብርና ባለሞያዎች ምላሽ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። ነገር ግን የብድርና የገንዘብ አቅርቦቱ ችግር ለከተማው ግብርና ማነቆ የመሆኑ አቅም አነስተኛ እንደሆነ በሰንጠረዥ 3 እንደምናዬው የባለሞያዎች ምላሽ ያረጋግጣል። በተጨማሪም የገንዘብ አቅርቦት ለሥራቸው ወሳኝ እንደሆነ አስረግጠው የሚናገሩ ገበሬዎች በቅርብ አመታት ውስጥ ግን ችግራቸው እየተቀረፈ እንደሆነ በቃለመጠይቁ የተሳተፉ የከተማ ገበሬዎች ምላሽ ያረጋግጣል።

ሰንጠረዥ 3. የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ዳሰሳ

| ከተሞች | የከተማ ግብርና በመዋቅራዊ ፕላን መካተታቸው | | የከተማ ግብርና ሥፍራ ስታንዳርድ | | የከተማ ግብርና ጥቅሞች መብራራቱ | | የከተማ ግብርና ዓይነቶች ዝርዝር | | የተለያዩ የከተማ ግብርናዎች የት መከናወን እንዳለባቸው ስለመለየቱ | | የአቅርቦቱስ በምን አይነት ሁኔታ?ለማን? | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አለ | የለም | አለ | የለም | አለ | የለም | አለ | የለም | ተለይ ቷል | አልተ ለየም | አለ | የለም |
| ኢታንግ | X | | | X | | X | | X | | X | | X |
| ሮቤ | | X | | X | | X | | X | | X | | X |
| ሺሬ እንዳስላሴ | X | | | X | | X | | X | | X | | X |
| ዜጌ | X | | | X | | X | | X | | X | | X |
| ዘንዘለማ | X | | | X | | X | | X | | X | | X |
| ጋምቤላ | X | | | X | | X | | X | | X | | X |
| አዲግራት | X | | | X | | X | | X | | X | | X |

ምንጭ፡ የዚህ ጥናት የመዋቅራዊ ፕላኖች ዳሰሳ 2004

ከላይ በሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው የከተማ ግብርና በከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ በመሬት አጠቃቀም ድልድል ውስጥ እውቅና እንደተሰጠው ቢገለፅም በሁሉም ፕላኖች ማለት በሚያስችል ሁኔታ የከተማውን የግብርና እምቅ አቅም በመለየት ይኸው እምቅ ሀብት ትኩረት ተሰጥቶት በምን ያህል መጠን፣ ምን ዓይነት ግብርና፣ ግብርናው ዬት፣ የአቅርቦቱስ በምን አይነት ሁኔታ? ለማን? እና የመሳሰሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መልስ ሰጥቶ ወደ ሥራ የሚያስገባ አይደለም፡፡

## 5.2.2.በፖሊሲ ማዕቀፍ

የፖሊሲ ማዕቀፍ የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን እና አስተዳደርን የሚመሩ የፕላን ፖሊሲን፣ የህግና የደንብ ማዕቀፍን ያጠቃለለ ነው፡፡ Maxwell and Armar-Klemesu (1998) የከተማ የህግ እና የደንብ ማዕቀፍ ከመሬት አቅርቦት ጋር ተዳምሮ ዋነኛ የከተማ ግብርና ማነቆ እንደሆነ እነኚሁ አጥኚዎች አረጋግጠዋል፡፡ ፖሊሲ ዋነኛው ችግር የከተማ ግብርናን መርሳት ወይም በትክክል ትኩረት ሰጥቶ አለመተንተን ወይም በከተማ ፖሊሲ ውስጥ ህጋዊነትን ማሳጣት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የከተማው ግብርና ጥግ ይዞ ቆይቷል፡፡ በLado (1990) እንደተመለከተው የኬንያ ፕላን አዘጋጆች የከተማ ግብርናውን በከተማ ፕላን ፖሊሲ ውስጥ ለማጠቃለል ግብርናው በከተማው ፈጣን ዕድገት ተዳምሮ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ፍርሃት እንዳለባቸው ተገንዝቧል፡፡

በኢትዮጵያም በተመሳሳይ ሁኔታ የከተማ ፕላን ፖሊሲ የተመለከተ በከተማ ልማት ፖሊሲ ውስጥ በአንድ አንቀጽ ከቀረበው ውጪ በዝርዝር የቀረበ የከተማ ፕላን ፖሊሲ ባለመኖሩ ለከተማ ግብርና መቀጨጭ አንድ ምክንያት መሆኑ አልቀረም፡፡ በከተማ ደረጃ በከተማ መሬት አጠቃቀም በቅርብ እየተዘጋጁ ያሉ የከተሞች መዋቅራዊ ፕላን የከተማውን ግብርና ያካተተ ቢሆንም ዘርፉ በከተሞች እቅድ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊ ጉዳዮች በዝርዝር እየተብራሩ እንዳልሆነ በመዋቅራዊ ፕላኖች ዳሰሳ ተረጋግጧል፡፡

### 5.2.3. በአመለካከትና ባህላዊ እይታ ችግር

የፕላን አዘጋጆች፣ ውሳኔ ሰጪዎች፣ ዜጎች እና በፕላን ዝግጅት ሚና ያላቸው ማህበረሰቦች ለከተማ ግብርና ያላቸው አመለካከት ግብርናውን ሊያሳድግ ወይም ሊያቀጭጭ ይችላል፡፡ እንደ አንዳንድ የፕላን አዘጋጆች እና ውሳኔ ሰጪዎች አመለካከት ግብርና ትክክል ሆኖ መቀጠል ያለበት በገጠሩ እንጂ በከተማ አይደለም (Mekouar 1997, Binns and Lynch 1998)፡፡ ግብርና በከተማ ውስጥ ህብረተሰቡ ወደ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች በመሳብ ሊያከማች የሚችለውን እድል የሚያዳክም ኋላቀር እንቅስቃሴ ተደርጎም በአንዳንዶች ይታያል፡፡

በታዳጊ አገሮች ባሉ የፕላን ባለሞያዎች ላይ በከተሞች የከተማ ግብርና አስፈላጊነት ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ በተደረገ ጥናት የአብዛው ምላሽ በከተማ ግብርና ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ የእነዚህ ባለሞያዎች ለግብርናው አስፈላጊነት የሚሰጡት ምክንያት ዘርፉ ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ለገቢ ምንጭነት፣ የህብረተሰቡን ኢኮኖሚ ለማሻሻል፣ የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል እና ለአካባቢ ጥበቃ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ነው (IDRC, 1999)፡፡

በሃገራችን ያሉ በዚህ ጥናት የተሳተፉ የፕላን ባለሞያዎች ምላሽ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ እንደ መላሾች አገላለፅ ከንብ እርባታ በስተቀር ሁሉም የግብርና አይነቶች በከተሞችና በከተሞች ዳርቻዎች ቢተገበሩ አግባብነት አለው ብለው ያምናሉ፡፡ ጥቂቶች ባለሞያዎች ደግሞ የከተማ ቆሻሻ ውሃን ዳግም ጥቅም ላይ በማዋል የሚካኼደውን የግብርና እንቅስቃሴ በተለይ ለጓሮ አትክልት ማዋል እጅግ ጎጂ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የግብርና ባለሞያዎችና ገበሬዎቹ ራሳቸው ግብርናው በከተማ ህጋዊ ድጋፍ አግኝቶ

በሥሬው ቢተገበር ለአብዛኛው የከተማ ህዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ ይስማማሉ።

## 5.3.በኢትዮጵያ የከተማ ግብርና ቁልፍ ማነቆዎች

የከተማ ግብርና ልማት ለኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ ኢንዱስትሪ ቢሆንም ዘርፉ በተለያዩ ማነቆዎችና በተዛባ አመለካከት የታጠረ ነው። እንደ ጃክ ስሚትና ሌሎች እይታ ዘርፉ ያለበት እነዚህ ማነቆዎች ቢወገዱለት ግብርናው በመቶ ሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች አስተማማኝ የምግብ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል (Smit et al; 1996: 211)። እነዚሁ አጥኚዎች ግብርናው በተጨባጭ ያለበትን እጥረት የለዩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። የተዛባ ባህላዊና ማህበራዊ የአመለካከት ማነቆዎች፣ ተቋማዊ ማነቆዎች፣ የግብዓትና የአገልግሎት እጥረቶች፣ ከምርት በኋላ በተለይም ለምግብነት በማቀናጀት፣ በገበያ እና በአደረጃጀት ደረጃ የሚከሰቱ ማነቆዎች ጥቂቶቹ ናቸው።
በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የከተማ ግብርና መሠረታዊ ማነቆዎች የመሬት እና ሌሎች ግብአቶች ለምሳሌ እንደ ማዳበሪያ፣ኬሚካሎች፣እና የማምረቻ ማሣሪያ አቅርቦት ችግሮች ናቸው (Drescher et al; 1999: 12)።

በ1999 በአብዛኛው የአፍሪካ አገራት ርዕሰ ከተሞችን ያቀፈው በከተማ ግብርና ማነቆዎች ዙሪያ የICRD የታዳጊ አገሮች ጥናት የዘርፉን መሠረታዊ ማነቆዎችን ለይቷል። የጥናቱም ውጤት መሬትና ከመሬት ጋር የተገናኙ ችግሮች በታዳጊ አገሮች የከተማ ግብርና ቁልፍ ችግሮች እንደሆኑ አረጋግጧል። በዚም ጥናት መሠረት በከተሞች ፈጣን ዕድገት ምክንያት በግብርናው ላይ የሚፈጠሩ ተፅዕኖዎችን ቀዳሚ ችግር እንደሆኑ ጠቁሞ የመሬት አቅርቦት እና የመሬት እጥረት እንደ ቅደም ተከተላቸው ተከታይ ችግሮች መሆናቸው አረጋግጧል።
የሀገራችንም የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ከላይ በተለያዩ አገሮች የታዩ ማነቆዎችን ይጋራል። ለዚህ ጥናት በተመረጡ ከተሞች ያሉ የፕላንና የግብርና ባለሞያዎች ውስጥ የ33 ናሙና ባለሞያዎች ምላሽ የሀገሪቱ ቁልፍ የከተማ ግብርና ማነቆዎችን አሳይቷል። እነዚህ ባለሞያዎች ቀጥሎ በተገለፀው ሰንጠረዥ ውስጥ ከተዘረዘሩ ማነቆዎች ውስጥ ዋና ዋና ማነቆዎችን አምስቱን እንዲመርጡ ተጠይቀው የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ሰንጠረዥ 4. የጥናቱ ናሙና ከሆኑ ባለሞያዎች የተመረጡ የከተማ ግብርና ቁልፍ ማነቆዎች

| ተ.ቁ | የተለዩ ማነቆዎች | የፕላን ባለሞያዎች ምላሽ N=16 | የግብርና ባለሞያዎች ምላሽ N=17 | ድምር የመላሾች N=33 | በ % |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመሬት አቅርቦት/ተደራሽነት ችግር(accessibility) | 10 | 11 | 21 | 69.93 |
| 2 | የመሬት እጥረት(availability) | 7 | 4 | 11 | 36.63 |
| 3 | የመሬት ይዞታ ዋስትና አስተማማኝነት ችግር | 5 | 7 | 12 | 39.96 |
| 4 | የከተማ ግብርና በከተማ መዋቅራዊ ፕላን (የመሬት ክፍፍል) ውስጥ እውቀና ማጣት | 8 | 7 | 15 | 49.95 |
| 5 | የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻርየሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማነስ | 6 | 11 | 17 | 56.61 |
| 6 | የከተማ ግብርናን ለመደገፍ የተሟላ የፖሊሲ የስትራቴጂና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር | 9 | 11 | 20 | 66.6 |
| 7 | የከተማ ግብርናውን ለመምራት ውጤታማ የሆነ ሥርዓት አለመኖር | 3 | 9 | 12 | 39.96 |
| 8 | የከተማ ግብርናን ለመደገፍ በፕሮግራም የሚመራ ቴክኒካዊ አገልግሎት አለመኖር | 8 | 2 | 10 | 33.3 |
| 9 | ለገበሬዎች የማስቻያ የብድር አገልግሎት አለመኖር | 3 | 2 | 5 | 16.65 |
| 10 | የአገልግሎት አቅርቦት አለመሟላት ለምሳሌ የግብአትና የመሳሰሉት | 2 | 6 | 8 | 26.64 |
| 11 | የመሠረተ-ልማት አለመሟላት ለምሳሌ የገበያ ማእከላት፣ የትራንስፖርትና ውሃ የመሳሰሉት | 1 | - | 1 | 3.33 |
| 12 | በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች የመረጃ እና የዕውቀት እጥረት | 1 | - | 1 | 3.33 |
| | ሌላ ካለ ቢገለጽ | - | - | - | - |

*ምንጭ፡ የዚህ ጥናት ዳሰሳ 2004*

ከላይ በሰንጠረዡ ማዬት እንደሚቻለው እንደ ባለሞያዎች ምላሽ በኢትዮጵያ ከተሞች የከተማ ግብርና ቀዳሚው ማነቆ የመሬት አቅርቦት ችግር ነው፡፡ በዳሰሳው ጥናት ከተሳተፉ 33 ባለሞያዎች ውስጥ 21 ባለሞያዎች የመላሾችን 69.93% ያህሉ በዚህ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ተስማምተዋል፡፡ ይህ ማለት በሀገሪቱ ከተሞች ውስጥና ዳርቻ ላይ ያሉ ለሌሎች የልማት ዕቅዶች ሊውሉ የማይችሉ ለግብርና ብቻ ሊውሉ የሚገባቸው ባዶ ቦታዎች ቢኖሩም በቋሚነትም ሆነ በጊዚያዊነት ለግብርናው ስራ እንዲውሉ ፈቃድ አያገኙም ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በሀገራችን ከተሞች ካለው የመሬት ሀብት ውስጥ በየዓመቱ ምንም ዓይነት ጥቅም ሳይሰጥ የሚባክን መኖሩን ያሳየናል፡፡

በኢትዮጵያ ከመሬት አቅርቦት ተከትሎ ለከተማ ግብርና ማነቆ በመሆን ትልቁን ሥፍራ የያዙት፡

1. የከተማ ግብርናን ለመደገፍ የተሟላ የፖሊሲ የስትራቴጂና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር፣

2. የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻር የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማነስ፣ እንደዚሁ ይህ ጥናት ግብርናው አሁን ባለበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ከተሞች በከተማው ግብርና ላይ አነስተኛ ተፅዕኖ ያላቸውን ጉዳዮችንም ጭምር ለይቷል፡፡ ከላይ በሰንጠረዡ ማዩት እንሚቻለው

1. በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች የመረጃ እና የዕውቀት እጥረት፣
2. የመሠረተ-ልማት አለመሟላት ለምሳሌ የገበያ ማእከላት፣ የትራንስፖርትና ውሃ የመሳሰሉት፣ እና
3. ለገበሬዎች የማስቻያ የብድር አገልግሎት አለመኖር

እንደ ቅደም ተከተላቸው በሀገሪቱ በከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ አነስተኛ እንደሆነ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

ይሁንና ከላይ በችግርነት የተጠቀሱ የከተማ ግብርና ማነቆዎች ለወንድና ለሴት ልዩነት በሚፈጥር መልኩ ተፅዕኖ ያደርግ እንደሆን በመጠይቁ ለተሳተፉ ባለሞያዎች ቀርቦ የነበረ ሲሆን ከ60 እጅ በላይ የመላሾች ስምምነት እንደሚያመለክተው የፆታ ልዩነት ተጽእኖ የሌለው መሆኑን ነው፡፡

## 5.4.የከተሞች አስተዳደር ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር

Drakakis-Smith (1997)እስተያየቱን እንደሰጠው የከተማ ግብርና እና የከተማ ፕላን ዝግጅት ቁርኝት የግድ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ሊዋቀር ይገባል፡፡ እንደዚሁ የከተማ ግብርና ሚና ለዘላቂ የከተማ ማህበረሰብ ግንባታ ያለው ፋይዳ ግንዛቤ ሊዳብር ይገባል፡፡ የከተሞች አስተዳደር ለከተማ ግብርና የድጋፍ ደረጃ መለየት በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አስፈላጊ ነው፡፡

1. የህብረተሰቡ አስተዳዳሪዎችና የፕላን አዘጋጆች በከተማቸው ግብርና ማነቆዎች ዙሪያ ያለቸው ግንዛቤ ለማገዝ
2. በከተማ ፕላንና በከተማ ግብርና ላይ የሚመራመሩ ተመራማሪዎች በከተማ ግብርና ዙሪያ በከተሞቻቸው የጋራ ቋንቋ እንዲኖራቸው ለማገዝ

ከተሞችን በዚህ መልኩ መከፋፈል የከተማ ፕላን ዝግጅትና መንግስት እና የከተማ ግብርና ያላቸውን ህብረት ሲያመለክት እንደዚሁም በንጽጽር የከተሞች ለከተማ ግብርና ያላቸውን ድጋፍ በማወዳደር አንዱ ከሌላው በችግር አወጋገድ ዙሪያ ልምድ ቀስሞ የራሱን

እንዲያቅድ ያስችላል። ከዚህ አንፃር ከተሞች ለግብርናው ከሚሰጡት ፈቃድ አንፃር ያላቸውን ደረጃ በአምስት ክፍሎች የለያቸው የIDRC ጥናት በጥናቱ ያካተታቸውን የታዳጊ አገሮች ዋና ከተሞችን በዳሰሳ ጥናቱ እንደሚከተለው ከፍሎአቸዋል።

ሰንጠረዥ 5. በዓለማችን የተለያዩ ከተሞች ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር

| በህግ ፈቅዶ ድጋፍ ጭምር እየሰጠ ይገኛል | ፈቃድ ቢሰጥውም ድጋፍ እያደረገለት አይደለም | ምንም የሚለው የለም (ኒውትራል ነው) | ፈቃድ ቢሰጥም በአፈፃፀም ላይ እምብዛም ነው | በህግ ይከለክላል |
|---|---|---|---|---|
| ዳሬሳላም | ካምፓላ | ስቶክሆልም | ሉሳካ | - |
| ሃራሬ | ኩማሲ | ሆንግ ኮንግ | - | - |
| ናይሪቢ | ደርባን | ፖርት ኦፍ ስፔን | - | - |
| ሲንጋፑር | አክራ | ትሪንዳድ | - | - |
| ኩይዞን ሲቲ | ቶሮንቶ | - | - | - |

**ምንጭ፡** IDRC, 1999

ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ በተለያዩ ከተሞች በጥናቱ የተሳተፉ የፕላን ባለሞያዎች ምላሽ እንደሚያሳየው በአብዛኞቹ ከተሞች ለከተማ ግብርና አስቻይ ሁኔታ መኖሩን እና የትኛውም ከተማ ግብርናን በህግ እንዳልከለከለ ጥናቱ ያሳያል።

በዚህ ጥናት ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የተጠየቁ የግብርና እና የፕላን ባለሞያዎች ከላይ በተቀመጡ በተለያዩ ባህሪያት ከተሞቻቸውን እንዲመድቡ ተጠይቀው የራሳቸውን ግምገማ እንደሚከተለው ሰጥተዋል።

ሰንጠረዥ 6. በኢትዮጵያ በተወሰኑ ከተሞች ለግብርና ያላቸውን ድጋፍ ንጽጽር

| በህግ ፈቅዶ ድጋፍ ጭምር እየሰጠ ይገኛል | ፈቃድ ቢሰጥውም ድጋፍ እያደረገለት አይደለም | ምንም የሚለው የለም (ኒውትራል ነው) | ፈቃድ ቢሰጥም በአፈፃፀም ላይ እምብዛም ነው | በህግ ይከለክላል |
|---|---|---|---|---|
| ቢሾፍቱ | - | ሞጆ | አዲስ አበባ | - |
| - | - | - | መቀሌ | - |
| - | - | - | አዳማ | - |

**ምንጭ፡** የዚህ ጥናት ዳሰሳ 2004

በግምገማቸውም አብዛኛዎቹ ከተሞች ለከተማው ግብርና ፈቃድ ቢሰጡም በአፈፃፀም ላይ እምብዛም እንደሆነ ማወቅ ተችሏል። እንደዚሁም በዳሰሳ ጥናት በተካተቱት ከተሞች በየትኛውም ከተማ ግብርና በህግ ክልከላ እንዳልተደረገበት የተጠያቂዎች ምላሽ ያሳያል።

# ክፍል ስድስት

## 6.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 6.1. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ የከተማ ገበሬዎች በሁሉም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ አብዛኞች ገበሬዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ለእነኝህም የከተማ ገበሬዎች ግብርናው የጤናን እና የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠርና በገቢ ምንጭነት፣ የከተሞችን አካባቢ ደህንነት በማስጠበቅ፣ እና ማህበራዊ ቀውሶችን በማስወገድ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል።

በሀገሪቱ ከተሞችም ለግብርናው አስቻይ እድሎችን የሚፈጥሩ በፌዴራል መንግስት የተቀረፁ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች ቢኖሩም ግብርናው በከተሞች ደረጃ በፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ላይ በብዙ ማነቆዎች የታጠረ እንደሆነ የዚህ ጥናት ውጤት ያሳያል።

በሀገሪቱ ከተሞች ለግብርናው እንቅስቃሴ መሠረታዊ ማነቆዎች ሆነው የተለዩት፣

1. የመሬት አቅርቦት ችግር፣
2. የከተማ ግብርናን ለመደገፍ የተሟላ የከተማ ግብርና ፖሊሲና ስትራቴጂ አለመኖር፣
3. የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻር የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማነስ ናቸው።

እነዚህ ማነቆዎች ቢወገዱ የከተማ ግብርና ዘርፍ በከተሞች ያለውን ድህነት በመዋጋት ከተሞች በአረንጓዴ ልማት የተዋቡ ሆነው ለኑሮ አመቺ እንዲሁኑ በማድረግ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብና አገሪቱ የነደፈችውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ለማሳካት የበኩሉን ድርሻ ይጫወታል። በመሆኑም በሚከተለው ክፍል ውስጥ ለግብርናው አስቻይ እድለሎችን የሚያሰፉ የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል።

### 6.2. በኢትዮጵያ ለከተማ ግብርና ማነቆዎች ሊሰጡ የሚገባቸው የመፍትሔ ምላሾች

**መግቢያ**

ከዚህ ክፍል በፊት የነበረው ክፍል ከፕላን ጋር በተገናኘ ለከተማ ግብርና ያለውን የመሬት ማነቆ እንደዚሁም የፕላን ተቋማት፤ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ እና የህብረተሰቡ አመለካከት

እና ባህል እንዴት በከተማ ግብርና ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው ተመልክተናል። ቀጥሎ በሚኖረን ክፍል ውስጥ ደግሞ ለከተማ ግብርና መስፋፋት ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን በምናስወግድባቸው ሁኔታ መልስ ልንሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እናያለን። የከተማ ግብርና ተዛማጅ ጹሁፎች ያቀረቧቸውን የመፍትሄ ሃሳቦችን እና የዚህ ጥናት ናሙናዎች የሰጡትን የመፍትሔ ሃሳቦች በመቀመር እንደዚሁም ለኢትዮጵያ ከተማ ግብርና ማነቆዎች ለማስወገድ መፍትሔ ናቸው ያልናቸውን ምላሾች ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ።

## 6.2.1.የፕላን ተቋማትን አደረጃጀትና የሃብት ሥርጭትን መለወጥ

ለከተማ ግብርና ኃላፊነት አለመኖር፣ የከተማ ግብርናን በከተማ ፕላን ፖሊሲ እና በሃብት ሥርጭት ድጋፍ ለማድረግ ተገቢውን ዕውቅና አለመስጠት በከተማ ፕላን ተቋማት በኩል የሚታዩ ግልጽ ችግሮች ናቸው። ለእነዚህ ማነቆዎች መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ምላሾች የሚከተሉት ናቸው። የከተማ ግብርናውን ለሚመሩ ተቋሞች ኃላፊነትን በግልፅ በተቀመጠ ስልጣንና ተግባር ማከፋፈል፣ ለከተማ ግብርና የሃብት ሥርጭት ማሳደግ እና የሃብት ክፍፍል ዘዴን ማበጀት፣ የከተማ ግብርና ፖሊሲን መቅረጽ እና የከተማ ግብርና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ማበጀት ናቸው።

### ሀ.በእያንዳንዱ የከተማ ግብርና ጉዳይ ኃላፊነትን ማከፋፈል

የከተማ ግብርናውን የሚመራ ኃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለመኖር ግብርናውን በሚያስተዳደሩ የተለያዩ ተቋማት መካከል እርስ በርስ የሚጋጩ የግብርና ፖሊሲን ሊያስከትል ይችላል። በግልፅ በተቀመጠ ስልጣንና ተግባር ግብርናውን የሚመራ ተቋም ማደራጀት ወይም ኃላፊነትን በግልጽ ማከፋፈል እንደዚሁም በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ ከላይ የተመጠውን ግጭት ሊያስቀር ይችላል።

የከተማ ግብርናውን ለመምራት ኃላፊነት ያላቸው ተቋማት ከግብርና እንቅስቃሴ ጋር ግኑኝነት አላቸው ተብለው የሚገመቱ በተለያየ የአስተዳደር እርከን ላይ ያሉ የጤና፣ የግብርና፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የፕላን እና የአካባቢ ጥበቃ ተቋሞችን የሚያጠቃልል ነው። መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችም ኃላፊነት እንዲኖራቸው ማድረግም ሚዛናዊነትንና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በከተማ ግብርና አስተዳደር ይበልጥ ሊያጎለብት ይችላል። ስለዚህ የከተማ ግብርናውን ለመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት የማስተባበርና የተለያዩ

ተግባሮችን የማከናወን ኃላፊነት የሚቀበሉ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህም ተቋማት ለግብርናው አስፈላጊ የሆኑ የግብአቶችን አቅርቦት ማቀላጠፍ፣ እና ለገበሬዎች ልዩ ልዩ ድጋፎችንና እገዛዎችን የማቅረብ በተመሳሳይ ሁኔታ ክትትልና ግብርናውን በምርምር ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአፍሪካም ሆነ በሌሎች አህጉራት የከተማ ግብርናው ማእከላዊነትን በጠበቀ ሁኔታ ኃላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት በቅንጅት እየተመራ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያም የከተማውን ግብርና ተቀናጅቶ መምራት አንደኛው ማነቆ እንደሆነ የዚህ ጥናት ውጤት ያረጋገጠ ሲሆን ግብርናው የከተሞችን ነዋሪዎች ኑሮ ከመደገፍና እና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የከተሞችን ውበትና የተፈጥሮ አካባቢ ሚዛንን የማስጠበቅ ግብን ሊያሳካ በሚያስችል መልኩ ግብርናውን የጤና፣ የግብርና፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የፕላን እና የአካባቢ ጥበቃ ተቋሞችን ተቀናጅተው የመምራት ሥራ ቢኖር የተሻለ ውጤት ሊገኝ ይችላል፡፡

### ለ.የስልጠናና የግብአት አቅርቦትን ማቀላጠፍ

ግብርናን የሚመሩ ተቋማት ለከተማ ግብርና ያላቸው ድጋፍ የሚገለፀው በምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የተሻሻለ የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦት፣ በቴክኒካዊ ምክር፣ በቋሚና በጊዜያዊ የመሬት አቅርቦት እና በመሳሰሉት የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ በአትዮጵያ የከተማውን ግብርና ለመደገፍ ኃላፊነት የተሰጣቸው የግብርና ተቋማት ቢኖሩም እየተሰጠ ያለው ድጋፍ አለመኖሩን ወይም በቂ አለመሆኑን በዚህ ጥናት ተለይቷል፡፡ ስለሆነም ግብርናውን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የግብርና ባለሞያዎች በተለያዩ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴዎች ዘላቂ በሆነ ሁኔታ በሚከተሉት መንገዶች ድጋፍና ክትትል ቢያደርጉ በከተማ ግብርና የተሻለ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

- ከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማዘጋጀት፣
- በከተማ ግብርና ባሉ መሠረታዊ ልማቶች ላይ ምርምር በማካሄድ አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣
- ጠቃሚ የውጪ አገር ተሞክሮዎችን ለሀገራችን ገበሬዎች ማስተዋወቅ፣
- ለዘርፉ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን በምርምር በመለየት ዘርፉን መደገፍ፣

- ለከተማ ግብርና የሚሆኑ ዞኖችን በመለየት ከሚመለከታቸው የፕላን እና የከተማ አስተዳደሮች ጋር በፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ በቅርብ ተባብሮ መሥራት፣
- በየደረጃው ባሉ ዘርፉን በሚመሩ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ያለውን የሰው ሃይል ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ሥራው እንዲመራ ማድረግ እና መዋቅራዊ አደረጃጀቶችንም ማጠናከር፣
- በአሰራር ላይ ያሉ የአፈጻጸም ክፍተቶችን በጥናት እንዲፈቱ ማድረግ፣ እና
- የግብዓት አቅርቦቶች (የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የአረም፣ የበሽታ እና የተባይ ማጥፊያ ኬሚካል እና የመድሃኒት አቅርቦቶችን) የሚቀላጠፉበትን መንገድ በማበጀት ናቸው፡፡

እነዚህንና የመሳሰሉትን አቅርቦቶች በማቀላጠፍ ምርትንና ምርታማነትን በማሳደግ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል የተጠያቂዎች ምላሽ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል የመሬት አቅርቦት ችግር ለግብርናው ማነቆ ከሆኑ ችግሮች ቀዳሚው እንደሆነ የዚህ ጥናት ውጤት ያረጋገጠ በመሆኑ የሚመለከታቸው የፕላንና የከተማ አስተዳደር ባለሞያዎች ለግብርና ሥራ ሊውሉ የሚገባቸውን ዞኖችን በመለየት በመንግስት የመሬት ማስተላለፍ ህግ መሠረት የግብርና መሬቶች ለገበሬው አቅርቦቱን ማቀላጠፍ የከተሞች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ ዘርፉን መደገፍ ለገበሬዎች ብቻ የመሬት አቅርቦት ማቀላጠፍ በቂ አይደለም፡፡ ለከተማም ሆነ ለገጠሩ ግብርና የግብዓት አቅራቢዎች በመሆን ለግብርናው ሥራ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመኖራቸው እነዚህንም የሥራው ደጋፊዎችን በከተማ የመሬት አቅርቦት ቅድሚያ ሰጥቶ ማስተናገድ ለከተሞችም ሆነ ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት በእጅጉ ጠቃሚ ነው እንላለን፡፡

**ሐ.በከተማ መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ ዕውቅና ሰጥቶ ማሳየት**

የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ ግብርና በመዋቅራዊ ፕላን ዝግጅት ውስጥ ዕውቅና በመስጠት ከሌሎች አገልግሎቶች ይልቅ ለግብርና ልማት ይበልጥ ሊውሉ የሚችሉ የከተማ ዞኖችን በከተማ ፕላኑ ላይ በመለየት ግብርናው ተደራራቢ ጥቅሞችን ሊሰጥ በሚያስችል መልኩ ማቀናጀት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በፓርኮችና በመንገድ ዳርቻዎች ለከተማ ውበት የሚተከሉ ዛፎች የፍራፍሬ ዛፎች እንዲሆን በማድረግ ግብርናውን በፕላን ማነቃቃት ይቻላል፡፡

## መ. የብድር አቅርቦት

በተለያዩ የአፍሪካና የኤስያ ታዳጊ አገሮች የከተማ ገበሬዎች እየቀረበላቸው ባለው የገንዘብ ብድር አቅርቦት በመነቃቃት በግብርናው ያላቸውን ምርታማነት በማሳደግ ከማህበራዊ ጥገኝነት ነፃ እንዲወጡ አስችሎአችዋል። በታንዛኒያ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር የራሳቸውን ህይወት ለመምራት በተገደዱ ሴቶችና ህፃናት የኢንሹራንስ ዋስትና ሽፋን ድጎማ መደረጉ በዳሬሳላም ከተማ ለእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተማማኝ የመኖር ዋስትና እንደሰጣቸው ጥናቶች አሳይተዋል። ከዚህ አንፃር በሀገራችንም የተጀመረው ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የብድር አገልግሎት አቅርቦት ገበሬዎችን በእጅጉ እየጠቀማቸው ያለ መሆኑ በዚህ ጥናት የተረጋገጠ ሲሆን አቅርቦቱ በተጠናከረ ሁኔታ ለሁሉም በግልም በቡድንም በዘርፉ ለተሠማሩ እጥረቱ ላለባቸው ገበሬዎች ጥረታቸው እየተጠና ድጋፉ ቢቀጥል አሁን የተገኘው ውጤትን ዘላቂ ሊያደርገው ይችላል።

## ሠ. በከተሞች ለግብርና የዋሉ የከተማ መሬቶች ይዞታዎችን መረጃ መሰብሰብ

ቀደም ሲል በነበሩት ክፍሎች እንደተገለፀው በኢትዮጵያ የከተማ ግብርናው ለኢኮኖሚው ያለው ጠቀሜታ እና ግብርናው በከተሞች ለነዋሪዎች እየሰጠ ያለው ጥቅም እንደዚሁ የግብርናውን የመሬት ሽፋን ይዞታ እና የመሳሰሉትን በተመለከተ የሚወሰዱ ስታትስቲካዊ መረጃዎች በሌሉበት ሁኔታ የከተማ ግብርና ፖሊሲ መቅረጽ፣ ስለ ጥቅሙ ማውራት እና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አዳጋች ይሆናል። በአንድ ከተማ በከተማ ግብርና ዙሪያ ያለው መረጃ ዘርፉን ለመደገፍ፣ ለመከታተል እና የፕላን ፖሊሲ ለመቅረፅ በጣም አስፈላጊ ነው። የፕላን አዘጋጆች የከተማ ፕላን ፖሊሲ ለመቅረፅ የሚያስችላቸውን ጥናት ሲያካሂዱ ዘርፉ እንደ አንድ ክፍል ታይቶ ጥናት ውስጥ እንዲካተት ለመደረጉ በከተሞች የተጨበጠ መረጃ የለም። የከተማ ግብርና በእንዲህ አይነቱ ጥናቶች መካተቱ የፕላን አዘጋጆች ስለዘርፉ በከተማ ውስጥና በከተማ ዳርቻ የተሟላ ስዕል እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ጥናት የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያጠቃልል ይገባል። ምን ዓይነት የግብርና አይነቶች እየተተገበሩ ነው? የት? ገበሬዎቹ እነማናቸው? (ምሳሌ፦ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የገቢ መጠን) እና ግብርናው ለምን ዓላማ? በተጨማሪም ጥናቱን በከብት እርባታ፣ በዕፅዋት ተክል፣ እና በአበባ ልማት ከፋፍሎ ማካሄዱ እንደአስፈላጊነቱ የተለያየ ፖሊሲ ለመቅረፅ ያስችላል።

ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ የአካባቢውን የመሬት ሃብት መረጃ መኖር ከዘርፉ ጋር የተገናኙ ልማቶችን ለመሳብ በጣም ጠቃሚ ነው (Mlozi 1992)። የአካባቢውን አቅም ማጥናት ለምሳሌ የመሬቱን ምርታማነት እና አካባቢው የሚፈልገውን ምላሽ ማጥናት የፕላን ባለሞያዎች የትኛው መሬት ለየትኛው አገልግሎት መዋል እንዳለበት ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። በዘመናዊ የመሬት መረጃ አያያዝ የታገዘ የቅርብ ጊዜያት የመሬት መረጃ መኖር የፕላን ተቋማት ባዶ የከተማ መሬቶች በጊዚያዊነት ለግብርናው ልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ህብረተሰቡን እና አካባቢውን እንዲያግዙ ያስችላቸዋል።

## ረ.የፕላን አፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ

የሰለጠነ የሰው ሃይል መኖር እና በፕላንና ፖሊሲ ላይ ተከታታይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ማበጀት የከተማ ፕላን ግቦችን ለማሳካት የሚያስችል የፕላን ተቋማት ቋሚ ተግባር ነው (Guberman 1995)። በመሆኑም በከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ላይ ያለውን ለውጥ እና የሚኖሩ እድሎችን መከታተል የከተማ ግብርናውን ከፕላን አንፃር ባገኘው እድል እያሳዬ ያለውን መሻሻል ለማጥናት ያስችላል። ጥናቶቹ ለምሳሌ፡ የከተማ ግብርና ለገቢ ምንጭነት ያለው ሚና፣ ለምግብ አቅርቦት ዋስትና ያለው ሚና፣ እና የከተማ ግብርና በአካባቢ ደህንነት እና በሰው ጤና ላይ ያለው ተፅዕኖ ላይ ክትትልና ግምገማ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። የከተማ ግብርና በከተማውና በከተማ አካባቢ ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ መገምገም በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ጸሐፍት አስፍረዋል። እንዲህ አይነቱ ግምገማ በኢትዮጵያ ከተሞች አለመኖሩን እና በሀገሪቱ ግምገማውን ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎች እየተመዘገቡ ባለመሆናቸው ሥራው እንዳልተጀመረ የተሰባሰቡት ምላሾች ያሳያሉ። በመሆኑም በኢትዮጵያ የዳበረ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የፕላን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ መጀመር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

## ሸ.በከተማ የግብርና ፖሊሲ መቅረጽ

የከተማ ግብርና በፖሊሲ እንዲመራ ማድረግ ለዘላቂ የከተማ ግብርና ልማት የመጀመሪያውና ትልቁ እርምጃ ነው። በሀገር እና በከተማ ደረጃ የተቀረፀ የከተማ ግብርና ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ በሌለበት ሁኔታ ግብርናን ያካተተ የከተማ ፕላን ፖሊሲ

ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ በእንዲህ አይነት በሚመራ ግብርና ውጤታማና እምነት ያለው ገበሬ ሊኖርም አይችልም፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ክፍል በኢትዮጵያ በሀገር ደረጃ የከተማ ግብርናውን እንቅስቃሴ የሚፈቅድ ህግ ቢኖርም የከተማውን ግብርና የሚመራ ፖሊሲ አለመኖሩን የዚህ ጥናት ውጤት ያረጋገጠ በመሆኑ የኢትዮጵያ የከተማ ግብርና ፖሊሲ መቅረፅ ለተሻለ ውጤት ቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡ በከተማም ደረጃ ከአዲስ አበባ በስተቀር በጥናቱ በታቀፉ ከተሞች የከተማ ግብርና ፖሊሲ እንደሌላቸው የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የፖሊሲ አለመኖር የግብርናው ሁለተኛው ግዙፍ ማነቆ በመሆኑ ግብርናውን የሚመሩ የመንግስት ተቋማት እና በከተሞች የከተማ ግብርና የሥራ ሂደቶች ዘርፉን በፖሊሲና በስትራቴጂ ቢመሩት አገሪቱ በዘርፉ የምታገኘውን ጥቅም ወደተሻለ ደረጃ ያሸጋግረዋል፡፡

### 6.2.2. የከተማ ፕላን ፖሊሲ ማዕቀፍን ማሻሻል

በከተሞች እያንዳንዱን የመሬት ክፍል አጠቃቀምን የሚመራ የከተማ ፕላን ፖሊሲ፣ የህግ ማዕቀፍ መኖር ለከተማው ግብርና አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የከተሞችን ዘላቂነት ሊያረጋግጥ የሚችል ለከተማው ግብርና ዕውቅና የሰጠ የከተማ መሬት አጠቃቀም የፕላን ፖሊሲ ለማምጣት ብልሃትን መጠየቁ አልቀረም፡፡ የከተማ ፕላን ዝግጅት በአንድ ከተማ የመሬት አጠቃቀም ውስጥ የትራንስፖርት ወጪን የሚቀንስ፣ ጉልበትን የሚቆጥብ እና የተፈጥሮ የአካባቢ ሚዛንን የሚጠብቅ እና እነዚህን እና የመሳሰሉትን መሠረታዊ የፕላን ግቦችን የሚያሳካ መሆን አለበት፡፡ በኢትዮጵያ እነዚህን የከተማ ፕላን ግቦችን የሚያሳካ የከተሞችን ፕላን ዝግጅት ለማሻሻል ለከተሞች የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይጠቅማል፡፡

#### ሀ.በከተሞች ልማት ፖሊሲ ለከተማ ግብርና ዕውቅና መስጠት

ከተሞች በልማት ፖሊሲያቸው ለከተማ ግብርና ዕውቅና በመስጠት ለከተሞች ዘላቂነት እና ለድህነት ቅነሳ ካለው ጥቅም አንፃር ዘርፉ የሚጫወተውን ሚና የተመለከተ ትንታኔዎችን ማካተታቸው ለዘርፉ እንቅስቃሴ የተሻለ በር ይከፍታል ብለው አንዳንድ ጸሐፍት ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ ዝምባብዌ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዋ የከተሞችን ዘላቂነት የሚያረጋግጥ ቢሆንም ለግብርናው አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥር በብሔራዊ እና በከተማም ደረጃ የፖሊሲ እና የህግ

ማዕቀፍ ቀርፃ እየተንቀሳቀሰች ነው በዚህም ተጠቃሚ ሆናለች። የኢትዮጵያ ከተሞችም የህዝቡንና የአካባቢውን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንፃር ለዘርፉ አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥር በብሔራዊ ደረጃ ካለው የከተማ ልማት ፖሊሲ ጋር የተቀናጀ የየራሳቸው የከተማ ልማት ፖሊሲ መቅረፅ ለዘርፉ ዕድገት የተሻለ በር ይከፍታል። ለግብርናው በር የሚከፍት የከተማ ፕላን ፖሊሲ ሊቀረፅ የሚችለው የፕላን ባለሞያዎች እና ባለስልጣናት ለከተማው ግብርና የሚሰጡት እውቅና ሲኖር ነው። የፕላን ባለሞያዎች ግብርናው ለከተማው ነዋሪዎች የኑሮ ዋስትና አማራጭ በመሆኑ ዘርፉ እየሰጠ ያለውን ጥቅም እውቅና ሊሰጡት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም የከተማ ግብርና የከተማ ፕላን ግቦችን ለማሳካት የሚጫወተውን ድርሻ በከተማ ፕላን ፖሊሲዎች  ዕውቅና ሊያገኝ ይገባል። የከተማ ግብርና በከተማ ፕላን ፖሊሲ ዕውቅና የተሰጠው ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆነው በከተማ ፕላን ፖሊሲ ውስጥ ዘርፉ በግልጽ ተለይቶ በትንታኔ ሲቀመጥ ነው።

## ለ. የከተማ ግብርና ዞን መለየት

የከተማ መሬት ዞን የከተማ ፕላን አዘጋጆች የከተማ መሬት አጠቃቀምን ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት ዋነኛው ዘዴ ሲሆን ይህም የከተማ መሬት አጠቃቀም ላይ ህጋዊነትን እና ዘላቂነትን ያረጋግጣል። ይህም የከተማ ግብርና ግብም ነው። የከተማ ግብርና በፕላን ፖሊሲ ውስጥ በዞን ዕውቅና መስጠት የፕላን ተቋማት በደረጃቸው ውሳኔ ለመስጠት የሚችሉበት አቅጣጫ ነው። በቅርብ ዓመታት እየተዘጋጁ ያሉ የኢትዮጵያ የከተሞች መዋቅራዊ ፕላኖች አንዳንዶች እውቅና እየሰጡ እንደሆነ ቢታወቅም በርካታ ከተሞች ገና መዋቅራዊ ፕላን ያልተዘጋጀላችው በመሆኑ የእነዚህ ፕላኖች ለከተማ ግብርናው እውቅና የሚሰጡ መሆን ይገባቸዋል። የከተማ ግብርና በዞን እውቅና እየተሰጠው በተጨማሪም በርካታ የከተማ መሬቶች ለሌላ ተግባር የተመደቡ ሆነው ለጊዜው ባዶ ሆነው ብዙ ዓመታትን የሚያስቆጥሩ በመሆናቸው እነዚህን ሥፍራዎችንም በጊዜያዊነት ለግብርናው ሥራ እንዲውሉ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ የከተማው ግብርና በዘላቂነት ሊያድግ የሚችለው ከምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ጋር ሲቀናጅ በመሆኑ የከተማ ግብርና በሚተገበርባቸው አካባቢዎች የከተማ መሬትን በሊዝ ለማስተላለፍ በወጣው አዋጅ መሠረት ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ በከተሞች

ፕላን የከተማው ግብርና የመሬት አጠቃቀም ከምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ጋር ተጣጥሞ ቢታቀድ ግብርናው የተሻለ ውጤት ይኖረዋል።

**ሐ.የህግ ማዕቀፍ**

የከተማ መስተዳድር የከተማ ግብርና በከተሞች ለመፍቀድም ለመከልከልም የሚጠቀሙበት መሳሪያ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ሲሆን በዚህ የህግ ማዕቀፍ የትኞቹ የከተማ ግብርና ዓይነቶች በከተማ ውስጥ የትኞቹ በዳርቻ ፈቃድ ሊያገኙ ይገባል? የትኞቹ ደግሞ ፈቃድ ሊሰጣቸው አይገባም? ከሚሉ ጉዳዮች በተጨማሪም ሌሎች የት፣ መች እና በምን ያህል መጠን የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ ህጎችን በማዘጋጀት ሥርዓት ማስያዝ ይገባል።

### 6.2.3. የአመለካከት ለውጥ ማምጣት

የከተማውን ግብርና የማይቀበል አመለካከት ባላቸው ባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ ህዝቡ፣ የፖለቲካ ሰዎችና የፕላን ባለሞያዎች) ግብርናው ጠንካራ ፈተና ሊያጋጥመው ይችላል። ምንም እንኳ በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩ የመላሾች አመለካከት በኢትዮጵያ የፕላን ባለሞያዎች አመለካከት ለከተማው ግብርና ችግር ባይሆንም በአፈጻጸም ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ችግር ከዚህ ጋር ሊገናኝ ስለሚችል የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ለግብርናው ዕድገት ጠቃሚ ይሆናል ።

1. ህዝቡን በከተማ ግብርና ጥቅም ላይ ማስተማር፣
2. በፕላን ዝግጅት ላይ ህብረተሰቡን ያሳተፈ እንዲሆን ማድረግ፣
3. የከተማ ግብርና ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ በየደረጃው ላሉት የአስፈፃሚ አካላትን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
4. የፕላን ባለሞያዎችን በከተማው ህዝብ የኑሮ አማራጭ ላይ ማስተማር እና የሃገሪቱን የከተማ ፕላን ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች ላይ የግንዛቤ መድረኮችን ማዘጋጀት።

## 6.3. በከተሞች ለከተማ ግብርና የሚመከሩ ስፍራዎችና ስታንዳርዶች

### 6.3.1. ለተለያዩ የከተማ ግብርና አይነቶች የመስክ ምርጫ አስፈላጊ መስፈርቶች

በተለያዩ የከተማ ግብርና አጥኚዎች ለተለያዩ የከተማ ግብርና አይነቶች ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉ የግብርና ቦታዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**1.የግለሰብ የጓሮ አትክልት፡**

የዚህ አይነቱ የአትክልት ልማት በሁሉም የከተማ ክልል ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ልማት ለምግብነት የሚያገለግሉትን የፍራፍሬ ዛፍ ተክልን፣ የአበባ ምርትን እና የጓሮ አትክልቶችንና የመሳሰሉትን ምርቶችን ያጠቃልላል፡፡ ይህም የግብርና ዓይነት በግለስብ መኖሪያ ቤት ጓሮ ወይም ጎን እና በቤት ውስጥ በተለያዩ እቃዎች ውስጥ የሚከናወነውን ጭምር ሲያጠቃልል በከተማ ውስጥ የሚገኙ ትንንሽ ባዶ ቦታዎች ላይ በግለሰቦች የሚተገበረውንም የአትክልት ምርትንም ያካትታል፡፡ በቤቶች ግድግዳ ወይም በረንዳ ላይ እና ጣሪያ ላይ የሚከናወኑ ተመሳሳይ የግብርና አይነቶች በዚሁ የሚጠቃለሉ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ግብርና ግን በከተማው አስተዳደር ልዩ ፈቃድ መሰረት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

**2. የህብረተሰብ እና የገበያ የጓሮ አትክልት ልማት**

የህብረተሰብ የጓሮ አትክልት ልማት ማለት ለፍራፍሬ፣ ለጓሮ አትክልት፣ ለአበባ ምርት ልማት እና ለመሳሰሉት ውጤቶች ግለሰቦች በቡድን ተሰባስበው ለግል ወይም ለጋራ ጥቅም የሚያለሙበት የግብርና ቦታ ነው፡፡ በሌላ በኩል የገበያ የጓሮ አትክልት ማለት ለፍራፍሬ፣ ለጓሮ አትክልት፣ ለአበባ ምርት ልማት እና ለመሳሰሉት ውጤቶች ግለሰቦች በቡድን ተሰባስበው ለሽያጭ እና ለትርፍ ዓላማ የሚያለሙበት የግብርና ቦታ ነው፡፡ እነኝህ የግብርና አይነቶች በመኖሪያ አካባቢዎች፣ የቅይጥ የመሬት አጠቃቀም ባሉባቸው አካባቢዎች፣ እና በኢንዱስትሪ ክልሎች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**3. የከብት እርባታ፣ የዶሮ እርባታ እና የንብ እርባታ**

**የከብት እርባታ**

የከብት እርባታ ለምግብነት የሚሆኑትን የለማዳ እንስሳትን ለምሳሌ የቀንድ ከብቶችን፣ የፍየል፣ የበግ፣ የአሳማና የመሳሰሉትን እርባታ ያጠቃልላል፡፡ በከተሞች የከብት እርባታ ሥፍራዎችን ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሜዳማ የሆነ የመሬት አቀማመጥ መኖር፣
2. በቂ የሆነ የውሃ አቅርቦት ያለበት አካባቢ ለምሳሌ ንፁህ ወራጅ ውሃ፣
3. የአየር ፀባዩን መቆጣጠር- ሙቀትን ወይም ቅዝቃዜን ለመስጠት የሚያስችል ቴክኒዮሎጂ፣
4. በቂ የሆነ የከብቶች መኖ አቅርቦት፣ መጋዘን፣ ወዘተ
5. በቂ የሆነ የህክምና አገልግሎት፣
6. በአካባቢው ያለው የአፈሩ አይነት ተስማሚነት፣
7. በቂ የሆነ የሃይል አቅርቦት፣
8. ለምርት አቅርቦት አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎት፣
9. ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ከከብቶች የሚወጡ እዳሪዎች የመኖሪያ አካባቢዎችን የውሃ ሃብት ለብክለት የማያጋልጡ ቦታዎች መሆን እንደሚኖርባቸው፣
10. ከጎረቤት፣ ከዋና መንገድ፣ ከፋብሪካዎች፣ ከመኖሪያ ቤቶች ያለው ርቀት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን እንደሚገባው፣
11. ከጎረቤት መኖሪያ ቤቶች ጋር በተያያዘ የነፋስ አቅጣጫ ግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት፣
12. አዛባዎችን በተገቢው መንገድ ለመያዝ በቂ መሬት መኖር እንደሚገባ፣
13. የገበያ መዳረሻዎች (በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ) መኖር እንዳለባቸው ናቸው፡፡

## የዶሮ እርባታ

የዶሮ እርባታን ለማካሄድ የሚፈልጉ ገበሬዎች የእርባታውን ሥፍራ ሲወስኑ ገበሬዎች ማወቅ ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ይገኙባቸዋል፡፡

1. የአካባቢ ተፅዕኖ ለምሳሌ፡ የውሃ ጥራት፣ ሽታ እና ዝንብ፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ዝግጅት እና የአፈሩ በፎስፈረስ ማዕድን የበለፀገ መሆኑ፣
2. በአካባቢው የአምልኮ ስፍራዎች፣ፓርኮች እና የንግድ ማዕከላት መኖር እንደሌለበት፣
3. ድምፅ ያላቸው ፋብሪካዎች እና ጎዳናዎች ሁኔታ፣
4. ለዶሮ እርባታን የሚከለክሉ ህግና መመሪያዎች መኖር አለመኖራቸው ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ የእርባታውን ሥፍራ ለመወሰን እና የዶሮ ቤት ለመገንባት የዶሮ እርባታ ባለሞያዎች የእርባታ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚያስችሉ የሚከተሉትን መነሻ ነጥቦች አሰቀምጠዋል፡፡

1. ለዶሮ እርባታ የሚመረጡ ቦታዎች የመሬት አቀማመጥ ዝቅተኛ ቦታ ሆኖ የጎርፍ መውረጃ እና ለውሃ የቀረቡ ሥፍራዎች መሆን የለባቸውም፡፡ የዶሮ እርባታ ሥፍራዎች በውሃ ማቆሪያ አካባቢ ወይም ውሃ የሚተኛበት አካባቢ መሆን የለባቸም፡፡
2. የዶሮ ቤቶች ረዘም ብለው ፊት ለፊት እና ጀርባቸው ወይ ወደ ግራ ወይ ወደ ቀኝ ያዞሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በዶሮ ቤቶች መስኮቶች የሚገባውን ቀጥታ የፀሐይ ብርሃን ይቀንሳል፡፡
3. የከተማው የንፋስ አቅጣጫን መለየት የዶሮ እርባታ ሥፍራን ለመወሰን ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዶሮ ቤቶች አካባቢ ወደ መኖሪያ ቤቶች የሚነፍሱ ነፍሳት ቢኖሩ በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ ከፍተኛ ሽታን የሚያመጡ በመሆናቸው የዶሮ ቤቶች በውስጣቸው አየር እንደልብ የሚመላለሱባቸው መሆን አለባቸው፡፡
4. የዶሮ እርባታ የሚካሄድበት ቦታ ከዶሮ ብዛት አንፃር ያሉትን የዶሮ ብዛቶች ሊሸከም የሚችል በቂ መሬት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡
5. የዶሮ እርባታ ስፍራዎችን ከመወሰን በፊት በአካባቢው ያለው ውሃ ለዶሮ እርባታ ተስማሚነቱ መታወቅ ይኖርበታል፡፡
6. የዶሮ እርባታ ሥፍራዎች አስተማማኝ የሃይል አቅርቦቶች ባሉባቸው አካባቢዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. የዶሮ እርባታ ሥፍራ በሩዝ ምርት አካባቢ መሆን የለበትም፡፡
8. የዶሮ እርባታ ሥፍራዎች በበቂ መንገድ ለገበያ የቀረቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
9. ከጎረቤት ቤቶች አንፃር ያለው ርቀት ቀዳሚ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ምክንያቱም ለጎረቤት ቤቶች የቀረቡ የዶሮ ቤቶች የጎረቤት ተቃውሞ የሚያስነሳና ለግጭት የሚጋብዝ በመሆኑ የእርባታው ቤት ከመገንባቱ በፊት ከጎረቤት ጋር ውይይት ሊደረግ ይገባል (Charles Goan,---) ፡፡

**የንብ እርባታ**

የንብ እርባታ ስፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉት ነጥቦች ማየት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ የዘርፉ አጥኚዎች ያስረዳሉ፡፡

1. የንብ ማነቢያ ስፍራዎች ለንቦች በቂ የሆነ የምግብ አቅርቦት ያለው መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ አበባ፣ አቦካዶ፣ ብርትኳን፣ ትርንጎ፣ የባህርዛፍ፣ ቴምር እና የመሳሰሉት ዛፎች፤

2. አካባቢው ለንቦች ንፁህ ውሃ ያለው መሆን ይኖርበታል፤
3. የንብ ማነቢያ ስፍራዎች ለመንገድ ትራንስፖርት አቅርቦት የቀረቡ መሆን አለባቸው፤
4. የንብ ማነቢያ ስፍራዎች በቂ ዝናብ ያለው መሆን አለበት። አመታዊ የዝናብ መጠኑ በአማካይ እስከ 1250 ሚ.ሜ. የሚደርስ መሆን አለበት፤
5. የማነቢያ ስፍራዎች ከጭስ፣ ከእሳት እና ከሌሎች አደጋዎች የራቁ መሆን አለባቸው፤
6. የንብ ማነቢያ ስፍራዎች ውሃ የማይቋጥሩ ደረቅ ሥፍራዎችና ከረግረጋማ ስፍራዎች የራቁ መሆን አለባቸው፤
7. ከመጫዎቻ እና ከፍተኛ ድምፅ ካላቸው ለምሳሌ ከኢንዱስትሪና ከንግድ ሥፍራዎች የራቁ መሆን አለባቸው
8. የንብ እርባታ ሥፍራዎች ሰዎች ከሚገኙባቸው አካባቢዎች የራቁ መሆን አለባቸው (Department of Agriculture of RSA, US No: 116309)።
9. የሰብል እርሻ ባሉባቸው አካባቢዎች የፀረ አረም፣ ጸረ ተባይ እና ማዳበሪያ በስፋት ጥቅም ላይ በሚውሉባቸው አካባቢዎች የዘመናዊ የንብ እርባታ ማዕከል ከእርሻ ቦታ ያለው ርቀት ከ5 ኪሎ ሜትር በላይ መሆን አለበት።

## 5. በከተሞች የደን እና የፍራፍሬ ዛፎች ሥፍራዎች

በከተሞች ውስጥና አካባቢ የደን እና የፍራፍሬ ዛፎች በሚከተሉት ሥፍራዎች ቢለሙ ተመራጭ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ይመክራሉ (Beatley, 2002 & Paul DE GRAAF Ir and Jan)።

1. የከተማው ዙሪያ ክልሎች የደን ዛፎች ሥፍራዎች እንዲሆኑ ቮን ቱነን ይመክራል፤
2. ዝቅተኛ የህዝብ ክምችት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የወንዝ ዳርቻዎችና የጎርፍ መውረጃዎች፣ ሃይቅ ዳርቻዎች እና ተዳፋትነት ያላቸው መሬቶች፤
3. በተለይ ለተዳፋታማ ቦታዎች ተስማሚ የሚሆነው የከተማ ግብርና አይነት የአፈሩን መሸርሸር እና ሙቀትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የደን እና የአትክልትና ፍራፍሬ ዛፎች ልማት ናቸው።
4. የዘላቂ ማረፊያ ሥፍራዎች፤
5. የመንገድ አካፋይ፣ ዳርቻ እና የመንገድ ዳር ፓርኮች፤
6. የፕላዛ እና ክብረበዓል ቦታዎች፤
7. የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ እና የመሳሰሉት ናቸው።

## 6.3.2. የግብርና ስፍራዎች መነሻ ስታንዳርድ

**1.የግለሰብ የጓሮ አትክልት፡** የዚህ አይነቱ የአትክልት ልማት በሁሉም ዞኖች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሲሆን ምንም ዓይነት ሽታ ወይም ተፅዕኖ በአካባቢው ነዋሪ ላይ የማያስከትል መሆን አለበት፡፡ በቤቶች ግድግዳ ወይም በረንዳ ላይ እና ጣሪያ ላይ የሚከናወኑ ተመሳሳይ የግብርና አይነቶች በዚሁ የሚጠቃለሉ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ግብርና ግን በከተማው አስተዳደር ልዩ ፈቃድ መሰረት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ በከተማው አስተዳደር ይህንን ጉዳይ የሚከታተለው የህንፃውን ጥንካሬ ፈትሾ ግብርናውን ሊሸከም የሚችል መሆኑን ሲያረጋግጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡

**2.የህብረተሰብ እና የገበያ የጓሮ አትክልት**

እነኝህ የግብርና አይነቶች በመኖሪያ አካባቢዎች፣ ቅይጥ የመሬት አጠቃቀም ባሉባቸው አካባቢዎች፣ እና በኢንዱስትሪ ክልሎች የሚከተሉትን መስፈርቶችን ሲያሟሉ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. በአካባቢው ላይ የአየር እና የውሃ ብክለት የማያስከትሉ ከሆነ፣
2. የአካባቢውን ውበት የማያበላሽ ከሆነ፣
3. የቆሻሻው ልቀት በአግባቡ የሚያዝ ከሆነ ነው፡፡

**3.የከብት እርባታ፣ የዶሮ እርባታ እና የንብ እርባታ**

የከብት እርባታ፣ የዶሮ እርባታ እና የንብ እርባታ በከተማ ክልል ውስጥ ለዚሁ ግብርና በተፈቀደው ዞን ብቻ ተወስኖ በመኖሪያ ቤቶች እና በሌሎች ዞኖች በከተማው አስተዳደር ልዩ ፈቃድ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና እነዚህ የከተማ ግብርና ተግባራት በከተማ ክልል ውስጥ ሲከናወኑ ከዚህ ቀጥሎ በሚገለፀው ስታንዳርድ የመሬት መጠን መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 1.የቀንድ ከብት እርባታ

ሰንጠረዥ 7. የቀንድ ከብት እርባታን ለማካሔድ የሚያስፈልግ የወለል መጠን ስታንዳርድ በከብቶች ዝርያ

| የከብት ዝርያ | የከብቱ ዓይነት | ለአንድ ከብት የሚያስፈልግ የወለል መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ርዝመት (ሜ) | ስፋት (ሜ) | ፍሳሽ ማስወገጃ ስፋት ሳንቲሜትር | በወይና ደጋ የግድግዳው ርዝመት (ሜ) | የሰራተኛ መዘዋወሪያ (ሜ) | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት በመቶኛ | የመመገቢያ መጠን (ሳ.ሜ) | የውሃ ገንዳ መጠን (ሳ.ሜ) |
| Friesian crosses | የወተት ላም | 2 | 1.20 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*30 | 40*30 |
| | ጊደር | 1.75 | 1.10 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 30*25 | 40*25 |
| | ጥጃ | 1 | 1.0 | 40 | 1.70 | 1.70 | 2 | 25*20 | 30*20 |
| | ኮርማ | 2.10 | 1.30 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*40 | 40*35 |
| Jersey crosses | የወተት ላም | 1.75 | 1.10 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*25 | 40*25 |
| | ጊደር | 1.70 | 1.05 | 40 | 1.70 | 1.70 | 3 | 30*25 | 40*25 |
| | ጥጃ | 1. | 1.0 | 40 | 1.70 | 1.70 | 2 | 25*20 | 40*25 |
| | ኮርማ | 2.05 | 1.25 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*40 | 40*35 |
| Simmental crosses | የወተት ላም | 2.05 | 1.25 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*35 | 40*30 |
| | ጊደር | 1.80 | 1.15 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 30*30 | 40*30 |
| | ጥጃ | 1.05 | 1.0 | 40 | 1.70 | 1.70 | 2 | 30*25 | 30*25 |
| | ኮርማ | 2.15 | 1.35 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*40 | 40*35 |
| Smallsize Zebu crosses | የወተት ላም | 1.75 | 1.10 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 30*25 | 40*30 |
| | ጊደር | 1.70 | 1.05 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 30*25 | 40*25 |
| | ጥጃ | 1.0 | 1.0 | 40 | 1.70 | 1.70 | 2 | 25*20 | 30*20 |
| | ኮርማ | 2.0 | 1.20 | 40 | 2.50 | 1.70 | 3 | 40*30 | 40*30 |

**ምንጭ፡** Kenneth Russell (1969), MOA,).

### ሰንጠረዥ 8. የወለል መጠን ስታንዳርድ በወተት ከብቶች የደም መጠን አንጻር

| የደም መጠን | የከብቱ ዓይነት | ለአንድ ከብት የሚያስፈልግ የወለል መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ርዝመት (ሜ) | ስፋት (ሜ) | ፍሳሽ ማስወገጃ ስፋት ሳንቲ ሜትር | በወይና ደጋ የግድግዳው ርዝመት (ሜ) | መኖ መስጫና የሰራተኛ መዘዋወሪያ (ሜ) | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት በመቶኛ | የመመገቢያ መጠን (ሳ.ሜ) | የውሃ ገንዳ መጠን (ሳ.ሜ) |
| Large size Zebu Local | የወተት ላም | 1.80 | 1.10 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*35 | 40*35 |
| | ጊደር | 1.75 | 1.10 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 35*30 | 40*30 |
| | ጥጃ | 1.0 | 1.0 | 1.75 | 1.75 | 30 | 2.5 | 30*25 | 35*25 |
| | ኮርማ | 2.05 | 1.25 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*35 | 40*30 |
| 75% በላይ የፍሪዝያን ዲቃላ | የወተት ላም | 2.10 | 1.25 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 45*35 | 40*30 |
| | ጊደር | 1.80 | 1.25 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*35 | 40*30 |
| | ጥጃ | 1.10 | 1.0 | 1.75 | 1.75 | 30 | 2.5 | 25*20 | 30*20 |
| | ኮርማ | 2.15 | 1.35 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*40 | 40*35 |
| 75% በላይ የጀርሲ ዲቃላ | የወተት ላም | 1.80 | 1.10 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*25 | 40*25 |
| | ጊደር | 1.75 | 1.10 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 30*25 | 40*25 |
| | ጥጃ | 1.0 | 1.0 | 1.75 | 1.75 | 30 | 2.5 | 25*20 | 40*25 |
| | ኮርማ | 2.10 | 1.25 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*40 | 40*35 |
| 75% የስመንታል ዲቃላ | የወተት ላም | 2.15 | 1.15 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*35 | 40*30 |
| | ጊደር | 1.85 | 1.10 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 30*30 | 40*30 |
| | ጥጃ | 1.10 | 1.0 | 1.75 | 1.75 | 30 | 2.5 | 30*25 | 30*25 |
| | ኮርማ | 2.20 | 1.40 | 2.50 | 2.0 | 30 | 3.0 | 40*40 | 40*35 |

**ምንጭ፡** Kenneth Russell (1969), MOA, Amaha Kassahun (1989).

ሰንጠረዥ 9. ለሚደልቡ ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን ስታንዳርድ በከብቶች ዝርያና በእድሜ

| የወንድ ከብቶች ዝርያ | የቦታው ዓይነት | ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን በዕድሜ (ካ.ሜ) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3-5 ዓመት | 6-8 ዓመት | 10- 12 ዓመት |
| ቦረና | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 2*1.20 | 2.10*1.30 | 2.20*1.30 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.50*2.0 | 1.60*2.0 | 1.70*2.0 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 5.8 | 6.0 | 6.2 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት(%) | 2 | 2.5 | 2.5 |
| ሆሮ | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 1.95*1.15 | 2.0*1.20 | 2.0*1.25 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.65 | 0.40*0.40*0.65 | 0.40*0.40*0.70 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.45*1.95 | 1.55*1.95 | 1.65*2.0 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 5.5 | 5.8 | 6.2 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት(%) | 2 | 2.5 | 2.5 |
| አርሲ | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 1.90*1.15 | 1.95*1.15 | 2*1.20 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.65 | 0.40*0.40*0.65 | 0.40*0.40*0.65 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.40*1.90 | 1.50*1.90 | 1.60*2.0 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 5.3 | 5.5 | 6.0 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት(%) | 2 | 2.5 | 2.5 |

**ምንጭ፡** Kenneth Russell (1969), MOA, Amaha Kassahun(1989).

## ሰንጠረዥ 10. ለሚደልቡ ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን ስታንዳርድ በከብቶች የደም መጠንና በዕድሜ

| የወንድ ከብቶች ዝርያ | የቦታው ዓይነት | ከብቶች የሚያስፈልግ የወለል ስፋት መጠን በዕድሜ (ካ.ሜ) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2-3 ዓመት | 4-5 ዓመት | 6-7 ዓመት |
| 50% የፍሪዥያን ዲቃላ | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 2.05*1.20 | 2.10*1.25 | 2.15*1.30 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.55*2.0 | 1.60*2.0 | 1.65*2.05 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 6.0 | 6.2 | 6.6 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት (%) | 2 | 2.5 | 2.5 |
| 50% የጀርሲ ዲቃላ | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 2*1.20 | 2.05*1.25 | 2.10*1.25 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.55*2.0 | 1.65*2.10 | 1.70*2.15 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 5.9 | 6.5 | 6.7 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት (%) | 2 | 2.5 | 2.5 |
| 50% የስመንታል ዲቃላ | ለመቆሚያ የሚሆን ቦታ | 2.10*1.25 | 2.15*1.30 | 2.20*1.30 |
| | የመመገቢያ ገንዳ | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 | 0.40*0.40*0.70 |
| | ለሽንትና ለአዛባ መፍሰሻ | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| | ለመዝናኛ እና ውሃ ማጠጫ | 1.60*2.10 | 1.65*2.15 | 1.70*2.20 |
| | የሚያስፈልግ ጠቅላላ ስፋት | 6.4 | 6.7 | 7.0 |
| | መኖ ማከማቻ | 5*4 | 6*5 | 7*6 |
| | የከብቶች መቆሚያ ተዳፋትነት (%) | 2 | 2.5 | 2.5 |

**ምንጭ፡** Kenneth Russell (1969), MOA, Amaha Kassahun (1989).

ምስል. 5 ዘመናዊ የከብት እርባታ በረት



ምንጭ፡ አዲስ አበባ የከተማ ግብርና (2004 ዓ.ም)

- የታመሙ ከብቶችን ማግለያ ስፍራ የሚያስፈልገው ስፋት ለአንድ ከብት በካሬ ሜትር 3 ሜ*2ሜ ሆኖ በጠቅላላው 6 ካሜ ነው
- አንድ ኮርማ በረት ውስጥ ለማዋል እና ለማሳደር 3 ሜትር * 4ሜትር በጠቅላላው 12 ካ.ሜ ያስፈልጋል

የቀንድ ከብት እርባታን ለማካሄድ የሚያስፈልግ የግብአትና የምርት ማከማቻ ቦታ ስታንዳርድ፡

1. የግብዓት ቦታ ወይም መጋዘን
   - አንድ ኩንታል የተመጣጠነ መኖን ለማከማቸት 0.2 ሜትር ኩብ ቦታ ያስፈልጋል፤
   - አንድ ኩንታል በቦንዳ የታሰረ ድርቆሽ ለማከማቸት 0.7 ሜትር ኩብ ቦታ ይፈልጋል፤
   - አንድ ኩንታል ብትን ያልታሰረ ድርቆሽ ለማከማቸት 1.6 ሜትር ኩብ ቦታ ያስፈልጋል፤
   - አንድ ኩንታል የተቀረጣጠፈ ድርቆሽ ለማከማቸት 0.6 ሜትር ኩብ ቦታ  ያስፈልጋል፤
   - አንድ ኩንታል ጭድ ወይም ገለባ በቦንዳ ያልታሰረ ለማከማቸት 3.0 ሜትር ኩብ ቦታ ያስፈልጋል፤
   - አንድ ኩንታል ጭድ ወይም ገለባ በቦንዳ የታሰረ ለማከማቸት 0.7 ሜትር ኩብ ቦታ ያስፈልጋል፤

2. የምርት ማከማቻ ቦታ(Dairy products store) ወተት ከታለበ በኋላ በወተት ማከማቻ ወይም ማጠራቀሚያ ማቀዝቀዣ ማጠራቀም ያስፈልጋል።

**ሰንጠረዥ 11. የምርት ማከማቻ ቦታ**

| የወተት ምርት በሊትር | የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት በሜትር |
|---|---|
| ከ100 በታች | 3.7 * 3 ካ.ሜ. |
| ከ100 እስከ 200 | 3.7 * 3.7 ካ.ሜ. |
| ከ200 እስከ 450 | 3.7 * 4.4 ካ.ሜ. |
| ከ450 እስከ 700 | 3.7 * 5.1 ካ.ሜ. |

**ምንጭ፡** አምሃ ካሳሁን (1989 ዓ.ም)

***2. ለበግ እና ፍየል***

ሰንጠረዥ 12. የበግ እና የፍዬል እርባታ መጠለያ የውስጥ ስፋት መጠን

| ለአንድ በግ ወይም ፍዬል | የወለል ስፋት | የመመገቢያ ቦታ ስፋት እና ርዝመት በሳ. ሜ. | የውሃ ገንዳ ስፋትና ርዝመት በሳ.ሜ | የመኖ ማከማቻ በካ.ሜ | የታመሙ ማግለያ ስፋት በካ.ሜ. |
|---|---|---|---|---|---|
| ለቁብ በግ ወይም ፍዬል | 1.1 ካ.ሜ. | 30- 40 | 25 * 35 | 6 | 1.20 * 0.70 |
| ለእናት በግ/ፍዬል | 1.5 ካ.ሜ. | 30-40 ሳ. ሜ. | 35 * 35 | 6 | 1.30 * 0.80 |
| ለግልገል | 0.3-0.5 ካ.ሜ | 20-30 ሳ. ሜ. | 30 * 25 | 6 | 1.10 * 0. 70 |
| ለአውራ በግ/ፍዬል | 2.8- 3 ካ.ሜ | 30-40 ሳ.ሜ. | 35 * 30 | 12 | 1.30 * 0.80 |

**ምንጭ፦** USAID (2002) and EIAR (2012)

ምስል. 6 የበግ እና የፍየል እርባታ



ምንጭ፡ አዲስ አበባ ከተማ ግብርና (2004ዓ.ም)

በአጠቃላይ ማንኛውም የእንስሳት እርባታ ሽታን፣ የድምፅ ብክለትን፣ ትንኞችን እና የመሳሰሉትን በከተማ ክልል ውስጥ በማያስከትሉ ሁኔታ መካኼድ አለባቸው። የማረጃ ስፍራዎችም እንደዚሁ ለዚሁ ተግባር በተፈቀዱ ክልሎች ብቻ መካሔድ አለባቸው።

**3.የዶሮ እርባታ** ፡ የከተማ አካባቢዎች ንፅህናቸው የተጓደለ፣ ለጤና ተስማሚ ባልሆኑ ሽታዎች እንዳይበከሉ ለመከላከል የዶሮ እርባታ ስፍራዎችን ማጤን ተገቢ ነው። በዚህም ምክንያት በከተሞች የሚደረጉ የዶሮ እርባታዎች በሚከተሉት አግባብነት ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ (Ohio Model, 2009)።

ለእርባታው ከተፈቀደው ክልል ውጪ የሚደረግ እርባታ በከተማው አስተዳደር ፈቃድ በሚከተለው አግባብነት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

1. ሁሉም የዶሮ ቤቶች በበቂ ሁኔታ የተከደኑ መሆን ይኖርባቸዋል፣
2. የዶሮ ቤቶች ንፁህ እና በቂ አየር ያላቸው መሆን አለባቸው፣
3. የዶሮ ቤቶች ሽታ የሌላቸው እና ትንኞች የማይታይባቸው መሆን አለባቸው።

የዶሮ እርባታ የሚካሄድባቸው የዶሮ ቤቶች ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከንብረት መስመሮች፣ ከህዝብ ማስተናገጃ ስፍራዎች፣ ከህዝብ መንገዶች እና ከመሳሰሉት ያለው ርቀት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ሰንጠረዥ 13. የዶሮ ማራቢያ ስፍራዎች ርቀት**

| የዶሮ ማርቢያ ስፍራዎች ርቀት | የዶሮ ማርቢያ ስፍራዎች ርቀት በጫማ | የዶሮ ማርቢያ ሥፍራዎች ርቀት በሜትር |
|---|---|---|
| ከመኖሪያ ቤት | - | 10 |
| ከንብረት መስመር | 100 | 30.4 |
| ከትምህርት ቤትs፣ከቤተ ክርስቲያን፣ከፓርክ ፣ከህዝብ መስተናገጃ ቦታዎች | 1500 | 50 |
| ከህዝብ መመላለሻ መንገዶች | 150 | 45.6 |
| ከውሃ ምንጭ | 100 | 30.4 |
| ከግለሰብ የውሃ ጉድጓድ | 100 | 30.4 |
| ከህዝብ የውሃ ጉድጓድ | 500 | 152 |
| ከጎርፍ መውረጃ መንገዶች እና ከረግረግማ ቦታዎች | 100 | 30.4 |

**ምንጭ፡** (Charles Goan,----)

**ሰንጠረዥ 14. ለዶሮ እርባታ የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት**

| የዶሮ ዝርያ አይነት | ዕድሜ | የቦታ ፍላጎት በአንድ ካሬ ሜትር |
|---|---|---|
| የእንቁላል ጣይ | ከጫጩት እስከ ሶስት ወር | 10 — 12 ዶሮ |
| የእንቁላል ጣይ | ከ 3 ወር - 5 ወር | 8 — 10 ዶሮ |
| የእንቁላል ጣይ | ከ 5 ወር በላይ | 5 — 6 ዶሮ |
| የሥጋ ዶሮ | ከጫጩት - 2 ወር | 10 — 12 ዶሮ |

**ምንጭ፦ ዶ/ር አለሙ ያሚ** (2001)

ምስል. 7 የዶሮ እርባታ



ምንጭ፡ አዲስ አበባ ከተማ ግብርና (2004ዓ.ም)

ምስል. 8 ዘመናዊ የዶሮ እርባታ



ምንጭ፡ አዲስ አበባ ከተማ ግብርና (2004ዓ.ም)

4.የንብ እርባታ ፦ ለንብ እርባታ ከተፈቀደው ክልል ውጪ ለሚደረግ እርባታ በከተማ አስተዳደር ልዩ ፈቃድ በሚከተሉት አግባብነት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል (Ohio Model, 2009)

ሀ. በመኖሪያ ዞን ውስጥ፦ በመኖሪያ ክልል ውስጥ የሚደረግ እርባታ በሚከተሉት አግባብነት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

1. ከ220 ካሬ ሜትር የመሬት ስፋት በታች ባለው ቦታ ምንም አይነት የንብ እርባታ ሊካሄድ አይገባም። ምክንያቱ ንቦች ከመጥፎ ጠረን፣ ከእሳት እና ከጭስ መራቅ ያለባቸው በመሆኑ።
2. ከመኖሪያ ቤት የመሬት ክልል ከ10 ሜትር በቀረበ ክልል ውስጥ ምንም የንብ እርባታ መካኼድ የለበትም።
3. የንብ ማንቢያ ቤት በጠንካራ አጥር የተከለለ መሆን አለበት
4. ንቦች ውሃ ፍለጋ ሲሉ በአቅራቢያው ባሉ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ወይም የሰዎችን መዝናኛ ቦታዎች እንዳይወሩ በማነቢያ ስፍራዎች በቂ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል።

ለ. ከመኖሪያ ዞን ውጪ ሲሆን፦ ከመኖሪያ ክልል ውጪ የሚደረግ የንብ እርባታ በሚከተሉት አግባብነት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

1. ከ92 ካሬ ሜትር የመሬት ስፋት በታች ባለው ቦታ ምንም አይነት የንብ እርባታ ሊካሄድ አይገባም።
2. በ92 ካሬ ሜትር የመሬት ስፋት አንድ የንብ ማነቢያ ቀፎ ሊኖር ይገባል። ከአንድ የንብ ማነቢያ ቀፎ በላይ ሲሆን በዚሁ ንፅፅር ተግባራዊ ይሆናል
3. ለመኖሪያ ዞን ለመሬት መጠን ከተጠቀሰው ውጪ የተጠቀሱት ሁሉም መመሪያዎች ከመኖሪያ ዞን ውጭ ላሉትም ያገለግላሉ

ለንቦች ማነቢያ የሚያገለግል የንቦች ጋጣ ለመሥራት የቦታ ስፋት

በአ.አ. የካ የከተማ ግብርና ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሰረት ለአንድ ዘመናዊ የንብ ቀፎ የሚያስፈልግ የቦታ መጠን በተመለከተ ስፋት- 150 ሳ.ሜ፣ ርዝመት- 200 ሳ.ሜ. እና ቁመት- 70 ሳ.ሜ. መሆን ይገባዋል።

ምስል. 9 ዘመናዊ የንብ እርባታ



ምንጭ፡ አዲስ አበባ ከተማ ግብርና (2004ዓ.ም)

## ዋቢ መፃህፍት


አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር (1995) .የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ

_______ (2004). የከተማ እና ከፊል ከተማ ግብርና ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ሰነድ.

የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት(2000). የኢትዮጵያ በግ እና ፍዬል ምርታማነት ማሻሻያ ፕሮግራም

አለሙ ያሜ (ዶ/ር) (2001). ዘመናዊ የዶሮ እርባታ ማንዋል

አምሃ ካሳሁን (1989 ዓ.ም). ዘመናዊ የወተት ከብቶች እርባታ

*ዴቪድ ሀችሰን (2006). የኢትዮጵያ ሰኒታሪ ደረጃዎች እና የእንስሳና ሥጋ በገበያ ፕሮግራም*

*ኢፌዴሪ* (1995) . የኢትዮጵያ ህገመንግስት

_______( 1999). የከተማ ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከልኮሚ

_______ *(1999).* የከተሞች ኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅ

_______ (2000).ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፤አዋጅ ቁጥር 574/2000

_______ (2003) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ፖሊሲ፤ የአፈፃፀም ስልቶችና የአቅም ግንባታ ማዕቀፎች

_______ (2004). የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስያዝ የወጣ አዋጅ

*ከልኮሚ ( 2003)* .የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ፣የድጋፍ ማእቀፍና የአፈፃፀም ስልቶች

_____(1998). የኢትዮጵያ ከተማ ልማት ፖሊሲ

_____ (2003). ክፍለኢኮኖሚ የአምስት አመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ

______ (2004). የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የአረንጓዴ ልማትና ውበት ስትራቴጂ (ያልፀደቀ)

*ደሳለኝ ገ/መድህን (1997). የወተት ከብት እርባታ የተግባር መመሪያ*

Aipira, Hoffman. (1995) “Urban Farming: Making Africa’s Cities Sustainable.” Ecodecision 15 (Winter 1995): 83-86. and Management in the Developing World, Longman, New York.

Anderson, Larz T. (1995) Guidelines for Preparing Urban Plans. Chicago: American Planning Association. +231pp.

Available at http://www.foodsecurity.org/PrimerCFSCUAC.pdf; accessed 8 March 2004.

Axumawit G. Egziabher, Memon PA, Mougeot L, Lee-Smith D, Maxwell D and Sawio C. 1994. Cities feeding people: an examination of urban agriculture in East Africa. Ottawa: IDRC.

Bartone, Carl, Janis Bernstein, Josef Leitmann and Jochen Eigen. (1994) Toward Environmental Strategies for Cities: Policy Considerations for Urban Environmental Management in Developing Countr ies. Washington: World Bank. Report 18, Urban Management Programme.

Beatley, Timothy. 2000. *Green Urbanism: Learning from European Cities.* Washington D.C.: Island Press.

Binns, Tony and Kenneth Lynch. (1998) "Feeding Africa's Growing Cities into the 21st Century: The Potential of Urban Agriculture." Journal of International Development 10:777-793.

Bunnell, Gene. 2002. Making Places Special. Chicago: Planner's Press

Canada Government (1999). Feeding the City from the Back 40: A Commercial Food Production Plan for the City of Toronto Cities feeding People Series Report 8. Ottawa: IDRC.

City Center to the Urban Fringe. [City]: North American Urban Agriculture Committee.

Community Food Security Coalition (CFSC), North American Urban Agriculture Committee. 2003. Urban Agriculture and Community Food Security in the United States: Farming from the Contributions to the Sustainability of African and Asian. In Brebbia, C. et al., (eds). The Sustainability City II.

De graaf, Paul & Jan-Willem Van der schans( ). Integrated urban agriculture in industrialised countries -design principles for locally organised food cycles in the dutch context

de Zeeuw, Henk, Marielle Dubbeling and Ann Waters-Bayer. (1998) " Integrating Agriculture into Urban Pl anning and Action: Some Options for Cities." [Paper based on two presentations]+10pp.

Deelstra T. 2000. *Urban agriculture and city ecology*. Paper presented at growing cities growing food workshop, Havana, Cuba, October 1999.

Department of agriculture of RSA( ), Learners Guide Primary agriculture ,US No: 16309)

Dongus, S. (2000): Vegetable Production on Open Spaces in Dar es Salaam - Spatial Changes from 1992 to 1999 , Accessed on 27 November, 2005 at http://www.cityfarmer.org/daressalaam.html

Dowall, D.E. and Clark, G. (1996): A Framework for Reforming Urban Land Policies In DevelopingCountries. Urban Management Programme Paper 7, World Bank, Washington DC.

Drakakis-Smith, David. (1996 (1997) "Third World Cities: Sustainable Urban Development III- Basic Needs and Human Rights." Urban Studies 34(5-6):797-823.

Drakakis-Smith, David. (1996) "Third World Cities: Sustainable Urban Development II - Popu lation, Labour and Poverty." Urban Studies 33 (4): 673-701.

Drechsel, P., C. Quansah and F. Penning de Vries. (1998) "Stimulation of Urban and Peri-urban Agri culture in West Africa- Characteristics, Challenges and Need for Action" (A paper prepared for the IDRC/CRDI Workshop on the Contribution of Urban

Agriculture to Food Security in West African Cities, Ouagadougou, Burkina Faso, Jun 15-18, 1998.
Drescher, A.W. (2001): The German allotment gardens - a model for poverty alleviation and food security in Southern African Cities? Proceedings of the Sub-Regional Expert Meeting on Urban Horticulture, Stellenbosch, South Africa, January 15 – 19, 2001, FAO/University of Stellenbosch, (2001):159-167. Accessed at online: http://www.cityfarmer.org/germanAllot.html.
Drescher, A.W. and Iaquinta, D. (1999): Urban and Periurban Agriculture: A New Challenge for the UN Food and Agriculture Organisation (FAO). FAO - Internal report. Rome.
EIAR(2012). Ethiopia Inistitut of Agricultural Resaerch

FDRE(1997. Environment policy
Foeken D and Mwangi A. 2000. *Increasing food security through urban farming in Nairobi.*
Goan, Charles ( ). Site Selection Factors for New Poultry Facilities
GRAAF Ir ,Paul DE and Jan and VAN DER SCHANS ,Willem PhD( ). Integrated Urban Agriculture in Industrialised Countries -Design Principles for Locally Organised Food Cycles in the Dutch Context
Guberman, Connie. (1995) "Sowing the Seeds of Sustainability: Plann ing for Food Self-Reliance." Pp. 111-129. In Change of Plans: Towards a Non-Sexist Sustainable City. Margrit Eichler (ed.) Toronto: Garamond Press.
Hack, Gary. (1988) "Physical Planning and Urban Design." Pp. 187-220 . In Urban Planning (2nd ed.) A.J. Catanese and J. C. Snyder (eds.) New York: McGraw-Hill.
Helmore, Kristin and Annu Ratta. (1995) "The Surprising Yields of Urban Agriculture." Choices: The Human Development Magazine 4 (1): 22-27. http://www.ruaf.org/node/961 (Accessed on July 2006)
IDRC,1999. Planning for Urban Agriculture: A Review of Tools and Strategies for Urban Planners.
Jacobi, P., Amend, J. and Kiango, S (2000): Urban Agriculture – a case study of Dar es Salaam (Tanzania). In: City Harvest – a Reader on Urban Agriculture, GTZ, Eschborn.
Jacobi, P., Amend, J. and Kiango, S. (2000): Urban Agriculture in Dar es Salaam: Providing for an Indispensable part of the Diet, in Bakker et al (2000), Pg. 257-284
Journal of Sustainable Development in Africa (Volume 12, No.3, 2010)
Kenneth Russell(1969). The Principles of Dairy Farming
Khosla, Prabha. (1993) "You Cannot Sleep Hungry, So You Should Be Able to Farm." Paper presented at the Canadian Association of African Studies Conference, Toronto, May 12-15, 1993. +14pp.
Kironde, M. Lusugga. (1992) "Received Comments and Theories in African Urbanisation and Management Strategies: The Struggle Continues." Urban Studies 29(8):1277-1292.
Klemesu M. 2000. Urban agriculture and food security, nutrition, and health.

Kyessi, A. (1997): City Expansion and Urban Agriculture in Dar es Salaam: Lessons for Planning, Journal of Building and Land Development 4 (2) P 28-37.
Lado, Cleophas (1990) "Informal Urban Agriculture in Nairobi, Kenya." Land Use Policy 7(3): 257-266 (July 1990).
Levy, John. (1991) Contemporary Urban Planning (2nd ed.) Englewood Cliffs: Prentice Hall.+296pp.
Magigi,wakuru 2008. Improving Urban Land Governance With Emphasis On Integrating Agriculture Based Livelihood In Spatial Land Use Planning Practice In Tanzania. A Thesis Submitted In Partial Fulfillment Of The Requirement For Higher Research Degree of Doctor of Natural Sciences (Dr. rer. nat.) of the Faculty of Forest and Environmental Sciences,
Margiotta, Mario. (1997) "L'agriculture Périurbaine en Panama: Une Approche Novatrice pour le Préservation de l'Environnement." Pp. 89-97. In Land Reform, Land Settlement and Cooperatives, 1997/2. Paolo Groppo (ed.) FAO. +124pp.
Maxwell, Daniel. (1994) "The Household Logic of Urban Farming in Kampala." Pp. 47-66. In Cities Feeding People: An Examination of Urban Agriculture in East Africa. A.G. Egziabher, D. Lee-Smith, D.G. Maxwell, P. AiMemon, L.J.A. Mougeot and C.J. Sawio. Ottawa: IDRC. +146pp.
Mbiba B. 1998. *Urban agriculture policy in Southern Africa: from theory to practice*.
_____. 2000. Urban agriculture in Harare: between suspicion and repression.
Mekouar, Mohamed Ali. (1997) "La Ville et la Nature." pp. 53-60. In Land Reform, Land Settlement and Cooperatives, 1997/2. Paolo Groppo (ed.). FAO. +124pp.
Menezes, Louis. (1983) "An Approach to Urban Land Policy." Pp. 34-49. In Urban Growth and Urban Planning: Political Context and People's Priorities. Alfred De Souza (ed.) New Delhi: Indian Social Institute. +163pp.
Mlozi, M.R.S., I.J. Lupanga and Z.S.K. Mvena. (1992) "Urban Agriculture as a Survival Strategy in Tanzania." Pp. 284-294. In The Rural-Urban Interface in Africa: Expansion and Adaptation (Seminar Proceedings No. 27). J. Baker and P.O. Pedersen (eds.) Uppsala: The Scandinavian Institute of African Studies.
Mlozi, M.R/ Lupanga,I. J./ Mvena, Z.S. (1992): Urban Agriculture as a Survival Strategy in Tanzania.In Bakker. J/Pedersen, P.(eds); The Rural Urban Interface in Africa-Expansion and Adaptation. Nordiska Africaka institutet, Uppsala. Pg. 284-294.
MOA( ). Dairy Extention Manual
*MOFAD*(2002).Plan for Accelerated and Sustainable Devlopment to End Poverty

Mohammed Jemal (2002).Urban Ugriculture initiatives in Addis Ababa with special evidences from selected vegetable producing copratives and housing in the city; Addis Ababa university Master thesis
Mougeot, L. *(*1993). Urban food production: evolution, official support, and significance.
Mougeot, L. (2000): *Urban agriculture: Definition, Presence, Potentials and Risks, and Policy Challenges*. Paper presented to the International Workshop "Growing Cities, Growing Food", October 11-15 1999, Havana, Cuba.
*MUDC* (2012). Stractural Plan Manual(Revised Version)

Nelliah, Vasanthi. (1999) Modèle Théorique d'Intervention Visant l'Intégratio n des Pratiques d'Agriculture Urbaine au Pratiques Municipales de Planification Urbaine. Unpublished manuscript, IDRC. +12pp.

Ohio Model(2009) http://caselaw.lp.findlaw.com/clevelandcodes/cco_part3_347.html. Program, New York, 1996.

Rakodi, C. and Devas, N. (1993): Managing Fast Growing Cities. New Approaches to Urban Planning

Sawio, C. [1998]. "Chapter Nine: Institutional and Legal Framework: Instruments of Intervention to Support Urban Agriculture in Dar Es Salaam." Unpublished manuscript. +49pp.

Sawio, C. (1998): Managing Urban Agriculture in Dar es Salaam Cities. Cities Feeding People Report 20. Ottawa:IDRC.

Smit, J. A. Ratta, and J. Nasr. 1996. Urban agriculture: Food, jobs, and sustainable cities. United

Smit, J. et al., Urban Agriculture: Food Jobs and Sustainable Cities, United Nations Development

Smit, Jac. (1996) Urban Agriculture, Progress and Prospect: 1975-2005. CFP report 18. +28pp.

Smith, Herbert H. (1993) The Citizen's Guide to Planning (3rd ed.) Chicago: American Planning Association. +267pp.

Taylor, J.L. and D.G. Williams. (1982) "Problems and Issues in Asian Urban Areas and the Response of Planning Practice." Pp. 3-45. In Urban Planning Practice in Developing Countries. John L. Taylor and David G. Williams (eds.) Toronto: Pergamon Press. +357pp.

Tinker, I. (1994). Urban Agriculture is Already Feeding Cities: In Cities Feeding People. IDRC: Ottawa. UN 1995;

UNDP, "Urban Agriculture: Food, Jobs, and Sustainable Cities", United Nations Development Programme, Publication for Habitat II, Vol. One, One UN Plaza, New York, New York, USA, 1996.

UNFPA (1993) The State of the World, United Nations Population Fund

United Nations (1990) Human Development Report: Oxford University Press

_____ *(1991)* . World Urbanization Prospects, New York

______ (2002) Press Release, POP/815, 21 March, p 1.

USAID(2002). **የኢትዮጵያ የበግና የፍዬል ምርታማነት ማሻሻያ**

USDA( ). Urban Agriculture: Differing Phenomena in Differing Regions of the World

Van den Berg, L.M. (2002): Urban Agriculture Between Allotment and Market Gardening:

Van Veenhuizen René., ed. (2006): Cities Farming for the Future, Urban Agriculture for Green and Productive Cities. Published by RUAF Foundation, IDRC and IIRR.

*World Bank* (*2008*). Urban Agriculture For Sustainable Poverty Alleviation and Food Security

_______(WB),(2008) Urban Agriculture For Sustainable Poverty Alleviation and Food Securit.

*እዝሎች*

## እዝል 1. ለከተማ ፕላን ባለሞያዎች የቀረበ መጠይቅ

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ፅዳትና ውበት ቢሮ ለከተሞች ፕላን ሥራና ለነዋሪዎቻቸው ዕድገት የሚያግዙ የተለያዩ የጥናት ሰነዶችን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ሰነዶች አንዱ የሆነው ከከተሞች ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር አንፃር የዘላቂ የከተማ ግብርና ማስፋፊያ ሰነድ በዝግጅት ላይ ሲሆን ለዚህ ጥናት የባለሞያዎች ግብአት አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ ለቀረቡት መጠይቆች በታማኝነት ትክክለኛውን መልስ በመስጠት የበኩሎን አገራዊ ድርሻ እንዲያበረክቱ በአክብሮት እንጠይቆታለን፡፡

**እናመሰግናለን**

***ማሳሰቢያ፦*** *ይህንን መጠይቅ በኢሜል የሚልኩልን ከሆነ ምርጫዎን ወይም መልሶን ቀይ ቀለም በመጠቀም ያመልክቱ፡፡ መልሶ በወረቀት ከሆነ ከፊት ለፊቱ የ "X" ምልክትን በመጠቀም ያመልክቱ፡፡*

**ክፍል አንድ፡የምላሽ ሰጪዎች የግል መረጃ የተመለከቱ ጥያቄዎች**

101.ክልል/ዞን…………………………………………………………

102.የመስሪያቤቶ ስልክ ቁጥር………………………………………

103.የራስዎ ኢ-ሜይል አድራሻ………………………………………

**ክፍል ሁለት፡የከተማ ፕላንና የከተማ ግብርና የተመለከቱ መጠይቆች**

205. በከተማው በተዘጋጁ ማንኛውም ሰነድ ውስጥ በመደገፍም ሆነ በመቃወም የከተማ ግብርና የተመለከቱ ጉዳዮች አሉ? አዎ……….. የለም……… አላውቅም……………

መልሶ አዎ ከሆነ የሰነዱን ስም ብቻ ቢገልገፁ…………………………………………………

206.የከተማ ግብርና የተመለከቱ ጉዳዮች በሀገሪቱም ሆነ በክልል ደረጃ በየትኛው ሰነድ ውስጥ ይገኛሉ

…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………

207.የከተማው አስተዳደር ስለከተማ ግብርና ያለውን አቋም በየትኛው ውስጥ ይመድቡታል

------- በህግ ፈቅዶ ድጋፍ ጭምር እየሰጠ ይገኛል

------ ፈቃድ ቢሰጥውም ድጋፍ እያደረገለት አይደለም

-------- ምንም የሚለው የለም (ኒውትራል ነው)

------- ፈቃድ ቢሰጥም በአፈፃፀም ላይ እምብዛም ነው

-------- በህግ ይከለክላል

208. በእርሶ አመለካከት የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥ ተገቢ ነው ይላሉ? አዎ…….. አይደለም……… አላውቅም………

209. የትኞቹ የከተማ ግብርና ሥራዎች በከተማ ውስጥ ፈቃድ ለያገኙ ይገባል ይላሉ?

------ የጓሮ አትክልት

-------- ሌሎች ለሰውና ለእንስሳ መኖነት የሚያገለግሉ ሰብሎችን መትከል

--------- የፍራፍሬ ዛፎችን መትከል

-------- የደን ዛፎችን መትከል

------- አበቦችንና የውበት ተክሎችን መትከል

------ ትንንሽ ለማዳ እንስሳትን ማርባት

------- ትልልቅ ለማዳ እንስሳትን ማርባት

-------- የአሳ ምርት

----- የንብ ዕርባታ

----- ቆሻሻ ውሃን ለመስኖ ሥራ ማዋል

------ የቤት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

------ የሽንት ቤት ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

------ የከተማው ምርት ውጤትን ለገበያ ማቅረብና ማከፋፈል

------- ሌሎች ካሉ-------------------------

210. በከተማዎ የከተማ ግብርና እየሰጠ ያለው ጥቅሞችን በዝርዝር ቢገልጹ

211. በከተማዎ በከተማ ግብርና ምክንያት የመጣ ችግር/ጉዳት ካለ ቢገልጹ

**ክፍል ሦስት፡ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴዎች የት መሆን አለባቸው በሚሉ ጉዳዮች የቀረቡ መጠይቆች**

301. በከተማዎ የከተማ ግብርና ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?

302. በከተማዎ የከተማ ግብርና የሚያካሂዱ አካላት እነማናቸው

……. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች

…….. በባለሃብቶች

…… በከተማ ዳርቻ በሚኖሩ አርሶ አደሮች

…… ነዋሪ ግለሰቦች

…… መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች(NGO)

------- ሌሎች………………………………………………………………………………

303. በከተማዎ ለግብርና ሥራ መዋል አለባቸው የሚሉዋቸው ሥፍራዎች አሉ? አዎ-----የለም-----አላውቅም---

መልሶ አዎ ከሆነ ቢገልፁ…………………………………………….................................................

…………………………………………………………………………………………………………..

304. የከተማዎ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ክፍፍል ውስጥ ለከተማ ግብርና ብቻ የሰጠው ድርሻ አለ? አዎ---------- አልሰጠም-------------- አላውቅም-----------

መልሶ አዎ ከሆነ ለከተማ ግብርና የተሰጠው/የተመደበውውን ቦታ እንዴት ይገመግሙታል …………………………………………………………………………………………………… …………………………………………………………………………………………………… ……………………………………………………………………………………………………

305. በከተማዎ የከተማ ግብርና ቦታ የሚሰጠው እንዴት ነው? በምን እይነት አግባብ ነው?

**ክፍል አራት፡የከተማ ግብርናን የመምራት ሀላፊነት በተመለከተ**

401. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ለመምራት፣ቴክኒካዊ ድጋፍ ለመስጠትና ለመቆጣጠር ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ?

አዎ………. የለም……….. አላውቅም……………….

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ……………………………………………………………………………………….

402. በከተማዎ የከተማ ግብርና ፖሊሲና ስትራቴጂ አለ? ........................................................

403. በከተማዎ የከተማ ግብርናን በተመለከተ ስትራቴጂ፣ መመሪያና ደንብ ለማውጣት ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ? አዎ………….. የለም………. አላውቅም………………..

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ……………………………………………………………………………………………

404. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ሥፍራዎችን ለመለየት ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ?

አዎ…………… የለም……………… አላውቅም…………………………

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ………………………………………………………………………………………………

405. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ሥፍራዎችን ለመለየት ሃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት ቅንጅት እንዴት ይገልፁታል

**ክፍል አምስት፡ዋናዋና የከተማ ግብርና ማነቆዎችን የተመለከቱ ጥያቄዎች**

501. በከተማዎ ለከተማ ግብርና ማነቆዎች ናቸው የሚሉአቸውን ከሚከተሉት ዝርዝሮች አምስቱን ዋናዋና ችግሮች ብቻ መርጠው በቅደም ተከተላቸው ቁጥር በመስጠት ምልክት ያድርጉባቸው።

------ የመሬት አቅርቦት/ተደራሽነት ችግር (accessibility)

----- የመሬት እጥረት (availability)

----- የመሬት ይዞታ ዋስትና አስተማማኝነት ችግር

------ የከተማ ግብርና በከተማ መዋቅራዊ ፕላን (የመሬት ክፍፍል) ውስጥ እውቀና ማጣት

------ የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻር የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማነስ

-------- የከተማ ግብርናን ለመደገፍ የተሟላ የፖሊሲ የስትራቴጂና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር

-------- የከተማ ግብርናውን ለመምራት ውጤታማ የሆነ ሥርዓት አለመኖር

-------- የከተማ ግብርናን ለመደገፍ በፕሮግራም የሚመራ ቴክኒካዊ አገልግሎት አለመኖር

------- ለገበሬዎች የማስቻያ የብድር አገልግሎት አለመኖር

------ የአገልግሎት አቅርቦት አለመሟላት ለምሳሌ የግብአትና የመሳሰሉት

------ የመሠረተ-ልማት አለመሟላት ለምሳሌ የገበያ ማእከላት፣ የተራንስፖርትና ውሀ የመሳሰሉት

------ በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች የመረጃ እና የዕውቀት እጥረት

------ ሌላ ካለ ቢገለፅ-------------------------------------------------------------------------------

502. ከላይ የተገለፁ ማነቆዎች ለወንድና ለሴት ገበሬዎች ተመሳሰይ ነው? አዎ………. አይደለም……… አላውቅም…………………

**ክፍል ስድስት፡የከተማ ግብርና ማነቆዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና መሳሪያዎች**

601. የከተማ ግብርና በስፋት ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድርግ በከተማዎ እየተወሰደ ያለ እርምጃ አለ? አለ-------------- ምንም ነገር የለም------------ አላውቅም-------------------------------

ከላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ ከሚከተሉት የትኞቹ ናቸው?

---- በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ ብቻውን እንዲካተት ዕውቅና ምስጠት

---- ለከተማ ግብርና ቢሆኑ የሚሻሉ የከተማ ዞኖችን መለየት

----- ለከተማ ግብርና ሥርዓት በማጀት መደገፍ

---- ለከተማ ገበሬዎች የመሬት አቅርቦትን ማቀላጠፍ

--- ለከተማ ገበሬዎች የሌሎች ግብአት አቅርቦትን ማቀላጠፍ

--- ለከተማ ገበሬዎች ልዩ የቴክኒካዊ እገዛና የምክር አቅርቦትን ማቀለቀጠፍ

--- ለከተማ ገበሬዎች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማቀላጠፍ

ሌሎች ካሉ ቢገለፅ……………………………………………………………

**ክፍል ሰባት፡ ወደፊት ሊሰሩ የሚገባቸው አስፈላጊ ነገሮችና ቅድመ-ሁኔታዎች**

701. ለከተማ ግብርና ችግሮች መፍትሄ ናቸው ወይም ሊሚሉ ይገባል የሚሉአቸውን ግብአቶች ቢገልፁ

702. የከተማ ግብርናን በተገቢው ሁኔታ ለመምራት በከተማዎ የወደፊት እርምጃዎች ወይም ቀዳሚ ጉዳዮች ምንድናቸው ይላሉ?

703. የከተማው አስተዳደር በከተማ ግብርና ጉዳዮች ላይ የሚሰበስባቸው ስታትስቲካዊ መረጃዎች አሉ? አዎ……… የሉም………… አላውቅም……….

መልስዎ አዎን ከሆነ፤ ምን አይነት መረጃዎች ናቸው ያሉት?

704. የከተማ ግብርና ሥራን በከተማዎ ለማቀላጠፍ የፕላን አዘጋጆችና ፈጻሚዎች ቡድንስ ምን ምን ሥራዎችን መሥራት አለበት ይላሉ?

## እዝል 2 ለግብርና ባለሞያዎች የቀረበ መጠይቅ

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ፅዳትና ውበት ቢሮ ለከተሞች ፕላን ሥራና ለነዋሪዎቻቸው ዕድገት የሚያግዙ የተለያዩ የጥናት ሰነዶችን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ሰነዶች አንዱ የሆነው ከከተሞች ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር አንፃር የዘላቂ የከተማ ግብርና ማስፋፊያ ሰነድ በዝግጅት ላይ ሲሆን ለዚህ ጥናት የባለሞያዎች ግብአት አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ ለቀረቡት መጠይቆች በታማኝነት ትክክለኛውን መልስ በመስጠት የበኩሎን አገራዊ ድርሻ እንዲያበረክቱ በአክብሮት እንጠይቆታለን፡፡

**እናመሰግናለን**

ማሳሰቢያ፦ ይህንን መጠይቅ በኢሜል የሚልኩልን ከሆነ ምርጫዎን ወይም መልሶን ቀይ ቀለም በመጠቀም ያመልክቱ፡፡መልሶ በወረቀት ከሆነ ከፊት ለፊቱ የ “X” ምልክትን በመጠቀም ያመልክቱ፡፡

**ክፍል አንድ፡የምላሽ ሰጪዎች የግል መረጃ የተመለከቱ ጥያቄዎች**

101. ክልል/ዞን…………………………………………………………….

102. የመስሪያ ቤትዎ ስልክ ቁጥር……………………………………….

103. የራስዎ ኢ-ሜይል አድራሻ……………………………………….

**ክፍል ሁለት፡የከተማ ፕላንና የከተማ ግብርና የተመለከቱ መጠይቆች**

201. በከተማዎ የትኞቹ የከተማ ግብርና ዓይነቶች ይካሄዳሉ?

------- የጓሮ አታክልት

------- የፍራፍሬ ዛፎች

------- ሌሎች ለሰውና ለእንስሳ መኖ የሚውሉ ተክሎች

------- የደን ዛፍ መትከል

------- አበቦችና ሌሎች  የውበት ተክሎችን መትከል

------- ትንንሽ ለማዳ እንስሳትን ማርባት (ፍየል፣ በግ፣ ዶሮ…)

------- ትልልቅ ለማዳ እንስሳትን ማርባት (በሬ፣ ላም…)

------- የዓሳ እርባታ

------ የንብ እርባታ

------- የእንጉዳይ ምርት

------- ሌሎች ካሉ ይገለፅ…………………………………………………………

-------- አላውቅም

-------- ምንም በግልፅ የሚታይ የከተማ ግብርና ዓይነት የለም

202.**በከተማዎ የከተማ ግብርናው የሚጠቀማቸው ግብአቶች**

----- ቆሻሻ ውሃን ለመስኖ ሥራ

----- የቤት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

----- የሽንት ቤት ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

------ ማዳበሪያ

------ ምርጥ ዘር

------ ተባይ ማጥፊያ

------ አረም ማጥፊያ

------ በሽታ ማጥፊያ

------- ማቀዝቀዣ

ዘመናዊ መሳሪያዎች ካሉ ቢጠቀስ…………………………………………………………

ሌሎች ካሉ…………………………………………………………………………

203.የከተማ ግብርና የምርት አጠቃቀምን በተመለከተ

------ ለቤት ውስጥ ፍጆታ

------- የከተማው ምርት ውጤትን ለገበያ ማቅረብና ማከፋፈል

ምርትን ለኢንዱስትሪ በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም የሚገኙ ምርቶች ካሉ ይግለፁ……………………………………………………………………………

------- ሌሎች ካሉ ……………………………………………………………………………

204. በከተማ ግብርና እንቅስቃሴዎች የተደረጉ ማንኛው እገዳዎች ካሉ ቢገልፁ

የት ቦታ………………………………………………………………………..

በዚህ እንቅስቃሴ ተጎጂ ተሳታፊዎች………………………………………………..

እገዳውን ያደረገ አካል ………………………………………ለምን………………………………..

205. በከተማው በተዘጋጁ ማንኛውም ሰነድ ውስጥ በመደገፍም ሆነ በመቃወም የከተማ ግብርና የተመለከቱ ጉዳዮች አሉ? አዎ……….. የለም……… አላውቅም……………

መልሶ አዎ ከሆነ የሰነዱን ስም ብቻ ቢገልገፁ…………………………………………………

206. የከተማ ግብርና የተመለከቱ ጉዳዮች በሀገሪቱም ሆነ በክልል ደረጃ በየትኛው ሰነድ ውስጥ ይገኛሉ

…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………..

207. የከተማው አስተዳደር ስለከተማ ግብርና ያለውን አቋም በየትኛው ውስጥ ይመድቡታል

------- በህግ ፈቅዶ ድጋፍ ጭምር እየሰጠ ይገኛል

------ ፈቃድ ቢሰጥውም ድጋፍ እያደረገለት አይደለም

------- ምንም የሚለው የለም (ኒውትራል ነው)

------- ፈቃድ ቢሰጥም በአፈፃፀም ላይ እምብዛም ነው

-------- በህግ ይከለክላል

208. በእርሶ አመለካከት የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥ ተገቢ ነው ይላሉ? አዎ…….. አይደለም……… አላውቅም………

209. የትኞቹ የከተማ ግብርና ሥራዎች በከተማ ውስጥ ፈቃድ ለያገኙ ይገባል ይላሉ?

------ የጓሮ አትክልት

-------- ሌሎች ለሰውና ለእንስሳ መኖነት የሚያገለግሉ ሰብሎችን መትከል

--------- የፍራፍሬ ዛፎችን መትከል

-------- የደን ዛፎችን መትከል

------- አበቦችንና የውበት ተክሎችን መትከል

------ ትንንሽ ለማዳ እንስሳትን ማርባት

------- ትልልቅ ለማዳ እንስሳትን ማርባት

------- የአሳ ምርት

----- የንብ ዕርባታ

----- ቆሻሻ ውሃን ለመስኖ ሥራ ማዋል

------ የቤት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

------ የሽንት ቤት ቆሻሻን ለማዳበሪያነት መጠቀም

------ የከተማው ምርት ውጤትን ለገበያ ማቅረብና ማከፋፈል

------- ሌሎች ካሉ-------------------------

210.በከተማዎ የከተማ ግብርና እየሰጠ ያለው ጥቅሞችን በዝርዝር ቢገልጹ

211. በከተማዎ በከተማ ግብርና ምክንያት የመጣ ችግር/ጉዳት ካለ ቢገልጹ

## ክፍል ሦስት፡ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴዎች የት መሆን አለባቸው በሚሉ ጉዳዮች የቀረቡ መጠይቆች

301.በከተማዎ የከተማ ግብርና ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?

302. በከተማዎ የከተማ ግብርና የሚያካሂዱ አካላት እነማናቸው

…….ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች

……..በባለሃብቶች

……በከተማ ዳርቻ በሚኖሩ አርሶ አደሮች

……ነዋሪ ግለሰቦች

……መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች(NGO)

-------ሌሎች…………………………………………………………………………….

303. በከተማዎ ለግብርና ሥራ መዋል አለባቸው የሚሉዋቸው ሥፍራዎች አሉ? አዎ----- የለም----- አላውቅም----------------

መልስዎ አዎ ከሆነ ቢገልፁ……………………………………………….............................................

…………………………………………………………………………………………………………….

304. በከተማዎ የከተማ ግብርና ቦታ የሚሰጠው እንዴት ነው? በምን እይነት አግባብ ነው?

## ክፍል አራት፡የከተማ ግብርናን የመምራት ሀላፊነት በተመለከተ

401. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ለመምራት፣ቴክኒካዊ ድጋፍ ለመስጠትና ለመቆጣጠር ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ?

አዎ………. የለም……….. አላውቅም……………….

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ……………………………………………………………………………………….

402. በከተማዎ የከተማ ግብርና ፖሊሲና ስትራቴጂ አለ? ......................................................

403. በከተማዎ የከተማ ግብርናን በተመለከተ ስትራቴጂ፣ መመሪያና ደንብ ለማውጣት ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ? አዎ………….. የለም………. አላውቅም………………..

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ…………………………………………………………………………………………….

404. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ሥፍራዎችን ለመለየት ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ?

አዎ…………… የለም……………… አላውቅም…………………………

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ…………………………………………………………………………………………………

405. በከተማዎ የከተማ ግብርና ሥራዎች ላይ የተሰማሩትን ለመመዝገብ ወይም ለመፍቀድ ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም አለ? አዎ--------- የለም--------------- አላውቅም-------------------

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ እባክዎ ሃላፊነት ያለውን የተቋም ስም ቢገልፁ---------------

406. በከተማዎ የከተማ ግብርናን ሥፍራዎችን ለመለየት ሃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት ቅንጅት እንዴት ይገልፁታል

## ክፍል አምስት፡ ዋና ዋና የከተማ ግብርና ማነቆዎችን የተመለከቱ ጥያቄዎች

501. በከተማዎ ለከተማ ግብርና ማነቆዎች ናቸው የሚሉአቸውን ከሚከተሉት ዝርዝሮች አምስቱን ዋና ዋና ችግሮች ብቻ መርጠው በቅደም ተከተላቸው ቁጥር በመስጠት ምልክት ያድርጉባቸው።

1. የመሬት አቅርቦት/ተደራሽነት ችግር (accessibility)
2. የመሬት እጥረት(availability)
3. የመሬት ይዞታ ዋስትና አስተማማኝነት ችግር
4. የከተማ ግብርና በከተማ መዋቅራዊ ፕላን (የመሬት ክፍፍል) ውስጥ እውቅና ማጣት
5. የከተማ ግብርናን ከማስፋፋት አንጻር የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ማነስ
6. የከተማ ግብርናን ለመደገፍ የተሟላ የፖሊሲ የስትራቴጂና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር
7. የከተማ ግብርናውን ለመምራት ውጤታማ የሆነ ሥርዓት አለመኖር
8. የከተማ ግብርናን ለመደገፍ በፕሮግራም የሚመራ ቴክኒካዊ አገልግሎት አለመኖር
9. ለገበሬዎች የማስቻያ የብድር አገልግሎት አለመኖር
10. የአገልግሎት አቅርቦት አለመሟላት ለምሳሌ የግብአትና የመሳሰሉት
11. የመሠረተ-ልማት አለመሟላት ለምሳሌ የገበያ ማእከላት፣ የተራንስፖርትና ውሀ የመሳሰሉት
12. በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች የመረጃ እና የዕውቀት እጥረት
13. ሌላ ካለ ቢገለፅ----------------------------------------------------------------------------------

502. ከላይ የተገለፁ ማነቆዎች ለወንድና ለሴት ገበሬዎች ተመሳሳይ ነው? አዎ………. አይደለም……… አላውቅም…………………

## ክፍል ስድስት፡ የከተማ ግብርና ማነቆዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና መሳሪያዎች

601. የከተማ ግብርና በስፋት ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድርግ በከተማዎ እየተወሰደ ያለ እርምጃ አለ? አለ-------------- ምንም ነገር የለም ------------ አላውቅም ------------------------------

ከላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መልሶ አዎ ከሆነ ከሚከተሉት የትኞቹ ናቸው?

---- በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ ብቻውን እንዲካተት ዕውቅና ምስጠት
---- ለከተማ ግብርና ቢሆኑ የሚሻሉ የከተማ ዞኖችን መለየት
----- ለከተማ ግብርና ሥርዓት በማጀት መደገፍ
---- ለከተማ ገበሬዎች የመሬት አቅርቦትን ማቀላጠፍ
---- ለከተማ ገበሬዎች የሌሎች ግብአት አቅርቦትን ማቀላጠፍ
---- ለከተማ ገበሬዎች ልዩ የቴክኒካዊ እገዛና የምክር አቅርቦትን ማቀለቀጠፍ
---- ለከተማ ገበሬዎች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማቀላጠፍ

ሌሎች ካሉ ቢገለፅ……………………………………………………………

## ክፍል ሰባት፡ ወደፊት ሊሰሩ የሚገባቸው አስፈላጊ ነገሮችና ቅድመ-ሁኔታዎች

701. ለከተማ ግብርና ችግሮች መፍትሄ ናቸው ወይም ሊሚሉ ይገባል የሚሉአቸውን ግብአቶች ቢገልፁ

702. የከተማ ግብርናን በተገቢው ሁኔታ ለመምራት በከተማዎ የወደፊት እርምጃዎች ወይም ቀዳሚ ጉዳዮች ምንድናቸው ይላሉ?

703. የከተማው አስተዳደር በከተማ ግብርና ጉዳዮች ላይ የሚሰበስባቸው ስታትስቲካዊ መረጃዎች አሉ? አዎ……… የሉም………… አላውቅም……….

መልስዎ አዎን ከሆነ ፤ምን አይነት መረጃዎች ናቸው ያሉት?

704. የከተማ ግብርና ሥራን በከተማዎ ለማቀላጠፍ የፕላን አዘጋጆችና ፈጻሚዎች ቡድንስ ምን ምን ሥራዎችን መሥራት አለበት ይላሉ?

## እዝል 3 ለከተማ ገበሬዎች የቀረበ የቃል መጠይቅ

1. የገበሬው/የማህበሩ የግል መረጃ

    ስም

    የትምህርት ደረጃ

    የኑሮ ደረጃ

    የቤተ ሰብ ሁኔታ

2. ግብርናውን የጀመሩበት ጊዜ መቼ ነው
3. ሥራውን ለመጀመር የወሰኑበት ምክንያት ምንድነው
4. አሁን እየሰሩ ያሉት የግብርና ዓይነት ምንድነው
5. እየተጠቀሙ ያሉት ግብዓትቶች ምን ምን ናቸው
6. ግብርናው እየሰጦት ያለው ጥቅም ምንድነው
7. በሥራው ላይ ያጋጠሞት ችግር ምንድነው
8. እየሰሩ ያሉት ግብርና የሚያስከትለው ችግር አለ
9. ለግብርና ሥራዎ የተሰጠ ያለው ድጋፍ ምንድነው
10. አሁን ለሥራዎ የሚፈልጉት ድጋፍ ምንድነው
11. እየሰሩ ያሉበትን ቦታ እንዴት አገኙት

## እዝል 4 ለዳሰሳው ጥናት የታቀፉ ከተሞች

1. አዲስ አበባ 2. ሞጆ 3. ቢሾፍቱ 4. አዳማ 5. መቀሌ 6. አዋሳ 7.ባህርዳር

በዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ባለሞያዎች

**በዚህ ምላሽ የሰጡ ናሙና ባለሞያዎች መሥሪያ ቤት ዝርዝር**

| የግብርና ባለሞያዎች | የፕላን ባለሞያዎች |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ግብርና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ ፕላን ኢንስቲትዩት |
| የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስትቲዩት | ኦሮሚያ ፕላን ኢንስቲትዩት |
| አዲስ አበባ የከተማ ግብርና የሥራ ሂደት | ትግራይ ፕላን ኢንስቲትዩት |
| አዳማ የከተማ ግብርና የሥራ ሂደት | አዳማ የከተማ አስተዳደር የፕላንና የአካባቢ ጥበቃ የሥራ ሂደት |
| ቢሾፍቱ የከተማ ግብርና የሥራ ሂደት | ቢሾፍቱ የከተማ አስተዳደር የፕላንና የአካባቢ ጥበቃ የሥራ ሂደት |
| | ሞጆ የከተማ አስተዳደር የፕላንና የአካባቢ ጥበቃ የሥራ ሂደት |